# እጩ መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በመተግበር ሂደት የተጣለባቸውን ሐላፊነት የመወጣት ብቃት


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ

አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


ተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ተሰራ አስማረ



የካቲት 2003

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ

አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# እጩ መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በመተግበር ሂደት የተጣለባቸውን ሐላፊነት የመወጣት ብቃት

በ

ተሰራ አስማረ

የካቲት 2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ጌታቸው አዱኛ (ዶክተር) ________________

አማካሪ ፊርማ

ጌታሁን አማረ (ዶክተር) ________________

ፈታኝ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋ.ጥ.ተ. ቤተ መጻሕፍት ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተገቢውን አቅጣጫ ተከትሎ ከፍጻሜ መድረስ ይችል ዘንድ የነበረኝን ጥረት ቅንነትና ግልጽነት ያልተለየው ምክር፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶክተር ጌታቸው አዱኛ የከበረ ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ የሚያግዝ በጀት በመመደብና ትምህርቱ መርሃ ግብሩን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ በመምራት፣ በማስተባበርና፣ በማስተማር እውቀት ላስጨበጠኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋምና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ምስጋና ይገባዋልና አመስግናለሁ፡፡የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትና የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅም ሙሉ ወጭዬን ሸፍነው ይህን የትምህርት እድል ስለሰጡኝ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ባለቤቴ ወ/ሮ ስለናት አለምነህና ልጆቼ ለመለያየትና ናፍቆት ሳትበገሩ እኔን እያበረታታችሁና የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ እየሰጣችሁ ለዚህ እንድበቃ አድርጋችሁኛልና የላቀ ምስጋናዬ ይገባችኋል፡፡ እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን! እህቴ ልኮነሽ አለምንህና ወንድሜ ደረጀ መንግስቱ ትምህርቴን ጀምሬ እስከምጨርስ ላደረጋችሁልኝ ወሰን የለሽ ድጋፍ ምስጋናዬ የላቀና የጠለቀ ነው፡፡

ወንድሞቼ፣ እህቶቼ፣ ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ በስልክና በአካል፣ በምክርና በሞራል ላደረጋችሁልኝ እገዛና ማበረታታት ምስጋና ይገበችኋል::

መጠይቆችን በመሙላት፣ ቃለመጠይቆችን በመመለስና ለስራ ስንቀሳቀስ ትብብር በማድረግ እግዛ ላደረጉልኝ እጩ መምህራን፣ አጋር መምህራን፣ ርእስ መምህራን፣ ምክትል ርእሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለቅን ተግባራቸውሁ ባይመጥንም ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ጥናቱን ቅንነት ባልተለየው ትጋትና በጥራት በመተየብ ትልቅ እገዛ ላደረገችልኝ ወ/ሮ ወይንሸት አሸናፊም የከበረ ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ማውጫ ---------- I

ምስጋና---------- II

የሠንጠረዦች ማውጫ ---------- III

የአባሪዎች ማውጫ ---------- IV

አጠቃሎ ---------- V

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ---------- 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------- 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግሮች ---------- 6

1.3 የጥናቱ ዓላማ ---------- 7

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ---------- 8

1.5 የጥናቱ ወሰን---------- 9

1.6 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች---------- 10

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ---------- 12

2.1 የመምህራን ስልጠና ታሪካዊ ዳራ---------- 12

2.2 የመምህራን ስልጠና አስፈላጊነት ---------- 14

2.3 በመምህራን ስልጠና ውስጥ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አስፈላጊነት ---------- 16

2.4 ከትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚጠበቁ ግቦች---------- 17

2.5. የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የአፈጻጸም መርሆዎች ---------- 18

2.6 የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን አስመልክቶ የተሰሩ ሀገር በቀል ጥናቶች ---------- 20

ምዕራፍ ሦስት


የጥናቱ ዘዴ ---------------------------------------------------------------- 24

3.1 የአጠናን ዘዴ ---------------------------------------------------------- 24

3.2 የመረጃ ምንጮች ------------------------------------------------------ 25

3.2.1 አብማ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ------------------ 26

3.2.2 ድብዛ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ------------------ 26

3.2.3 ንጉስ ተክለሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ------------------------------------------------------ 27

3.2.4 የእንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት -------------- 28

3.3 የናሙና አመራረጥ ---------------------------------------------------- 29

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ------------------------------------------ 30

3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ ---------------------------------------------------- 30

3.4.2 ቃለ መጠይቅ ------------------------------------------------------ 31

3.4.3 ምልከታ --------------------------------------------------------- 32

3.5 የመረጃዎች አተናተን ------------------------------------------------- 33


ምዕራፍ አራት


የመረጃዎች አቀራረብና አተናተን ------------------------------------------------ 35

4.1 የመረጃዎች ትንተና --------------------------------------------------- 36

4.1.1 ለእጩ መምህራን ከቀረበው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ------- 37

4.1.2 ለአጋር መምህራንን ከቀረበው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ---- 57


ምዕራፍ አምስት


ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣብ ----------------------------------------------- 76

5.1ማጠቃለያ ---------------------------------------------------------- 76

5.2.የመፍትሔ ሃሣብ ----------------------------------------------------- 78

ዋቢ መጻህፍት ---------------------------------------------------------- 80

ገጽ


ሠንጠረዥ 1፡ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያሠማራው ኮሌጅ የሠጠው ተልእኮ ተገቢነት ---------- 37

ሠንጠረዥ 2፡እጩ መምህራን በራስ አገዝ ዘዴ ከትምህርት ቤት ተሞክሮ ለመማር የሚያደረጉት ጥረት ---------- 40

ሠንጠረዥ 3፡የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያላቸው ዝግጅት ---------- 42

ሠንጠረዥ 4፡እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ ተግባራት ለመማር እያደረጉት ያለው ጥረት ---------- 44

ሠንጠረዥ 5፡እጩ መምህራንና የትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር ያላቸው ግንኙነት 46

ሠንጠረዥ 6፡ የእጩ መምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት ---------- 48

ሠንጠረዥ 7፡አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚያደርጉትን እገዛ ---------- 51

ሠንጠረዥ 8፡እጩ መምህራን በተጓዳኝ ትምህርት ያላቸው ተሣትፎ ---------- 53

ሠንጠረዥ9፡የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለሰልጠና ያሠማራቸውን እጩ መምህራን የሚከታተልበት ሁኔታ ---------- 54

ሠንጠረዥ 10፡የመምህራን ኮሌጁና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመርሃ ግብር መጠጣም ---------- 56

ሠንጠረዥ 11፡በመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን መርሀ ግብር መጣጣም ---------- 58

ሠንጠረዥ 12፡ በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እጩ መምህራን እያደረጉት ያለው ራስ አገዝ ጥረት ---------- 59

ሠንጠረዥ 13፡ እጩ መምህራን ከሌሎች መደበኛ መምህራንና ከአጋር መምህሮቻቸው ጋር ያላቸው ትብብርና ያመጡት ሙያዊ መሻሻል ---------- 60

ሠንጠረዥ 14፡የእጩ መምህራን ንድፈ ሃሣብን ወደ ተግባር የመለወጥ አቅም -- 62

ሠንጠረዥ 15፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ለእጩ መምህራን ተግባራዊ ስልጠና የሠጠው ትኩረት---------- 63

ሠንጠረዥ 16፡ አጋር መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም የሠጡት ትኩረት ---------------------------------- 65
ሠንጠረዥ 17፡ እጩ መምህራን ለአጋር መምህራን ግብረ መልስ የሰጡት ትኩረት-66
ሠንጠረዥ 18፡የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እያደረገው ያለው ድጋፍና ክትትል ------------------------------------------------------------ 68
ሠንጠረዥ19፡አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት ------------------------------------------------------------ 72

## የአባሪዎች ማውጫ

ገጽ

አባሪ 1፣በእጩ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ ------------------------------------------------------------------ 83

አባሪ 2፣ለአጋር መምህራን/ Mentors/የቀረበ መጠይቅ ------------------------------------------ 86

አባሪ 3፣ለርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርባይዘሮች

የቀረበ ቃለ መጠይቅ--------------------------------------------------------------------------- 89

አባሪ 4፣ የምልከታ መከታተያ ቅጽ ------------------------------------------------------------------------ 91

አባሪ 5፣ ለቃለ መጠይቁ የተሰጠ ምላሽ ------------------------------------------------------------------ 92

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ እጩ መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሂደት የተጣለባቸውን ሀላፊነት የመወጣት ብቃት መመርመር ነው። ይህን አላማ መሰረት በማድረግ የጥናቱን አነሳሽ ችግሮች ለመመርር ገላጭ የምርምር ስልት በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ለጥናቱ መሳካት ከአራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 92 እጩ መምህራንና 62 አጋር መምህራን በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች የተሰበሰቡት በዋነኛነት ለእጩ መምህራንና ለአጋር መምህራን በተዘጋጁ መጠይቆች ሲሆን ቃለ መጠይቅና ምልከታም በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በአገልግሎት ላይ ውለዋል። በቃለ መጠይቅ መረጃ የተሰበሰበው ከአራቱ ትምህርት ቤቶች ርእሰ መምህራን፣ምክትል ርእሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ነው። ምልከታው የተከናወነው ደግሞ በትምህርት ቤቶች አጠቃላይ እንቅስቃሴና በእጩ መምህራን ተሳትፎና ግንኙነት ላይ ነው። በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በሰንጠረዥና በገለጻ ተተንትነው ያሳዩት ውጤት በገለጻ ተጠቃሏል። በውጤቱ መሰረትም እጩ መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በመተግበር ሂደት የአላቸው የአፈጻጸም ብቃት ከተወሰኑ ችግሮች ባሻገር በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ጥናቱ አመልክቷል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ትምህርት ኢ- መደበኛ ወይም መደበኛ በሆነ መንገድ ሊገኝ የሚችል የባህርይ ለውጥ ሲሆን ለውጡም የተለያዩ ክስተቶችን የሚያስተናግድ እንደሆነ አመልካች መረጃዎች አሉ። ይህን ሁኔታ Mangal (2007:35) ሲያብራሩ በአንዳች ሁኔታ ላይ የተማርነው አዲስ ነገር ቀደም ሲል በነበረን እውቀት ላይ ተፅእኖ አለው የሚለው አመለካከት አይቀሬ ሀሳብ ለመሆኑ ማረጋገጫ ዋስትና የለውም። አዲስ የተማርነው ነገር አንዳንድ ጊዜ ለነበረን እውቀት ማጠናከሪያ ሲሆን አንዳድ ጊዜ ደግሞ ለሌላው አፈጻፀም እንቅፋት የሚሆንበት ጊዜ አለ። ከዚህም በመነሳት የትምህርትን ሽግግር ሦስት ገፅታዎች መስጠት ይቻላል። እነዚህም አወንታዊ ሽግግር/ Positive Transfer/፣ አሉታዊ ሽግግር/ Negative transfer/ እና አልቦ ሽግግር/ zero transfer/ ናቸው በማለት ይገልፁታል። በመሆኑም አዲስ የሚገኘው ትምህርት ተማሪው ቀደም ሲል በነበረው እውቀት ላይ ማጠናከሪያ ሊሆን እንደሚችል ወይም የነበረውን ባህርይ ሊያስጥለው (ሊያስተወው) እንደሚችል፣ አለበለዚያም በነበረው ባህሪ ላይ ምንም አይነት ለውጥ ሳያመጣ በአዲስነት ሊዳብር እንደሚችል የሚያመለክቱ ሀሳቦች ናቸው።

መደበኛ የሆነው ትምህርት ባህሪ፣ እውቀት፣ ክህሎትና የመሳሰሉት በታቀደና በቀለጠፈ መንገድ የሚተገበሩበት ዘዴ ነው። ይህን ሁኔታ በተሳካ መንገድ ለመፈፀም ደግሞ ስልጠና በመሳሪያነት ያገለግላል። በየትኛውም የሙያ መስክ ለሚሰጡ ስልጠናዎች ሁለት አበይት ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው Walter (1960:50) ባቀረቡት ገለጻ ውስጥ ያብራራሉ። እነዚህም አበይት ተግባራት የንድፈ ሀሳብ ትምህርትና የተግባር ልምምድ ናቸው። የንድፈ ሀሳብ ትምህርቱ የአንድን ነገር የማከናወኛ ደንቦችና አጋዥ ጥናቶችን ጠቋሚ ሲሆን፣ ተግባራዊ ልምምዱ ደግሞ በሙያው ላይ ተግባራዊ ተሳትፎና እውናዊ ሙከራ በማድረግ ክህሎት የሚዳብርበት መንገድ ነው። በማለት ይገልፁታል። መምህርነትም የማስተማር ተግባር የሚከወንበት በመሆኑ በስልጠና ላይ ያሉ እጩ መምህራን የንድፈ ሀሳብ ትምህርትና የተግባር ልምምድ በማድረግ እውቀትና ክህሎታቸውን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑን የተጠቀሱት ምሁር ገለጻ ያስረዳል።

መምህራንን የማስልጠን ተግባር በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተካትቶ የሚከናወን ሲሆን የመጀመሪያውና ዋነኛው ክፍል እጩ መምህራን የመምህርነትን ሙያ እውቀት የሚያገኙበት ተግባር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ያገኙትን ንድፈ ሀሳባዊ እውቀት በተግባራዊ ልምምድ የሚያዳብሩበት እንደሆነ በማብራራት Ellis (1986:90) ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ያጠናክሩታል፡፡

የመምህርነትን ሙያዊ ተክህና ለመላበስ ንድፈ ሀሳባዊ እውቀትና ተግባራዊ ልምምድ ተጣምረው መሰጠት እንዳለባቸው Perrot (1982) ሲገልፁ የማስተማር ክሂልን ለማዳበር በቂ ጊዜ የተሰጠው ጥናትና የተግባር ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ሦስት ደረጃዎችን የተከተለ ድርጊት መፈፀም አስፈላጊ ነው፡፡ የመጀመሪያው አእምሯዊ የሆነው ተግባር ሲሆን፣ ሰልጣኞች ከክፍል ውስጥ ገለጻ የሚማሩትንና በግል ንባባቸው የሚያዳብሩትን እውቀት ያጠቃልላል፡፡ ሁለተኛው በማስተማር ልምምድ በገሃዱ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተግባር ክዋኔ በማድረግ የሚዳብር ክህሎት ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ሂደቱን ከሚገመግሙት ባለሙያዎች የሚገኘውና የሰልጣኞችን ደካማና ጠንካራ ጎን የሚያመለክተው ግብረ መልስ (Feedback) ነው፡፡ በማለት የመምህራንን ስልጠና ለማሳካት የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ያመለክታሉ፡፡

መምህራንን በማስልጠን ተግባር ላይ የተሰማሩ ተቋማት የሚያስለጥኗቸው መምህራን በሚሰማሩበት የማስተማር ተግባር ውጤታማ መሆን ይችሉ ዘንድ ሙያዊ ብቃታቸውና ግላዊ ስብእናቸው የተሟላ ሊሆን እንደሚገባው Azeb (1984:50) ሲያብራሩ እጩ መምህራን በሚሰለጥኑበት መምህራን ማስልጠኛ ተቋም ሊያገኙት የሚገባቸው እውቀትና ክህሎት ከማስተማር ሙያቸው ጋር የተሳሰረ መሆን እንዲችል በመማር ማስተማር ልምምድ ራሳቸውን መፈተሽ ይገባቸዋል፡፡ ይህን ተግባራዊ ሲያደርጉ ድክመቶቻቸውን ይረዱና እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ ካሰልጣኞቻቸው ጋር እየተወያዩ የመፍትሔ ሀሳብ ይጨብጣሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በስራ አለም ሲሰማሩ ለሚያጋጥሟቸው አንዳንድ ችግሮች እራሳቸውን ከወዲሁ እንዲያዘጋጁ ስለሚያስችላቸው የተግባር ልምምዱ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት ሊከናወን ይገባል፡፡ ብለው ይገልፁታል፡፡

በአጠቃላይ ማስተማር በአግባቡ የሰለጠኑ መምህራንን የሚፈልግ ተግባር በመሆኑ መምህራንን የማሰልጠኑ ሂደት በማስተማር ልምምድ የታገዘ ሊሆን ይገባዋል። መመህርነት የሚጠይቀው በትምህርት አይነቱ እውቀት ብቻ ጠንካራ የሆነ መምህር ሳይሆን ያለውን እውቀት በጥሩ ሁኔታ ማስተማር የሚችል ባለሙያን ነው። ይህ ሁኔታ ከነበረው የኢትዮጵያ መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር አንጻር ሲታይ በስልጠና መርሃ ግብሩ ውስጥ የማስተማር ልምምድ ቢካተትም በቂ ጊዜና ትኩረት የተሰጠው እንዳልነበር ቀደምት ጥናቶች ይጠቁማሉ። (ዓለም፣ 1988፣ ዓለማየሁ፣ 1998፣ ሂሩት 1998)። በመሆኑም ይንን ክፍተት ለመሙላት በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ስርአተ ትምህርት ውስጥ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ/Practicum/ እንዲካተት ተደርጓል።የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ምንነት Ministry of Education / MOE 2003:96) ሲገልጽ፤ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለእጩ መምህራን ሰፊ የተግባር ልምምድ ጊዜ የሚሰጥና ሰልጣኞች ሙያውን በእወናዊ አውድ እንዲለማመዱት እድል የሚከፍት፣ መርሀ ግብር ነው። በመሆኑም የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የመምህራንን ስልጠና ተጨባጭ በሆነ ተግባር እንዲታገዝ ያደርጋል በማለት ያብራራዋል።

እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ንድፈ ሀሳባዊ እውቀታቸውን በተግባር መፈተሻቸው ያለውን ጠቀሜታ አስመልክቶ ደግሞ (MOE፣ 2003፣44) ሲያብራራ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በመምህራን ስልጠና ሂደት ውስጥ በጣም ጠቃሚና ከሚፈለገው ግብ ሊያደርስ ይችላል ተብሎ የሚታመንበት ስልት ነው። በዚህ ስልት እጩ መምህራን ከእውናዊው የትምህርት ቤት ገፅታና የመማር ማስተማር ክንውን ጋር ይተዋወቁበታል። ከተማሪዎች ከመምህራንና ከማህብረሰቡ ጋር በመቀራረብ ለሙያቸው የሚያግዝ ባህሪ ያዳብሩበታል። በአጠቃላይ መርሃ ግብሩ እጩ መምህራን በንድፈ ሀሳብ የቀሰሙትን የመማር ማስተማር ስልት እንዴት ወደ ተግባር መለወጥ እንደሚችሉ በተግባር የሚማሩበት ነው። የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እጩ መምህራን ለስልጠና በመረጡዋቸው አብይና ንዑስ የትምህርት አይነቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው ሰፋ ያለ ልምምድ እንዲያደርጉ

ሁኔታዎችን የሚያመቻች በመሆኑ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ሊከናወን የሚገባው ተግባር ነው።

በየክልሉ የተቋቋሙት የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መሰረታዊ ተልእኮ ሙያዊ ብቃት የተላበሱ መምህራንን ማፍራት ነው። መምህራኑን ሙያዊ ክህሎት ለማስጨበጥ በስራ ላይ የሚውለው ዘዴ ደግሞ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ተከትሎ ለውጥ እየተደረገበት ነው። አሁን በስራ ላይ ያለውን የመምህራን ስልጠና ተተኳሪ ነጥብ በተመለከተ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በ10+3 ለሚሰለጠኑ እጩ መምህራን ባዘጋጀው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ ሲገልፅ

> *ሰልጣኞች በኮሌጅ የስልጠና ቆይታቸው ወቅት በየትምህርት ቤቶች ተመድበው እንዲሰሩ በማድረግ፣ የትምህርት ቤቶችን አጠቃላይ ሁኔታ፣ የማስተማር መማር ሂደት፣ የተማሪዎችን የግልና የወል ባህሪያት፣ ተማሪዎች በማስተማር መማር ሂደት ላይ የሚያሳዩትን ተሳትፎ፣ የነባር መምህራንን የማስተማር ሁኔታ፣ የሚጠቀሙባቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎችና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ምን እንደሚመስሉ፣ በሚመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው እየተመለከቱ፣ እያጠኑና እየሞከሩ በመምህርነት ሙያ ሰልጥነው እንዲወጡ ማድረግ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መሰረታዊ ተልእኮ ይሆናል( አብክመትቢ 2002፣3)።*

በማለት እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ቆይታቸው ትኩረት ሊሰጡባቸው የሚገቡ አበይት ተግባራትን ይዘረዝራል። ይኸው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የአፈጻጸም መመሪያ የመርሃ ግብሩን አጠቃላይ አላማ ሲያመለክትም

> *የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ /practicum/ መሰረታዊ ዓላማ ሰልጣኞች በስልጠና የሚያገኙትን እውቀት፣ ክህሎትና ዝንባሌ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተሞክሮ ጋር በማስተሳሰር፣ በተግባራዊ ልምምድ የዳበሩና ለሚዘጋጁበት ደረጃ የሚመጥን የሙያ ብቃት ይዘው እንዲመረቁ ማስቻል ነው (አብክመትቢ፣ 2002፡2)።*

በማለት ያስረዳል፡፡ ሰነዱ ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት የነደፈው ዝርዝር አላማ የሚያመለክተውም እጩ መምህራን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እውናዊ ልምምድ በማድረግ የወደፊት የስራ ቦታቸውን በትክክል እንዲገነዘቡ ለማድረግ፣ የሙያ ብቃታቸውንና የማስተማር ክህሎቸውን ለማጎልበት፣ የተማሪዎችን ባህሪ፣ የመማር አቅምና ፍላጎት ለማጥናት ከሚችሉበት አካባቢ ጋር በቀጥታ ለማገናኘት ነው በማለት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያስፈለገበትን አበይና ንዑስ ጭብጦች ከዘረዘረ በኋላ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ (ትቤተማል) ኮርስ በአራት ተከፍሎ የሚተገበር መሆኑን በሚከተለው ዝርዝር ያሳያል፡፡

- ትቤተማል I ( Prace 201)፣ ሁለተኛ ዓመት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት
- ትቤተማል II ( Prace 202)፣ሁለተኛ ዓመት ሁተለኛው ወሰነ ትምህርት
- ትቤተማል III (Prace 301)፣ ሦስተኛ ዓመት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት
- ትቤተማል IV(Prace 302)፣ሦስተኛ ዓመት የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት

ብሎ መድቧቸዋል፡፡ በዚህ ምድብ መሰረት በተለይ Prace 301 እና Prace 302 በአንድ ወሰነ ትምህርት (Semister) የሚሰጡ ሲሆኑ ተግባራቸውም 301 በአጋር መምህራን (Mentor) እየታገዙ ማስተማር ሲሆን Prace 302 ደግሞ ራስን ችሎ ማስተማር ነው ፡፡በመሆኑም የተያያዥነትና ተለጣጣቂነት ባህሪ ያላቸው ኮርሶች እንደሆኑ (አብክመትቢ. 2002፡5-9) ያብራራል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት አለም አቀፋዊ፣ ብሔራዊና ክልላዊ ሀሳቦች ተጠቃልለው ሲታዩ በመምህራን ስልጠና የሚሳተፉት እጩ መምህራን ጠንከራ ሙያዊ ክህሎት መጨበጥና ማዳበር የሚችሉት በማሰልጠኛ ኮሌጆቻቸው የተማሩትን የስነ- ትምህርት እውቀት ተመርኩዘው በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አማካኝነት በተግባር ሲሳተፉ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እጩ መምህራን ትምህርት ቤቶች እውናዊ እንቅስቃሴ ጋር በገሃድ የሚተዋወቁበትና በተግባር የሚሳተፉበት በመሆኑ ከመምህርነት ሁለንተናዊ ተግባር ጋር የሚያስተዋውቃቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባራዊ ሲደረግ አሰልጣኝ ኮሌጆችና እጩ መምህራን፣ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር በሚፈጥሩት ትብብርና

መስተጋብር ውጤታማ ስራ ይሰራል ተብሎ እንደሚታመን የ MOE ሰነድ TESO (2003) እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ያዘጋጀው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አፈጻጸም መመሪያ ያስረዳል። የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መሰረታዊ አላማም እጩ መምህራንን በትምህርት ቤቶች እውናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ በማስገባት በተግባር ማሰልጠን ነው። በመሆኑም በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ትግበራ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ለስልጠና የሚሰማሩትን እጩ መምራህን ተልእኳቸውን የመወጣት ብቃታቸው ምን ይመስላል? የሚለው ርእሰ ጉዳይ መጠናት እንዳለበት መነሻ ምክንያት ሆኗል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግሮች

ይህ ጥናት በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ትግበራ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እጩ መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንን በብቃት ለማሰልጠን የተሰጣቸውን ተልእኮ የማሳካት ብቃታቸውን ለመፈተሽ የተካሄደ ነው። የጥናቱ አነሳሽ ችግሮችም የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል) መምህርነት የሚሰለጥኑ እጩ መምህራንን በሦስተኛው አመት የመጀመሪያ መንፈቀ አመት ለስድስት ወር ተግባራዊ የማስተማር ልምምድ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይመድባል። ሰልጣኞች ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመድበው ሲወጡ የትምህርት ቤቶችን ውጫዊና ውስጣዊ እንቅስቃሴ በመቃኘት በእውናዊው የመማር ማስተማር ሂደት እንዲሳተፉ ትልእኮ ይሰጣቸዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የመንፈቀ አመቱን ስራቸውን በጊዜ በተመጠነ እቅድ አካትተውና ከፋፍለው ለእያንዳንዱ መምህር ሰጥተዋል። ይህ በመሆኑም በሰልጣኞች ተልእኮና በትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት አፈጻጸም መካከል የመርሃ ግብር ግጭት ሊፈጠር ይችል ይሆናል የሚል ስጋት በአጥኚው ላይ አሳድሯል። አጥኚው ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋር ባለው ማህበራዊ ግንኙነትም የሰልጣኞች ስምሪት በስራቸውና የእቅድ አፈጻጸማቸው ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድርባቸው ሲያጉረመርሙና ሲያማርሩ ሰምቷል። ሰልጣኞችም ቢሆኑ

ለስልጠና በሚሰማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ያሉት መደበኛ መምህራን የሚጠብቁትን ያህል እገዛ፣ ድጋፍና ልምድን የማካፈል ትብብር እንደማያደርጉላቸው አጥኝው በተከታታይ አመታት ለግምገማ በተመደበባቸው የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ያወያያቸው እጩ መምህራን ገልፀውለታል። ይህም ሀሳብ በመርሃ ግብሩ ትክክለኛ አፈጻጸም ላይ ያለውን ስጋት የበለጠ አጠናክሮታል። ከዚህ በመነሳት ቀጥሎ የተመለከቱት የምርምር ጥያቄዎች በአጥኝው አእምሮ ውስጥ ተፈጥረዋል።

1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መደበኛ መምህራን የእጩ መምህራኑን ተልዕኮ ከመደበኛ መርሃ ግብራቸው ጋር አጣጥመው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምዱን በትክክል ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ?
2. እጩ መምህራን የማስተማር ተግባር በሰአት ተመጥኖ የሚከናወን መሆኑን ተረድተው የሚያደርጉት የማስተማር ልምምድ የመደበኛ መምህራኑን ተግባር የማያደናቅፍና የሚያጠናክር አድርገው መፈፀም ይችላሉ?
3. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ብቁ መምህራንን ለማፍራት የሚያደረገውን ጥረት ተገንዝቦ የእጩ መምህራኑን ተልእኮ ከመደበኛ መምህራን መርሃ ግብር ጋር የሚያጣጥምበት ስልት ዘርግቷል?
4. የመማር ማስተማሩ ተግባር በሰአት የተመጠነ ድርጊት ያካተተ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለእጩ መምህራን ተልእኮ በቂ ትኩረት ተሰጥቷል? ትኩረት ቢነፈገው በስልጠናው ላይ የሚከሰተው ችግር ምን ሊሆን ይችላል?
5. የእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገቢ ትኩረት ሲሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መደበኛ መርሃ ግብር የሚጎዳ ቢሆን ግጭቱ በምን መልክ ሊታረቅ ይችላል? የሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ጥናት ምላሽ ያገኛሉ።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ እጩ መምህራንና ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመደቡባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተሰጣቸውን ሀላፊነትና ተልእኮ የመወጣት ብቃት ለይቶ ማሳየት ነው። ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳትም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል።

- በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሂደት ዋነኛ ተሳታፊ

የሆኑት እጩ መምህራን በተመደቡባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሊጫወቱት የሚገባቸውን ሚና ለይቶ ማሳየት፣

- ተለይተው የታወቁትን ሚናዎች በተገቢው መንገድ መወጣት መቻል አለመቻላቸውን መመርመር፣
- በማስተማር ልምምድ ወቅት እጩ መምህራን ከመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋር ተባብረው በመስራት ሊያከናውኑ የሚችሉትን ተግባር መተንተን፣
- እጩ መምህራን ከማሰልጠኛ ኮሌጁ ለልምምድ ሲወጡ የሚሰጣቸው ተልእኮ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት ጋር ያለውን መጣጣም መመርመርና መገምገም፣

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች የሚሆኑት ለመምህርነት ሙያ በመሰልጠን ላይ ያሉት እጩ መምህራን፣ የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሃ ግብር የሚያስፈጽሙት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ የሚገኙና ለእጩ መምህራን በአጋራነት የተመደቡ መምህራን፣ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣የትምህርትን ስራ በመምራት ላይ ያለው የትምህርት ቢሮና በዚህ መስክ ጥናት ሊያደርጉ የሚፈልጉ ሌሎች አጥኝዎች ናቸው። ጥናቱ ለተጠቃሚዎች የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል

- በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመደቡ እጩ መምህራን በትምህርትቤት ቆይታቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን ተግባር ለይቶ ያመለክታል። ይህ ሲሆን ደግሞ እጩ መምህራንም ሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች አንዱ የሌላውን መርሃ ግብር ሳያደናቅፍ በመረዳዳትና በመተጋገዝ ዓላማቸውን የሚያሳኩበትን ዘዴ ይጠቁማል፣
- እጩ መምህራን ከአጋር መምህራን/ Mentor/ እና ከመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ጋር ሊፈጥሩት የሚገባውን ትስስርና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ሊኖረው የሚችለውን ገንቢ ሚና ለይቶ ይጠቁማል በመሆኑም አጋር

መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የተሰጣቸውን ተልእኮ ለይቶ ከማሳየቱም ባሻገር በመማር ማስተማሩ ሂደት ሰልጣኞች የሚኖራቸውን ሚና ያመለክታል፡፡

- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚወጡት እጩ መምህራን ከማሰልጠኛ ኮሌጁ ይዘውት የሚነሱት ተልእኮ የተቀባዩን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ዓላማ ከማሳካት አንጻር ምን ማከናወን እንዳለበትና በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት ጠቋሚ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡ ይህ በመሆኑም በኮሌጁና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚኖረው ሙያዊ መደጋገፍ የተጠናከረ ይሆናል፡፡
- ከዚህ ርእስ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነትና ትስስር ላላቸውና የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበርን ለማጠናከርና ለማሻሻል ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ ሀሳብ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ብሔራዊ ክልል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን መስተዳድር፣ በደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ አስተዳደር ነው፡፡ በዚህ ከተማ ወረዳ አስተዳደር ዘጠኝ የመንግስትና ሁለት የግል በድምሩ አስራ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል (ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ አስራአንድ ትምህርትቤቶች መካከል የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች አራት የመንግስት ትምህርትቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የጥናቱ መሰረታዊ ዓላማ የትምህርት ቤቶችንና የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር፣ ለጉዳዩ የሚሰጡትን ትኩረትና ሀላፊነትን የመወጣት ብቃት መለየት በመሆኑ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚከናወነው ተግባር ተመሳሳይነት ያለውና በአንድ መርሃ ግብር የሚመራ ስለሆነ ድግግሞሽን በማስወገድ ጊዜን ጎልበትንና ገንዘብን ለመቆጠብ ሲባል ነው፡፡

የግል ትምህርት ቤቶች በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡ ምክንያቱም የግል ትምህርት ቤቶች በመሰረታዊ አቋማቸው የአትራፊነት ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ በመሆኑ ይኸው ባህሪያቸው የጥናቱን ትክክለኛ መረጃዎች ይሸፍን ይሆናል ከሚል ስጋት ነው፡፡

ጥናቱ በ 2003 ዓ.ም ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለአንድ መንፈቀ ዓመት ተግባራዊ ልምምድ በወጡ እጩ መምህራንና ለስልጠና በተሰማሩባቸው አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተካሄደ ነው። ዋነኛ ትኩረቱም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ከማስተግበር አኳያ እየፈፀሙት ያለውን ተግባር ትክክለኛነት መፈተሽ፣ እጩ መምህራን ለስልጠና የተቀበላቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መሰረታዊ ዓላማ በማስፈፀም ረገድ ሊጫወቱት የሚችሉትን ሚና መመርመር ነው።

በጥናቱ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መርሃ ግብሩን የማስፈፀም ዓላማና ተልእኮ፣ የእጩ መምህራን መሰረታዊ ተልእኮና የተልእኮ አፈጻጸም፣ የአጋር መምህራን/mentors/ መሰረታዊ ተግባር፣ አሰልጣኝ ኮሌጁ ለሰልጣኞች የሰጠው ተልእኮና ተግባራዊነቱ፣ ሰልጣኞች ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያበረክቱት ሙያዊ ተግባር፣ ሰልጣኞች ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በተለይም ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነትና የሚያሳዩዋቸው የባህሪ ለውጦች፣ ተካትተዋል። በአንጻሩ ጥናቱ የመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አደረጃጀትና ለመማር ማስተማር ያላቸውን ምቹነት፣ የአጋር መምህራንን የትምህርት ዝግጅትና የማስተማር ብቃት፣ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁን አጠቃላይ ስርአተ ትምህርትና የሚጠቀምባቸው የማሰልጠኛ መጻህፍት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምዱን የተሳካ ለማድረግ ያላቸው ብቃት፣ የሚሉትን አልተመለከተም።

## 1.6 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

ጥናቱ በሚከናወንበት ወቅት የአጥኚውን አቅም የተፈታተኑ ችግሮች ገጥመውታል። ከነዚህም መካከል

1. የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ አመት የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ተማሪዎች ምዝገባ እስከ ጥቅምት ወር መጨረሻ ድረስ ዘግይቷል። ይህም ሁኔታ አጥኚው ሀሳቡን አሰባስቦ ወደ ጥናቱ እንዳይገባ እንቅፋት ሆኖት ቆይቷል። በመሆኑም የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ ከፍተኛ የጊዜ እጥረት

ገጥሞታል። ሆኖም ችግሩን ለመወጣት ያለምንም እረፍት በመስራት ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ተሞክሯል።

2. የተጠቀሰው የጊዜ እጥረት እንዳለ ሆኖ ለጥናቱ የተጠየቀው በጀት በወቅቱና በተጠየቀው መጠን አለመድረሱ ደግሞ ሌላ ጋሬጣ ሆኖ ነበር። በጀቱ በተጠየቀው መጠንና ለስራው በሚያስፈልግበት ጊዜ አለመሰጠቱ በጥናቱ ሂደት ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል። አጥኚው ይህን ችግር ለማቃለል በግል ወጭው እየሸፈነ በመስራት ችግሩን ለመቋቋም ምክሯል።

በአጠቃላይ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ከጊዜ፣ ከአቅምና ከሁኔታ ጋር በማጣጣም ጥናቱን በታቀደለት የጊዜ ገደብ ለመፈፀም አጥኚው ጥረት አድርጓል።

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.1 የመምህራን ስልጠና ታሪካዊ ዳራ

መምህራንን ማሰልጠን ያስፈለገው ትምህርትን በቀለጠፈ ሁኔታ ለማከናወን ነው። ትምህርትና የሰው ልጅ ህይወታዊ እንቅስቃሴ ደግሞ የራሳቸው የሆነ ትስስር ያላቸው ናቸው። ይህን ሁኔታ Castle (1993፡1) ሲያብራሩ፣ ትምህርት ከሰው ልጅ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴና የሕይወት ተሞክሮ ጋር የጠበቀ ትስስር ያለው ተግባር ሲሆን በሰው ልጅ የህይወት ሂደት ውስጥ ከልደት እስከ ሞት ድረስ የሚታይ ክስተት ነው። እያንዳዱ ሰው ህጻንም ሆነ ጎልማሳ፣ የተማረም ሆነ ያልተማረ፣ ከዘወትር እንቅስቃሴው አዳዲስ ነገሮችን ይማራል። የመማር ማስተማር ሂደቱም ከተለመደው የህይወት እንቅስቃሴ የሚመነጭ እንጂ በፍላጎትና በአላማ ላይ የተመሰረት አይደለም። በዚህም የተነሳ ማንኛውም ሰው በህይወታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በሚያደርግበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ኢ- ንቁ ህይወታዊ ጉዞ ውስጥ ባለበት ሁኔታም ቢሆን ከሌሎች ልምድና ተግባር ይማራል። የራሱንም ተሞክሮ ለሌሎች ያስተምራል በማለት ገልፀውታል።

የሰው ልጅ ህይወታዊ እንቅስቃሴ ሁሉ ትምህርት ነው ሲባል አንዱ ከሌላው እየተማረና ተሞክሮውን እያሻሻለ ወደ እድገት የሚያመራበት ጎዳና ትምህርት መሆኑን ያመለክታል። በመሆኑም ተፈጥሮአዊዉን የሰው ልጅ የመማር ፍላጎት በመደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት ስርዓት ቃኝቶ መተግበሩ ለተፋጠነ እድገት አስፈላጊ ይሆናል። ይህ ከሆነ ደግሞ ለመማር ማስተማር ተግባር ቀጥተኛና አብይ ድርሻ ያላቸው መምህራን አስፈላጊነት ጎልቶ ይወጣል። ትምህርት ከሰው ልጅ ህይወት ጋር ካለው ቁርኝት አንጻር ሲታይ ይህን ተግባር ለሚያከናውኑት መምህራን ስልጠናና ዝግጅት ትኩረት የተሰጠው በቅርብ ጊዜ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ እንደ Myra and David (2000, 7-19) አገላለፅ በአሜሪካ የመጀመሪያው መምህራንን በመደበኛ የማስተማር ስልት እያሰለጠነ የሚያወጣ ተቋም የተመሰረተው በ 1823 ነበር። በፈጣን ስልጣኔና እድገት ላይ በነበረችው አሜሪካ የመምህራንን ስልጠና በመተግበር የመጀመሪያው የሆነው ይኸው ተቋም እየሰጠው ያለው ግልጋሎት አስፈላጊ ሆኖ

በመገኘቱም ከ 16 አመት ቆይታ በኋላ በ 1839 ሆራክማን በማሳቹ ግዛት በመንግስት ድጋፍ እየተሰጠው በወቅቱ ለመምህራን ስልጠና አስፈላጊ የሆኑት ቁሳቁሦች የተሟሉለት የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም መሰረተ፡፡ በዚህ ተቋም የተለያዩ የእውቀት ዘርፎችን ያካተቱ የትምህርት አይነቶች ከስነ- ትምህርት /pedagogics/ ጋር እየተቀናጁ የሁለት አመት ስልጠና የሚሰጥበት ነበር፡፡ ይህ ተቋም እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የመምህራን ስልጠናን በማሳካት እረገድ የጀርባ አጥንት ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ ይቀበላቸው የነበሩት ሰልጣኞችም የተወሰኑት በቀጥታ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚመጡ መምህራን ሲሆኑ፣ የተወሰኑት ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ከጊዜ ቆይታ በኋላ በመላው አሜሪካ ጊዜው በሚፈልገው ደረጃና በጥሩ ሁኔታ የሰለጠኑ መምህራን ተፈላጊነት እያደገ በመምጣቱ በ 1900ዎቹ በርካታ የግል ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ለመምህራን ስልጠና የተለየ ትኩረት መስጠት ጀመሩ፡፡ በመሆኑም የተቋማቱ ፕሮግራም ወደ ሶስትና አራት አመት እያደገ መጥቶ ወደ መንግስታዊ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅነት ተለወጠ፡፡ በ 1950ዎቹ ብዙዎቹ የመምህራን ኮሌጆች የበለጠ መስፋፋትና ጥንካሬ ታየባቸው፡፡ ሁኔታው ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለና እያደገ መጥቶ በ1980ዎቹ በሁሉም የአሜሪካ ግዛቶች የትምህርት ሂደትን እንደገና የማደራጀት ተግባር ሲጀመር በበርካታ ዘርፎች ላይ ሰፊ የፕሮግራም ማሻሻያ ስለተደረገ የመምህራን ስልጠና አሁን ወዳለበት እርከን ሊሸጋገር እንደቻለ መረዳት ይቻላል፡፡፡

የዘመናዊ ትምህርት አጀማመርና ለዚሁ ብቁ የሆኑ መምህራንን የማፍራት ተግባር ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ደግሞ እንደ አለም አቀፋዊው ሁሉ እድሜው ሩቅ አይደለም፡፡ እንደ Bridges and Marew (2000:7) አገላለፅ ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ የተጀመረው በ 1908 ከዳግማዊ ሚኒልክ ትምህርት ቤት መቋቋም ጋር ነበር፡፡ በወቅቱ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው ተግባርም በተቻለ አቅም የመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት ነበር፡፡ በመሆኑም እስከ 1943 ድረስ 22 የሚደርሱ የመንግስትና የሚሽነሪ የመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተቋቁመዋል፡፡ በዚሁ አመት የመጀመሪያው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ተከፍቷል፡፡ ይኸውም የቀደማዊ ሐይለስላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በ 1944/45 የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን የሚያሰለጥን የመምህራን ማሰልጠኛ ተመሰረተ፡፡ ይህም

እስከ 1950/51 የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ መቋቋም ድረስ ብቸኛው ሆኖ እንደቆየ መረጃው ያሳያል።

የኢትዮጵያ የመምህራን ስልጠና በአጭር ጊዜ ታሪኩ በየጊዜው ለሚለዋወጠው የፖለቲካ ስርአት እየተንበረከከ ለውጥ ተደርጎበታል። ይህንን ሁኔታ Tirusew (2006) ሲያብራሩ የሀገራችን የትምህርት ስርአት ተሞክሮ እንደሚያመለክተው የመምህራን ትምህርት ከመንግስት ስርአት ጋር ቁርኝት አለው። በመሆኑም ስርአቱና አስተዳደሩ ሲቀየር የአሰለጣጠን ዘዴውም ይቀየራል፤ በማለት ይገልፁታል።

## 2.2 የመምህራን ስልጠና አስፈላጊነት

የመምህራን ስልጠና ፕሮግራምን አስፈለጊነት Natalie, (1998፣1-5) et.al. ሲገልፁ በእውቀትና ክህሎት ሽግግር ውስጥ ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው ግንዛቤን ማዳበርና የጨብጡትን ግንዛቤ መልሶ የማንፀባረቅ ችሎታ ነው። እውቀትን፣ ክህሎትን፣ ባህላዊ ልምዶችንና ማህበራዊ እሴቶችን በቀለጠፈ መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል ሁኔታዎችን በአግባቡ መመርመርና መፈተሽ የሚያስችል አቅም መፍጠር ያስፈልጋል። ይህ አቅም ሊፈጠር የሚችለው ደግሞ በስልጠና ነው ። ስለሆነም መምህራንን በተገቢው ሁኔታ ማስልጠን ተልእኳቸውን ለመወጣት የሚያስችል አቅም የመፍጠር ተግባር ነው። መምህራን በሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ብቻ መብቃት ሳይሆን አካባቢያቸውን በአግባቡ መፈተሽና መረዳት የሚችሉና ከአካባቢያቸው ያካበቱትን ግንዛቤ በትክክል ለማንፀባረቅ የበቁ፣ የተግባር ሰዎች መሆን ይኖርባቸዋል ። ለዚህ ሁኔታ መመቻቸት ስራው መጀመር ያለበት ከማሰልጠኛ ተቋማት ነው። እጩ መምህራን በስልጠና ቆይታቸው የተገነዘቧቸውን የመማር ማስተማር ችግሮች እያስታወሱ ባፈታታቸው ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ አጠቃላይ አመለካከታቸው ለወቅታዊ እንቅስቃሴዎች ተገቢ ይሆንና ለማህበረሰቡ የሚያስፈልገውን ክህሎት ሊያበረክቱ ይችላሉ። በመሆኑም አካባቢን መሰረት ያደረገና ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የተገናዘበ የመመህራን ስልጠና አስፈላጊ ይሆናል፤ በማለት መምህራንን በተገቢው ሁኔታ ማስልጠን ከትምህርት የሚጠበቀውን ውጤት ጠንካራና አዋጭነት ያለው ተግባር መሆኑን ገልጸዋል። በመሆኑም ከላይ በተሰጠው የምሁራን ገለጻ አንጻር ሲታይ ከመምህርነት የሚጠበቅ ተግባርን በጥራትና በብቃት ለማከናወን ስልጠና አስፈላጊ ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

Befekadu (1998:378) ይህንን ሁኔታ ሲያብራሩ ደግሞ፣ ከጊዜ ሂደት ጋር እየዘመነ የመጣውን የመደበኛ ትምህርት ሂደት በተገቢው ሁኔታ ለመተግበር፣ የመምህራን ስልጠና በአግባቡ መከናወን አለበት። ይህ መምህራንን በብቃት የማሰልጠን ተግባር በተለይ በታደጊ ሀገሮች ወቅታዊ የመነጋገሪያ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በበርካታ የአፍሪካ አገሮች የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን የበቁ አድርገው ለማሰልጠን ያላቸውን ፍላጎት በተለያዩ የፖሊሲ ሰነዶቻቸው ላይ ጠቅሰውታል። ቀጥተኛ ተጠሪነቱንም የማስፈፀም አቅም አላቸው ብለው ለሚያምኑባቸው ግዙፍ ኢንስቲትዮቶቻቸው ሰጥተዋል። ለምሳሌ ያህል በኬንያ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ስልጠና መርሃ ግብርን የመከታተል ሃላፊነት የተሰጠው ለኬንያ ዩኒቨርስቲ ነው። በቦትስዋና ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን የሚያሰለጥኑ መምህራንና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ መምህራንን የማሰልጠን ሃላፊነት የተሰጠው ለቦትስዋና ዩንቨርስቲ ነው። በቦትስዋናና ሌሴቶ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን የሚያሰለጥኑ መምህራን የሚመለመሉትም ከመጀመሪያ ደረጃ መምህራን መካከል ነው። ለምልመላ የሚጠቀሙበት መስፈርትም የትምህርት ደረጃና የማስተማር ልምድን መሰረት ያደረገ ነው። ይህ ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን ስልጠና አስፈላጊነትና ሊሰጠው የሚገባውን ትኩረት የሚያመለክት ነው። በሀገራችንም የመጀመሪያ ደረጃ መምህራንን የሚያሰለጥኑ መምህራንን የማሰልጠን ሀላፊነት የተሰጠው ተቋም በባህርዳር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መመሰረት የተጀመረና በቀላሉ የማይገመት ልምድ የተካበተበት ሂደት ነው። የባህርዳር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተመሰረተበት ዋነኛ ዓላማ በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት (TTI) የሚያስተምሩ መምህራንን ለማፍራት ነበር፤ በማለት ይገልጹታል።

እንደ ምሁሩ ገለጻ መምህርነት በቂ ትኩረት ያልተሰየው ስልጠና ሊሰጥበት የሚገባ ተግባር በመሆኑ በሚመለክተውና ሀላፊነት በተሰጠው ተቋም እየተመራ ስልጠናው መከናወን እንዳለበት መረዳት ይቻላል።

### 2.3 በመምህራን ስልጠና ውስጥ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አስፈላጊነት

መምህርነት ንድፈ ሀሳባዊ እውቀት ከተግባራዊ ክንዋኔ ጋር ተዋህዶና ተቀናጅቶ የሚተገበርበት መስክ ነው፡፡ ስለሆነም ስልጠናው ንድፈ ሀሳባዊ እውቀትን ከተግባራዊ ልምምድ ጋር ያቀናጀ መሆን እንዳለበት Sirvastava and Bose፣ (1978:112) ሲያስረዱ፣ በመምህራን ሰልጠና መርሃ ግብር ውስጥ የማስተማር ልምምድ የመከተቱ አስፈላጊነት የግድና መታለፍ የማይገባው ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም እጩ መምህራን በስልጠናው ሂደት የቀሰሙትን ንድፈ ሀሳባዊ እውቀት በተግባር እንዲተረጉሙት በማድረግ ወደፊት በሙያው ለመሰማራት የሚያዳርጉትን ዝግጅት ስለሚያጠናክርላቸው ነው፤ በማለት ይገልፁታል፡፡

Shiundu and Omulando፣ (1992,229) ከላይ የቀረበውን የምሁራን ገለጻ ሲያጠናክሩት ደግሞ የማስተማር ልምምድ የመምህራን ስልጠና አንዱ ገፅታ መሆኑንና መሰረታዊ ትኩረቱም በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚደረግ ልምምድ ላይ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰልጣኞች በክፍል ውስጥ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የተማሩትን የመማር ማስተማር እውቀትና ክህሎት በእውናዊ አውድ በትምህርት ቤት ውስጥ ተገኝተው እየሰሩ መለማመድ፣ እንደሚጠበቅባቸው እኚሁ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

Armstrong. O(1991:90) የመምህራን ስልጠና በተግባራዊ ልምምድ መደገፍ እንዳለበት ሲገልፁ የመምህርነት ተግባርን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ንድፈ ሀሳባዊ እውቀት በተግባራዊ ልምምድ እየታገዘ ስልጠናው መከናወን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ስልጠና ግለሰቦችን የተቋሙን መሰረታዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ጠቃሚ እውቀትና ክህሎት የሚያለብስ ስርአታዊ ዘዴ ስለሆነ በተግባራዊ ልምምድ የመታገዙ ጉዳይ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በሌላ በኩል የሰልጠና ጉዳይ ሲነሳ የአሰልጣኙ ሁለንተናዊ አቅምና ስልጠናውን የመተግበር ብቃት፣ የሰልጣኞች ፍላጎትና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ለስልጠናው አሰጣጥ ያላቸው ድጋፍ የመሳሰሉት ተያያዥና አይቀሬ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ይህን ጉዳይ Smith፣(1970:71) ሲያስረዱ ማሰልጠን ማለት ግለሰብ ወይም ግለሰቦች አንድን

እውቀትና ችሎታ በተግባር ለመፈፀም እንዲችል (እንዲችሉ) መምራት ማለት ነው። በመሆኑም የሰልጣኞችን የመሰልጠን ፍላጎትና አቅም፣ የአሰልጣኙን ስልጠና የመስጠት ብቃትና የአካባቢውን ለስልጠና ምቹነት፣ የመሳሰሉትን በትክረት ማየት እንደሚገባ ይገልጻሉ።

Http://www. Jamensah. Compssee chs. Praticum 20 in Teacher % 20 Educ %20 do፣ ከተባለው ደህረ ገጽ የተገኘው መረጃ እንደሚያብራራው ደግሞ የመምህራን ስልጠና፣ የማህብረሰቡን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለማጠናከርና ለማሳደግ፣ በፍጥነት እየተለወጠ ስለመጣው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታ ግንዛቤ ለማግኘትና የነፍስ ወከፍ ገቢን ለማሳደግ እራሱን የቻለ ጠቃሚ ሚና ይጫወታል። እንደዚህ ድህረገጽ አገላለፅ በዚህ አይነቱ ትልቅ ሙያ አስተማማኝና በተግባር የጎለበተ ክህሎት ለማስጨበጥ ትክክለኛው ዘዴ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተግባር መተርጎም ነው። ስለዚህም የመምህራን ስልጠናን ስኬታማ በማድረግ ሂደት ውስጥ የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር፣ ልምምድ የሚጫወተው ሚና በንፅፅር ሲታይ ልብ በህይወት ቀጣይነት ውስጥ ያለውን ድርሻ ያህል ሲሆን በሌሎች ሙያዎች ደግሞ እንደ ስርአተ እስትንፋስ እነደሚቆጠር ድህረ ገፁ ያስረዳል።

ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ በመምህራን ስልጠና ሂደት ንድፈ ሀሳብ ከተግባር ጋር ተቀናጅቶ መስጠት እንዳለበት የተለያዩ ምሁራን ይመክራሉ። ንድፈ ሀሳብ ከተግባር ተዋህዶ በማይሰጥበት የመምህራን ስልጠና ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ አለማየሁ፣ (1997፡269) በምሳሌ ሲያብራሩ ‹‹አንድን ተማሪ ስለ ብስክሌት አነዳድ ሌክቸር ከሰጡ በኂላ ያለምንም ተግባራዊ ልምምድ ግለሰቡ ብስክሌት በአግባቡ እንዲነዳ የመጠበቅ ያህል ነው።›› በማለት ቀለል ባለ አገላለፅ በስልጠና ሂደት ውስጥ የተግባራዊ ልምምድን አስፈላጊነት አጉልተው አሳይተውታል።

## 2.4 ከትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚጠብቁ ግቦች

የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲከወን የሚጠበቁ ታላላቅ ግቦች አሉት። ይህንን በተመለከተ Http://www. Jamensah. Com/Speeches/

practicum%20 in Teacher %20 Educ %20 do Janamuahmensah)፣ ሲያስረዳ በመምህራን ስልጠና ሂደት ውስጥ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንደየ ሀገራቱና ተቋማቱ አላማና ፍላጎት የተለያየ ነው። አንዳንዶች በስድስት ሳምንታት ወስነው ይተገብሩታል። አንዳንዶቹ ደግሞ ከአስራ ስድስት እስከ ሰላሳ ሁለት ሳምንታት ጊዜ ይመድቡለታል። በነዚህ የተለያዩ የጊዜ ልኬቶች እጩ መምህራንን ከእውናዊው የተማሪዎችና የትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴ ጋር በማገናኘት በመምህርነት ተግባር ውስጥ ያሉ ዝርዝር ሁኔታዎችን በተግባር እንዲለማመድ ይደረጋል። ችግር ፈች ክህሎትንና ቡድናዊ አቅምን ማዳበር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸትም ሌላው ተግባር ነው። በዚህ ሂደት እጩ መምህራን ከንድፈ ሀሳባዊ ትምህርት የቀሰሙትን እውቀት በተግባር ለመፈተሽ እድል ስለሚፈጠርላቸው የማስተማር አቅማቸው ይጎለብታል ተብሎ ይታመናል። በማለት ይዘረዝራል።

በመምህራን ስልጠና ሂደት የትምህረት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ፣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ ብቁ መምህራንን ከማፍራት መሰረታዊ ጭብጥ በመነሳት እንደየ ክልሎች የተለያየ አፈጻጸም ስልት ተዘርግቶለታል። የመርሃ ግብሩን መሰረታዊ ግብ በተመለከተ ( አብክመ ትቢ 2002፡ 7-10) ሲያብራራ፣ እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ስለ ትምህርት ቤት አጠቃላይ ተጨባጭ ሁኔታ አደረጃጀትና የተግባር አፈጻጸም ምልከታ ማድረግ፣ የአጋር መምህሮቻቸው እገዛና ክትትል ያልተለየው ራስን ችሎ የማስተማር ልምምድ ማድረግና ስለተመለከቱትና ስለተሳተፉበት የመማር ማስተማር ሂደት ጥናታዊ ጽሁፍ ማዘጋጀት የሚችሉበትን አቅም ማዳበር ይጠበቅባቸዋል በማለት ገልጾታል፡፡፡

## 2.5. የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የአፈጻጸም መርሆዎች

በሀገራችን ካሉት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንዱ የሆነውና በመምህራን ስልጠና ተግባር የዳበረ ልምድ ያለው የባህርዳር ዩንቨርስቲ የርቀት ትምህርት ክፍል ባዘጋጀው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሞጁዩል BDU (2008፡13-15) MOE 2003 ን በመጥቀስ በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ትግበራ ሂደት

ሃላፊነት የተጣለባቸው አካላት እጩ መምህራን፣ ልምምድ የሚካሄድባቸው ትምህርት ቤቶች፣ አሰልጣኝ የኮሌጅ መምህራንና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ አጋር መምህራን እንደሆኑ ይዘረዝራል። የነዚህ አካላት የየራሳቸው ሃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው በመጥቀስ ሲያብራራ ደግሞ እጩ መምህራን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገኝተው ከትምህርት ቤቶች ማህበረሰብ ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ መስራትን፣ ከሌሎች የመማር ልምድን፣ አስተዳደራዊ ህግጋትንና የማስተማር ስልትን፣በተግባር እንዲለማመዱ እንደሚጠበቅባቸው፤ አሰልጣኝ የኮሌጅ መምህራን እጩ መምህራንን ለተግባራዊ የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከማዘጋጀት ጀምሮ የእጩ መምህራኑን አጠቃላይ የልምምድ ሂደት በቅርብ የመከታተልና ከአፈጻጸም አላማው ጋር አገናዝቦ በመገምገም ግብረ መልስ የመስጠት ሃለፊነት እንዳለባቸው ያብራራል። የመጀሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በበኩላቸው ለስልጠና የሚመደቡላቸውን እጩ መምህራን በሁሉም የክፍል ደረጃዎችና የትምህርት አይነቶች ተግባራዊ ተሞክሮ እንዲያገኙ የሚያስችል ምቹ መርሀ ግብር የመዘርጋትና እያንዳንዱን ስልጣኝ በስልጠና ሂደቱ እገዛና ክትትል የሚያደርግለት አጋር መምህር የተመደበለት መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰሩ አጋር መምህራንም ለተመደቡላቸው እጩ መምህራን ጥሩ ሞዴልና ቅን አማካሪ በመሆን ከክፍል ውስጥና በክፍል ውጭ የሚከናወኑ የትምህርት ተግባራትን በአግባቡ እንዲያከናወኑ የማገዝ ሃላፊነት የተሰጣቸው መሆኑን በዝርዝር አብራርቷል።

ሰልጣኞችን በአውድ ውስጥ በማሰልጠን ንድፈ ሀሳባዊ እውቀትን ከተግበራዊ አፈጻጸም ጋር ያጣመሩ መምህራንን ለማፍራት የሚደረገው ጥረት በአሰልጣኝ ተቋማቱ መርሀ ግብር ላይ ብቻ የሰፈረ ሳይሆን በመንግስታዊ አዋጆችም የተደገፈ ነው። ለምሳሌ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተጠቃለሉ ህጎች (አብክመ 1997፡683) ‹‹በስራ ላይ ልምምድ የሚሳተፉ ድርጅቶችን ተግባርና ሀላፊነት ለመወሰን የወጣ አዋጅ›› በሚል ርእስ ባወጣው አዋጅ የማሰልጠኛ ተቋማትን፣ ተግባራዊ ስልጠና የሚደረግባቸውን ድርጅቶችና የሰልጣኞችን ሀላፊነትና ግዴታ ዘርዝሯል። በዚህም መሰረት የማሰልጠኛ ተቋማት ለተግባራዊ ስልጠናው አሰራር መመሪያና ዝርዝር መርሀ ግብር በማውጣትና የስራ ላይ ልምምዱን የሚከታተልና የሚቆጣጠር ባለሙያ በመመደብ በየጊዜው

መከታተልና መገምገም እንዳለበት ያመለክታል። ሰልጣኞችን እንዲያለማምዱ በሃላፊነት የሚቀበሉ ድርጅቶች ደግሞ ተለማማጆችን ከድርጅቱ የአሰራር ስርአትና ደንብ ጋር ከማስተዋወቅ ጅምሮ የመለማመጃ ቦታና ሁኔታ በማመቻቸት የልምምድ ሂደቱን እየገመገሙ ለአሰልጣኝ ተቋሙ ግብረ መልስ የመስጠት ሀላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳል። ተለማማጆች በበኩላቸው የሰልጠናውን ግብ ለማሳካት ለስራ ላይ ልምምድ የተመደቡበትን ድርጅት የአሰራርና አመራር ሂደት ከመገንዘብ ጅምሮ ልምምዱን በትጋት በማከናወን እራስን ብቁ ባለሙያ ለማድረግ መጣር እንዳለባቸው ያብራራል።

## 2.6 የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን አስመልክቶ የተሰሩ ሀገር በቀል ጥናቶች

የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ ከዘርፉ ጋር ተዛማጅ ሙያና ዝንባሌ ያላቸው ምሁራን ጥናቶችን አካሂደዋል። የተካሄዱትን ጥናቶች በመዳሰስ ለጥናቱ አላማ መሳካት የሚያስችሉ መነሻ ሀሳቦችን ለማሳየት ተሞክሯል።

Alemayehu (1998)."Teachers Education Trends in Some countries: Implication for the Ethiopian Context" በሚል ርእስ ጥናት አካሄደዋል። በጥናታቸው ውጤትም የሀገራችን የመምህራን ስልጠና መርሀ ግብር ከሌሎች አገራት የመምህራን አሰለጣጠን መርሀ ግብር ጋር ሲነጻጸር ለማስተማር ልምምድ የተመደበለት ጊዜ ጠባብ እንደሆነ አሳይተዋል።

ዓለም (1988)። በበኩላቸው ከመምህራን ስልጠና ጋር አያይዘው ‹‹በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ትንተና።›› በሚል ርእስ ጥናት አካሄደዋል። ለጥናታቸው መሳካትም በግብአትነት የአስተማሪዎችን ማስታወሻ፣ የቃለ መጠይቅ የካሴት ቅጅ፣ የጽሁፍ መጠይቅና የመገምገሚያ ቅጽን ተጠቅመዋል። በተደረገው የመረጃ ትንተናም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጀ የሚከናወነው የማስተማር ልምምድ በኮሌጁ የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን፣ የማስተማር ልምምዱ በበቂ ዝግጅት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን፣ የማስተማር ልምዱ አላማና ተግባር በሱፐርቫይዘሮችና በእጩ መምህራን በቂ ግንዛቤ አለማግኘቱን ካሳዩ በኋላ እነዚህ

ችግሮች የመምህራን ስልጠና መርሀ ግብሩ በተቃና ሁኔታ እንዳይካሄድ እንቅፋት ሆነዋል ይላሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስነ- ትምህርት ፋኩልቲ የመምህራን ስለጠና መርሀ ግብር የተደረገው የ Gebremedhin (2001) ጥናትም በመምህርን ስልጠና ዙሪያ ከተካሄዱ ጥናቶች አንዱ ነው። የጥናቱ ርእስ " Aspects of Teacher Development for English Language Teaching" የሚል ነው በጥናቱም እጩ መምህራን ለአንድ ወር የሚቆየውን የማስተማር ልምምድ ከተገበሩ በኋላም በአዲስ አበባ የኒቨርስቲ የሚካሄደው የመምህራን ሰልጠና ችግር ያልተለየው እንደሆነ አመልክተዋል።

ተሰጠ (1997) ‹‹የፕራክቱክም የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፊኬት (10+1) መርሀ ግብር›› በሚል ርእስ ጥናት አካሄደዋል። የመርሃ ግብሩን አፈጻጸም ለመመርመርም የእጩ መምህራኑን ማስታወሻ፣ ተከታታይ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና የመገምገሚያ ቅጽ ተጠቅመው መረጃ ሰብስበዋል። መረጃዎቹ ሲተነተኑም የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰርቲፊኬ(10+1) መርሀ ግብር ችግሮች እንዳሉበት አመልክተዋል። ለችግሩ መከሰት በመንስኤነት የተጠቀሱት በኮሌጁ የቅድመ ፕራክቱክም ውይይት አለመካሄድ፤ መደበኛ መምህራን ለፕራክቲክም ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን፤ ኮሌጁ የማስተማር ልምምዱን በአግባቡ አለመከታተሉ፤ የሚሉትን ጠቅሰዋል። እነዚህና ሌሎች ችግሮች ተዳብለው የፕራክቲክምን የማስተማር ልምምድ ውጤታማነት በእጅጉ እንደጎዱት አመልክተዋል።

Kindualem (2005) "The implementation of practicum in the Education faculity of AAU. ELT. In Focus" በሚል ርእስ ያደረጉት ጥናት በመምህራን ስልጠና ላይ ከተካሄዱት ጥናቶች መካከል የሚመደብ ነው። የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በእጩ መምህራኑ ማስታወሻ ላይ በተደረገ ፍተሻ ነው። መረጃው ሲተነተንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስነ ትምህርት ፋኩልቲ በውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የተተገበረው የፕራክቲክም

መርሀ ግብር የተለያዩ ችግሮች እንደታዩበት አመልክቷል። ለችግሮቹ መከሰት በምክንያትነት የተጠቀሱትም በፕራክቲከም አፈጻጸም ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት አካላት ስለ መርሀ ግብሩ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን፤ ሃለፊነት ያለባቸው አካላት የተሰጣቸውን ግዳጅ በአግባቡ አለመወጣት፤ መርሀ ግብሩ የሚፈፀምበትን አመቺ ጊዜ አለመምረጥ፤ ለእጩ መምህራኑ ድጋፍ አለመስጠት፤ በመርሃ ግብሩ ተሳታፊ የሆኑ፣ አካላት በቅንጅት አለመስራትና ስራውን በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያስችል በጀት አለመኖር ናቸው።

ሂሩት (1998) ‹‹በፕራክቲከም ሶስት የመማር ማስተማር ልምምድና የሱፐርቫዥን አተገባበር በደቡብ ኢትዮጵያ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ 10+3 መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር›› በሚል ርእስ ጥናት አድርጋለች በጥናቱ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም የፕራክቲከም አተገባበር በችግር ውስጥ መሆኑን አሳይታለች። ለችግሩ መከሰት ምክንያት የሆኑትም ስለፕራክቲከም የግንዛቤ ማስጫበጫ ውይይት አለመካሄዱ፣ ለሱፐርቫይዘሮች ስልጠና አለመሰጠቱ፣ ሙያዊ ተዛምዶ በሌለው ባለሙያ የሱፐርቪዥን አገልግሎት መሰጠቱ፣ ትምህርት ቤቶች ፕራክቲከምን ለማስተግባር ዝግጁ ሆነው አለመገኘታቸው፤ የመሳሰሉትን ጠቅሳለች።

በላይሁን (1991) ‹‹በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሃ ግብር፣ በአማርኛ ቋንቋ ድህረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አሰጣጥ ፈተሻ›› በሚል ርእስ ጥናት አካሂዷል። ጥናቱን ከውጤት ላይ ለማድረስም የእጩ መምህራንን ማስታወሻ፣ መቅርፀ ድምፅ፣ የፅሁፍ መጠይቅ፣ የኮሌጁን የፕራክቲከም መገምገሚያ ቅጽ፣ በመሳሪያነት ተጠቅሟል። በጥናቱ ማጠቃለያ ላይም ሱፐርቫይዘሮች፣ ስለ ሱፐርቪዥን አተገባበርና ምግበ መረጃ አሰጣጥ ስልጠና አለመውሰዳቸውን፣ከሰለጠኑበት ሙያ ውጭ የሚመደቡ መሆናቸውን፣ የሚሰጡት ምግበ ምላሽ በመመሪያ አሰጣጥና በምክር ልገሳ ላይ ያተኮረ መሆኑን፣ ለምግበ ምላሽ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ያነቃቂነት ባህሪ የሌለው መሆኑን፣ ሱፐርቪዥኑ ግምገማና ምዘና ተኮር መሆኑንና የአጋር መምህራን እገዛና ክትትል አናሳ መሆኑን ያመለክታል።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የተጠቀሱት አገር በቀል ጥናቶች የተወሰኑት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከመጀመሩ በፊት የነበሩ ሲሆን ከፊሎቹ ግን ወቅታዊ ናቸው። በመሆኑም ቀደም ሲል በነበረው የማስተማር ልምምድና አሁን በተግባር ላይ ባለው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መካከል ያለውን ሁኔታ በንፅፅር ለማየት ጥናቶች ጥሩ የመነሻ ሀሳብ ይሆናሉ። ከዚህም በመነሳት ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ውጤታማ ትግበራ እንቅፋት የተባሉትን ነጥቦች ለመለየትና ለማጥናት በአጣቃሽነት ያገለግላሉ።

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

### 3.1 የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ ያተኮረው የእጩ መምህራንንና ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ስልጠና የሚሰማሩባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተልእኮ አፈጻጸም ብቃት በመቃኘት ላይ ነው። በመሆኑም ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የተመረጠው የአጠናን ዘዴ ገላጭ የምርምር ዘዴ ነው።

የጥናቱን ዘዴ ለመወሰን መነሻ የሆነው የጥናቱ አይነት የሚፈልገው ምቹ ዘዴ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ምክንያቱም በምርምር ሂደት ሁሉም ነገር በመጠን ብቻ የሚገለጽ አይደለም። በመጠን ሳይሆን በአይነት መገለጽ የሚገባቸው ጉዳዮች ብዙ ናቸው። እንደ ያለው (2001፡21) አገላለጽ ገላጭ የምርምር ዘዴ ተመራማሪው አንድን ጉዳይ አንስቶ ከፊተሽ በኋላ ካለው ነባሪዊ ሁኔታ አንጻር መረጃዎችን መሰረት አድርጎ የችግሩን አሳሳቢነት በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብበት ነው። በዚህ የምርምር ዘዴ የችግሩ ምንነት፣ የችግሩ አይነት፣ የችግሩ መጠን፣ የመሳሰሉት በመረጃ ላይ ተመስርተው የሚተረኩበት ነው። እንደ ምሁሩ አገላለጽ በገላጭ ምርምር አማካይነት የሚደረጉ ጥናቶች በጣም ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች ሲሆኑ በተለይም ችግሮች ስፋት ያላቸው ሆነው ቀጣይና ተያያዥ ጥናቶች የሚካሄዱ ከሆነ የችግሩን መልክ ለመለየትና የምርምሩን አቅጣጫ ለመወሰን የሚያስችሉ መረጃዎች ከሚደረገው ገለጻና ማብራሪያ ይገኝበታል። ምክንያቱም ገላጭ ምርምር መረጃዎችን በአሃዛዊ መጠን ለክቶ ብቻ የሚተው ሳይሆን ሰፊ ማብራሪያዎችንም አክሎ የሚከናወን የምርምር ዘዴ ነውና። በማለት ያብራሩታል።

በመሆኑም እጩ መምህራንና ለትምህት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመደቡባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች በስልጠናው ሂደት እንዲፈፅሙት የተሰጣቸውን ተልእኮ አፈጻጸም ብቃት ለመመርመርና የአለውን ገሀድ እውነታ ለማሳየት አመቺና ተመራጭ ዘዴ ገላጭ የምርምር ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ አጥኚው ሊመረምረው ለፈለገው ሀሳብ ምቹ መሆኑንም ከላይ የተገለፀው የምሁሩ ሀሳብ

የሚደግፈው ስለሆነ ይህ ጥናት በዋነኛነት የሚከተለው ገላጭ የምርምር ዘዴን እንዲሆን ተደርጓል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

በጥናቱ ወሰን ላይ በግልጽ እንደሰፈረው ይህ ጥናት የተከናወነው በደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኙ አራት የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በነዚሁ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተመደቡ እጩ መምህራን ላይ ነው፡፡ እጩ መምህራኑ በትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉት በአንደኛው ወሰነ ትምህርት ባሉት አምስት ወራት ወስጥ በተከታታይና በመደበኛነት ተመድበው ነው፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎች የሚሆኑትም ለልምምድ የተመደቡ እጩ መምህራን፣ ለእጩ መምህራኑ በአጋር መምህርነት የተመደቡ መምህራንና የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ናቸው፡፡ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚመደቡት እጩ መምህራን መሰረታዊ ተግባር በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሂደት ከቀጣዩ ቋሚ ተግባራቸው ጋር እውናዊ ትውውቅ ማድረግ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተግባርም እንዲዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ለእጩ መምህራኑ ስልጠና ምቹ ሁኔታዎች መፍጠርና ስልጠናውን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ልምምዱ ከሚካሄድባቸውና ልምምድ ከሚያደርጉ በርካታ እጩ መምህራን፣ አጋር መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በነዚሁ ትምህርት ቤቶች የተመደቡ እጩ መምህራንና እጩ መምህራኑን በቅርብ እንዲከታተሉ የተመደቡ አጋር መምህራን በተጠኝነት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህም ትምህርት ቤቶች

- አብማ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት
- ድብዛ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት
- ንጉስተክልሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት
- እንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

የነዚህ ትምህርት ቤቶች ወቅታዊ አቋምና ያላቸው ሁለንታናዊ አቅም ዝርዝር መረጃ የትምህርት ቤቶችን ወቅታዊ መረጃዎች መገለጫ ቻርት መሰረት በማድረግና በከተማው ውስጥ የሚገኙበትን ቦታ በአቅጣጫ በመጠቆም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.2.1 አብማ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት

አብማ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ሰሜናዊ ዳርቻ የሚገኝና አሁን ባለበት ሁኔታ በመደበኛ መርሃ ግብሩ ብቻ

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ተማሪ | 852 | 1012 | 1864 |
| አስተማሪ | 31 | 37 | 68 |
| የአስተዳደር ሰራተኛ | 7 | 2 | 9 |

አካትቶ የሚንቀሳቀስ ትምህርትቤት ሲሆን በዚህ የትምህርት ዘመን የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወንድ 35 ሴት 9 ድምር 44 እጩ መምህራን ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅና ከደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የተከታታይ ትምህርት ክፍል ተመድበዋል፡፡ ለነዚህ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ ነባር መምህራን መካከል 14 መምህራን በአጋር መምህርነት ተመድበው እየሰሩ መሆናቸውን ከትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ጋር በተደረገው ውይይት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 3.2.2 ድብዛ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት

ድብዛ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ምእራባዊ ዳርቻ አካባቢ የተቋቋመ የመንግስት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ በ 2003 የትምህርት ዘመን የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ለሚያከናውነው መደበኛ ተግባር

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ተማሪ | 489 | 622 | 1111 |
| አስተማሪ | 13 | 31 | 644 |
| የአስተዳደር ሰራተኛ | 7 | 1 | 8 |

ይዞ እየተንቀሳቀሰ ነው። በዚህ ትምህርት ቤት በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ብቻ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚተገብሩ ወንድ 17 ሴት 12 ድምር 29 እጩ መምህራን ተመድበዋል። የነዚህን እጩ መምህራን ተልእኮ ለማሳካት በቅርብ ክትትል እያደረጉ ድጋፍ የሚሰጡ 18 መምህራን በአጋር መምህርነት ተመድበው እየሰሩ መሆናቸውን ከትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የተሰጠው መግለጫ ያረጋግጣል።

### 3.2.3 ንጉስ ተክለሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት

ንጉስ ተክለሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ መሃል አካባቢ የተመሰረተና በከተማዋ ካሉት ትምህርት ቤቶች እድሜ ጠገቡ እንደሆነ አጥኚው በትምህርት ቤቱ በነበረው ቆይታ ከተመለከተው መረጃ አረጋግጧል። ትምህርትቤቱ በ2003ዓ.ም ዓ.ም የትምህርት ዘመን በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት መደበኛ መርሃ ግብር

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ተማሪ | 820 | 931 | 1751 |
| አስተማሪ | 34 | 41 | 75 |
| የአስተዳደር ሰራተኛ | 7 | 2 | 9 |

በማንቀሳቀስ የተለመደ ተግባሩን ያከናውናል። በዚህ የትምህርት ዘመን በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉ ወንድ 28 ሴት 5 ድምር 33 እጩ መምህራን ተመድበዋል። ትምህርት ቤቱም 21 መደበኛ መምህራንን በአጋር መምህርነት አሰማርቶ ስልጠናውን እያገዘ መሆኑን ከትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ጋር በተደረገ ውይይት ማረጋገጥ ተችሏል።

### 3.2.4 የእንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት

እንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ምስራቃዊ ዳርቻ የሚገኝ የመንግስት ትምህርት ቤት ነው። ይህ ትምህርት ቤት በ 2003ዓ.ም የትምህርት ዘመን የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት በሚተገብረው መደበኛ መርሀ ግብር

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ተማሪ | 590 | 632 | 1222 |
| አስተማሪ | 24 | 28 | 42 |
| የአስተዳደር ሰራተኛ | 6 | 3 | 9 |

ይዞ መደበኛ ተግባሩን ያከናውናል። በዚህ የትምህርት ዘመን የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ወንድ 43 ሴት 31 ድምር 74 እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅና ከደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የተከታታይ ትምህርት ክፍል ተመድበውለታል። ለነዚህ እጩ መምህራን ክትትልና እገዛ እያደረጉ ልምዳቸውን የሚያከፍሉ 21 መምህራን በአጋር መምህርነት ተመድበው እየሰሩ መሆኑን ከትምህምርት ቤቱ ርእሰ መምህር ጋር በተደረገ ውይይት ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ በተጠቀሱት አራት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተመደቡ እጩ መምህራን ወንድ 123 ሴት 57 ድምር 180 ሲሆኑ የተመደቡትም ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅና ከደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የማታው መርሀ ግብር መሆኑ በተደረገው ቅኝት ተረጋግጧል። ለእነዚህ እጩ መምህራን ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ የተመደቡ አጋር መምህራንም 86 መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል። አጥኝው በመረጃ ምንጭነት ያተኮረባቸው ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በመደበኛው መርሀ ግብር ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (10+3) የሚሰለጥኑትን 92 እጩ መምህራንና ለነዚህ እጩ መምህራን በአጋርነት የተመደቡትን 62 አጋር መምህራን ነው። ቀሪዎቹ

88 እጩ መምህራን ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ የማታው መርሀ ግብር የተመደቡ ስለሆነና ዩኒቨርስቲዎች በመደበኛ መርሀ ግብራቸው የዲፕሎማ ስልጠና ስለማይሰጡ የመረጃ መጣረስ ይፈጥረል የሚል ግምት በማስነሳቱ በመረጃ ምንጭነት አልተካተቱም፡፡ ከአጋር መምህራንም መካከል 24ቱ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ ለተላኩት እጩ መምህራን የተመደቡ በመሆናቸው በመረጃ ምንጭነት አልተያዙም፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

አጥኚው ይህን ጥናት በሚያከናውንበት ጊዜ ከመረጃ ምንጮች መካከል ተፈለጊዎችን ተጠኝዎች ለመለየት የተጠቀመበት የናሙና አመራረጥ ስልት አመቺ የናሙና ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስማር ልምምድ በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት መርሀ ግብር ተቀርጾለት የሚከናወንና አላማ ተኮር ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉም ትምህርት ቤቶች እጩ መምህራንና አጋር መምህራን የሚጠበቀው ተግባር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ አጥኚው ተጠኝዎቹን በአመቺ የናሙና ስልት እንዲመርጥ ሁኔታው ገፋፍቶታል፡፡ አመቺ የናሙና ስልትን አስመልክቶ ያለው (2001፡131) ሲያብራሩ ተመራማሪው ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ በሆኑለት ወይም በቅርበት በሚያገኛቸው ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ጥናቱን የሚያከናውን ከሆነ አመቺ የናሙና ስልት ተጠቅሟል ማለት ይቻላል፡፡ በማለት ገልጸውታል፡፡

በመሆኑም አጥኚው ለጥናት ይዞት የተነሳውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና እጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በመተግበር ሂደት የተጣለባቸውን ሀላፊነት የመወጣት ብቃት ለመፈተሽ አመቺ የመረጃ ምንጭ ናቸው ብሎ ያመነባቸውንና ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመደበኛው መርሀ ግብር በአራቱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመደቡ 92 እጩ መምህራንን፣ ለእነዚህ እጩ መምህራን በአጋር መምህርነት የተመደቡትን 62 መደበኛ መምህራንና በአራቱ ትምህርት ቤቶች ያሉ ርእሰ መምህራን፣ ምክትል ርእሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በአጠቃላይ 11 የአስተዳደር ሰራተኞች በአመቺ የናሙና ስልት በተጠኝነት ተመርጠዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ማንኛውም ጥናት ለሚሰነዝረው ሀሳብ ደጋፊ መረጃ ያስፈልገዋል። የጥናቱ ጠቀሜታ ጥንካሬና ድክመት ሊመዘን የሚችለውም በመረጃዎች ጥራትና ብቃት አማካይነት ነው። ለጥሩ መረጃ መገኘት መሰረት የሚሆነው ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው ጥራትና ትክክለኛነት መሆኑን ምሁራን ያረጋግጣሉ። ይህን ሁኔታ Lokesh (2006፡187) ሲያብራሩ ለአንድ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ጥንካሬ በሚሰበሰቡበት የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ አይነት ትክክለኛነት ላይ የተመሰረተ ነው። በተለይም አብዛኞቹ የሰነ ባህርይ፣ የስነ ልቦናና የስነ ትምህርት ሳይንስ ጥናቶች መረጃዎቻቸው ቃላዊ /Verbal/ ናቸው። እንዲህ አይነቱን መረጃ ለመሰብሰብ ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ ወይም ቃለመጠይቅ፣ መጠቀም አለበለዚያም ምልከታ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም ጎልቶ የሚታየው የመረጃዎቹ ባህሪ አይነታዊ/qualitative/ በመሆኑ ነው። በማለት ይገልጹታል።

በመሆኑም አጥኚው ይዞት ለተነሳው ርእሰ ጉዳይና ለመረጠው የአጠናን ዘዴ ተስማሚነት አላቸው ብሎ ያመነባቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መርጦ በማዘጋጀት በስራ ላይ አውሏል። ለጥናቱ የተመረጠው የአጠናን ዘዴ ገላጭ የምርምር ዘዴ በመሆኑና የተለያየ ባህሪና መጠን ያላቸውን ተጠኚዎች የሚያተኩር በመሆኑ ከእጨ መምህራንና ከአጋር መምህራን የሚፈለገውን መረጃ በሁለት የተለያዩ የጽሁፍ መጠይቆች፣ ከአስተዳደር ሰራተኞች የሚፈለገውን መረጃ በቃለ መጠይቅ፣ አጠቃላዩን የእጨ መምህራን እንቅስቃሴና ከትምህርት ቤቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ የሚፈለገውን መረጃ ደግሞ በምልከታ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። እነዚህን ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አጥኚው እንዴት በስራ ላይ እንዳዋላቸውና ለምን እንደመረጣቸው በዝርዝር ማየት አስፈላጊ በመሆኑ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ በበርካታ ጥናቶችና አጥኚዎች በስራ ላይ ሲውል ይታያል። ይህን ሁኔታ Kothar (2006:100-102) ሲያብራሩ መጠይቅ እጅግ ሰፊ እውቅና ያለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። መሳሪያው በታዋቂ ተመራማሪዎች፣

በግልና በህዝባዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ ተቋማት፣ በመሳሰሉት ተዘውትሮ አገልግሎት ላይ ይውላል። ለዚህም አብይ ምክንያቱ ቦታ ሳይወስነው በአንድ ጊዜ ከበርካታ ተጠኝዎች ምላሽ ለማሰባሰብ ማስቻሉ ነው። መሳሪያው ዝግ ወይም ክፍት ጥያቄዎችን እንደስፈላጊነቱ ለማስተናገድ አመቺ ከመሆኑም በላይ ለመላሾች ሙሉ ነጻነት የሚሰጥ በመሆኑ ብዙዎቹ ተመራማሪዎች ይመርጡታል። በማለት የመጠይቅን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ጠቀሜታና ተመራጭነት ያብራራሉ።

ስለሆነም እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ቆይታቸው የተሰጣቸውን ሀላፊነት ለመወጣት የሚሳዩትን ትጋትና ሀላፊነትን የመወጣት ብቃት፣ አጋር መምህሮቻቸው የሚያደርጉላቸውን ድጋፍና የአጋር መምህራንን ሀላፊነት የመወጣት ብቃት፣ የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አመቺውና አዋጭው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መጠይቅ መሆኑን አጥኝው አምኖበት አዘጋጅቷል። ምክንያቱም እጩ መምህራን የመምህርነት ተግባርን በእውናዊ አውድ ውስጥ ለመለማመድ፣ አጋር መምህራን ደግሞ እጩ መምህራንን በመምራት፣ በማሳተፍና በመገምገም ሂደት የሚያደርጉት ጥረት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆኑን ለመለየት የሚያስችል በመሆኑ ነው። መጠይቆች ሁለት የተለያየ ይዘት ያላቸው ሲሆኑ አንዱ ለእጩ መምህራን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለአጋር መምህራን የተዘጋጁ ናቸው። መጠይቆች እያንዳንዳቸው ሁለት፣ ሁለት፣ አበይት ክፍሎች ያሏቸው ሲሆን፤ የመጀመሪያው የተጠኝዎችን አጠቃላይ መረጃ የሚመለከት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተጠኝዎች በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የየበኩላቸውን ሃለፊነት የመወጣት ብቃት የሚጠይቁና በጣም ጥሩ፣ ጥሩ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ አምስት፣ አምስት፣ አማራጮች ያሏቸው ሃያ፣ ሃያ፣ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች በአመቺ የናሙና ስልት ለተመረጡት 92 እጩ መምህራንና 62 አጋር መምህራን ታድለው በነጻ ስሜትና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል።

### 3.4.2 ቃለ መጠይቅ

ከተለመዱት የጥናትና ምርምር መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ። እንደ ያለው (2001፡178) አገላለጽ፣ ቃለመጠይቅ

በጠያቂና በተጠያቂ መካከል የሚካሄድ የፊት ለፊት ተራክቦ ነው። በመሆኑም ቃለ መጠይቅን ተጠቅሞ ከበርካታ ተጠኝዎች መረጃ መሰብሰብ ያስቸግራል። ቃለ መጠይቁን ማድረግ ቢቻል እንኳ ከቃለ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ ማቀናጀትና መተንተን በጣም አስቸጋሪ ይሆናል በመሆኑም በብዙ ተመራማሪዎች እንደዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተደርጎ አይወሰድም ሆኖም በቁጥር ውሱን ከሆኑ ተጠኝዎች መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ አስፈላጊ ነው በማለት ያስረዳሉ።

ስለዚህ አጥኝው የጥናቱ ተተኳሪ ካደረጋቸው ተጠኝዎች መካከል አራት ርእሰ መምህራን ሦስት ምክትል ርእሰ መምህራንና በአራቱም ትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት ያላቸው አራት የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች በድምሩ አስራ አንድ የትምህርት አስተዳደር ሰራተኞች የሚሰጡት መረጃ ተዛምዶ ያለውና ከውሱን ተጠኝዎች የሚሰበሰብ በመሆኑ በቃለ መጠይቅ እንዲሰበሰብ ተደርጓል። እነዚህ ተጠኝዎች በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሂደት እጩ መምህራን ያላቸውን የርስ በርስ ትብብርና መግባባት፣ ከሌሎች ለመማርና እርስ በርስ ለመማማር የሚያደርጉትን ጥረት፣ ከአጋር መምህራንና ሌሎች መደበኛ መምህራን ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ ለትምህርት ቤቶች ደንብና ስነ ስርአት ያላቸውን ተገዢነት፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ ልምዶችና ወጎች ያላቸውን አመለካከት፣ የመሳሰሉትን መረጃዎች ይሰጣሉ ተብሎ ታምኖባቸዋል። በመሆኑም ከአስራአንዱ የትምህርት አስተዳደር ሰራተኞች መረጃ የሚሰበሰብባቸው አስር የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ምላሹ በመቅርፀ-ድምፅ ከተቀዳ በኋላ ወደ ጽሁፍ ተለውጧል። የተገኘው መረጃም በዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ከተገኘው መረጃ ጋር ተቀናጅቶ ተተንትኗል።

### 3.4.3 ምልከታ

ምልከታ አጥኝው የሚፈልገውን መረጃ ይገኝበታል ብሎ ባቀደው ክልል ተገኝቶ ሁኔታውን የሚቃኝበት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። ይህን አስመልክቶ Kothar (2006:96) ሲያብራሩ፣ ምልከታ በታቀደ ጥናትና ምርምር ውስጥ እንዲያገለግል ታልሞ ሲሰራበት ሳይንሳዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ይህም የሚሆነው በስልታዊ ዘዴ ታቅዶ እየተመዘገበ የሚከናወን ከሆነ ነው። የምልከታ ዘዴን

በመሳሪያነት ተጠቅሞ የሚሰበስቡ መረጃዎች በተመራማሪው በራሱ ቀጥታ ምልከታ የሚደረግበትና መልስ ሰጪ ወይም ተጠያቂ የማያስፈልገው በመሆኑ መረጃው አስተማማኝነት ያለው ነው። በምልከታ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በተለይ ለስነ- ባህሪ ጥናት ያላቸው ጠቀሜታ የላቀ ነው። በማለት ገልጸውታል።

በመሆኑም አጥኚው ለጥናት በመረጣቸው አራት የመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመገኘትና ምልከታ በማድረግ ትህምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሰጡትን ትኩረት፣ እጩ መምህራን ተልኳቸውን በብቃት ለመወጣትና ክህሎታቸውን ለማዳበር እያደረጉት ያለውን ጥረት፣ አጋር መምህራን እጩ መምህራኑን በማቅረብ፣ በመምራት፣በማረምና ልምድ በማካፈል እያደረጉላቸው ያለውን ድጋፍ በተመለከተ መረጃዎችን ሰብስቧል። ይህንን ሁኔታ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግም 21 የምልከታ መከታተያ ነጥቦችን በሰንጠረዥ አዘጋጅቶ በስራ ላይ አውሏል። በምልከታ የተገኘው መረጃም በሌሎች መሳሪያዎች ከተሰበሰቡት ጋር ተቀናጅቶ ተብራርቷል።

በአጠቃላይ አጥኚው የጥናቱን መረጃዎች በሶስት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰበሰበ ሲሆን የተገኙት መረጃዎች ባግባቡ ተተንትነው ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ጥያቄ መልስ እንዲያመለክቱ ተደርጓል።

## 3.5 የመረጃዎች አተናተን

የምርምር መሰረታዊ አካል መረጃ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል። ያለው (2001፡133) ይህን በተመለከተ በሰጡት ገላጻ ትክክለኛና አስተማማኝ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መጠቀምና ለጥናቱ መጣኝ መረጃ መሰብሰብ የምርምር ዋነኛ አካል ነው። ሆኖም ግን ይህ በራሱ ጥናቱን ከመጨረሻው ደረጃ ላይ አያደርሰውም ምክንያቱም የተሰበሰበው መረጃ አግባብ ባለው የትንተና ዘዴ ተተንትኖ ውጤቱን ማመልከት ይኖርበታል። ትንተናውን ለማካሄድ እንዲቻል የተሰበሰበው መረጃ ለትንተና በሚያመች መልክ ተደራጅቶ ትርጉም ሊሰጥ በሚችልበት ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል። በማለት ያብራሩታል።

በመሆኑም ለዚህ ጥናት ግብአት ይሆናሉ ተብለው በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት ለተሰበሰቡት መረጃዎች አመቺ ነው ተብሎ የታመነበትን ስልት በመምረጥ ትንተናው ተከናውኗል። ጥናቱ የተጠቀመበት ስልት ገላጭ እንደመሆኑ መጠን አብዛኞቹ መረጃዎች የተተነተኑትም በገለጻ ስልት ነው። በይዘታቸው አሃዛዊ የሆኑት መረጃዎች በመቶኛ እየተሰሉ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። የመረጃ አተናተን ስልቱን ቅደም ተከተል በተመለከተም በመጀመሪያ በመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ተተንትነው ውጤታቸው ከታየ በኋላ ከቃለ መጠይቅና ምልከታ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ እንደአስፈላጊነቱ በደጋፊነት ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች አቀራረብና አተናተን

ይህ ክፍል በመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበትና የሚብራሩበት ነው። በመሆኑም አጥኝው በዋነኛ የመረጃ መሠብሠቢያ መሣሪያነት የመረጠውን የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች በማስቀደምና የቃለ መጠይቅና የምልከታ መረጃዎችን በደጋፊነት በማስከተል ትንተናውን አከናውኗል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ ሁለት አይነት ነው፡፡ ይኸውም ለእጩ መምህራን የቀረቡና በ10 መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ 20 ጥያቄዎችና ለአጋር መምህራን የቀረቡና በ9 መሠታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ 20 ጥያቄዎች ናቸው። ጥያቄዎች ያተኮሩባቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ፣ ለእጩ መምህራኑ በተዘጋጀው መጠይቅ ላይ የቀረቡት 20 ጥያቄዎች በ10 ሰንጠረዦች ለአጋር መምህራን የቀረቡት 20 ጥያቄዎች ደግሞ በ9 ሠንጠረዦች በድምሩ በ19 ሠንጠረዦች ተጠቃለው ቀርበዋል።

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተሳታፊዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በኃላፊነት በመምራት ላይ ያሉ ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርእሰ መምህራንና የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ናቸው። ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁት ጥያቄዎች 10 ሲሆኑ ከነዚህም የተገኙት መረጃዎች በሚያስተላልፉት መልእክት አንፃር ከመጠይቅ የተገኘውን መረጃ ተከትለው ተብራርተዋል።

ምልከታው የተከናወነው በአራቱ ተጠኝ ትምህርት ቤቶች ላይ ሁለት፣ ሁለት፣ ጊዜ ነው። ምልከታውን ለማድረግ የሚያስችሉ 21 ነጥቦች ያሉት የምልከታ መከታተያም ተዘጋጅቷል። ከምልከታው የተገኘው ጥቅል መረጃም ለግልጽነት በሚያመች መልኩ ተዘርዝሯል።

ከላይ የተጠቀሱትን የመረጃ መሰብሰቢያዎች ዝርዝር ይዘት ከአባሪ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስትና አራት ከገጽ 83 እስከ 91 መመልከት ይቻላል።

የተጠኝዎች አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ እጩ መምህራን ወንድ 60 ሴት 32 ድምር 92 ሲሆኑ ሁሉም የሶስተኛ ዓመት 10+3 መርሃ ግብር ሰልጣኝ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል መምህራን ናቸው። አጋር መምህራን በተመለከተ ደግሞ ወንድ 37 ሴት 25 ድምር 62 ሲሆኑ የትምህርት ደረጃቸው ሁሉም የዲፕሎማ ምሩቃን ናቸው። የአጋር መምህራኑ እድሜ ከ26-51 ሲሆን የአገልግሎት ዘመናቸውም ከ7-32 ዓመት መሆኑን ከሞሉት መጠይቅ ላይ ለመረዳት ተችሏል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች ርእሰ መምህራን ወንድ 4 ሴት ----- ድምር 4፣ ምክትል ርእሰ መምህራን ወንድ 1 ሴት 2 ድምር 3 ሱፐርቫይዘሮች ወንድ 4 ሴት ----- ድምር 4 ሲሆኑ በአጠቃላይ በዚህ የስራ ዘርፍ የተሰማሩና በቃለ መጠይቅ የተስተናገዱ ተጠኝዎች ወንድ 10 ሴት 1 ድምር 11 ናቸው። የነዚህ ተጠኝዎች እድሜ ደግሞ የርእሰ መምህራን ከ 29-54 የምክትል ርእሰ መምህራን ከ27-42 የሱፐርቫይዘሮች ደግሞ ከ28-38 መሆኑ ተረጋግጧል። የትምህርት ደረጃቸው ርእሰ መምህራን ዲግሪ 3 ዲፕሎማ 1 ድምር 4 ምክትል ርእሰ መምህራን ዲግሪ 1 ዲፕሎማ 2 ድምር 3 ሱፐርቫይዘሮች ደግሞ 4ቱም የዲግሪ ምሩቃን መሆናቸውን መረጃው ያሳያል።በመሆኑም ሁሉም ተጠኚዎች የቀረቡላቸውን የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ዳራ ያላቸው በመሆኑ የሰጡት መረጃ የተሟላ ነው ተብሎ ተምኖበታል።

## 4.1 የመረጃዎች ትንተና

መጠይቅ ከተበተነላቸው 92 እጩ መምህራንና 62 አጋር መምህራን የተሠበሠበው መረጃ በትክክል ለመሞላቱ ከተፈተሸ በኋላ በእያንዳንዱ አማራጭ የተገኘው ውጤት በአሃዝ እየተሰላ ተጠቃሏል። የተጠቃለለውን ምላሽ መሠረት በማድረግም በየርእሰ ጉዳዮቹ ሠንጠረዦች ተዘጋጅቶለት በመቶኛ እየተሠላ የተጠኝዎችን ዝንባሌ በግልፅ እንዲያሣይ ተደርጎ ተቀምጧል። ከእያንዳንዱ ሠንጠረዥ ግርጌም በየሠንጠረዡ የተደረገው ስሌት የሚያመለክተውን አሃዛዊ መረጃ የሚያብራራ መግለጫ ተሠጥቶበታል።

### 4.1.1 ለእጩ መምህራን ከቀረበው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለእጩ መምህራን የቀረበው መጠይቅ 20 ጥያቄዎችን ያካተተ ነው፡፡ እነዚህ ሃያ ጥያቄዎች ያተኮሩባቸው ፍሬ ነገሮች ደግሞ 10 ናቸው፡፡ በነዚህ 10 ፍሬ ነገሮች ላይ የተሠጡት መረጃዎች በቀጣዮቹ 10 ሠንጠረገዦች አማካይነት ተተንትነዋል።

ሠንጠረዥ 1፡ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያሠማራው ኮሌጅ የሠጠው ተልእኮ ተገቢነት፣

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሃ-ግብር ወደ ተመደብህበት /ሽበት/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመምጣትህ/ሽ/ በፊት ከምትማርበት/ሪበት/ ኮሌጅ የተሠጠህ/ሽ/ የተግባር አፈፃፀም ተልእኮ አሁን ለምታደርገው/ጊው/ ተግባራዊ ልምምድ ምን ያህል እገዛ አድርጐልሃል/ሻል/? | በ/ጥሩ | 18 | 56.3 | 42 | 70.0 | 60 | 65.2 |
| | | ጥሩ | 8 | 25.0 | 14 | 23.3 | 22 | 23.9 |
| | | መካከለኛ | 5 | 15.6 | 1 | 1.7 | 6 | 6.5 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | 3 | 5.0 | 4 | 4.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 2 | ከማሠልጠኛ ኮሌጁ የተሠጠህ/ሽ/ የተግባራዊ ልምምድ አፈፃፀም ተልእኮ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አቀባበል ጋር ስታገናኘው/ኝው/ ስምምነቱ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 10 | 31.3 | 14 | 23.3 | 24 | 26.8 |
| | | ጥሩ | 14 | 43.8 | 31 | 51.6 | 45 | 48.9 |
| | | መካከለኛ | 6 | 18.8 | 10 | 16.6 | 16 | 17.4 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 3 | 5.0 | 5 | 5.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | 2 | 3.3 | 2 | 2.2 |

በሠንጠረዥ 1 ላይ የሠፈረው መረጃ እንደሚያመለክተው ተጠኝዎች ለቀረቡላቸው ሁለት ጥያቄዎች የሠጡት ምላሽ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ እጩ መምህራኑን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሢያሠማራ የሚሠጣቸው ተልእኮ መሠረታዊ አላማቸውን ግብ ለማስመታት ያለውን እገዛና ከመጀመሪያ ደረጃ

ትምህርት ቤቶች አላማ ጋር ያለውን ስምምነት የሚለካ ነው። በመሆኑም ተልእኮው ለተግባራዊ ልምምዱ ያለውን እገዛ በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኝዎች 65.2% በጣም ጥሩ፣ 23.9% ጥሩ፣ 6.5%፣ መካከለኛ፣ 4.4% ደግሞ ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሠጥተዋል።

ተጠኝዎች የሠጡትን ምላሾች ካላቸው ቀረቤታ አንፃር አጠቃግተን ብንመለከታቸው ደግሞ በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች ከጠቅላላ ተጠኝዎች መካከል 89.1% ናቸው፡፡ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ብለው ምላሽ የሠጡት ደግሞ 4.4% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 6.5% ደግሞ መካከለኛ ብለው የመለሱ ናቸው፡፡ ይህ እንግዲህ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለእጩ መምህራን የሚሠጠው የአፈፃፀም ተልእኮ ለተግባራዊ አፈፃፀማቸው ያለውን እገዛ የሚመለከት ነው። በዚህ መረጃ መሰረት እጩ መምህራኑ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች ሲሄዱ ከአሰልጣኝ ኮሌጁ የሚሰጣቸው የአፈጻጸም ተልእኮ ለተግባራዊ ክንዋኔያቸው ያለው እገዛ በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ተልእኮው እጩ መምህራኑ ለተግባር ከሚሠማሩበት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያለውን ስምምነት በተመለከተም ለቀረበው ጥያቄ 26.8% በጣም ጥሩ፣ 48.9% ጥሩ፣ 17.4% መካከለኛ፣ 5.4% ዝቅተኛ፣ 2.2% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሠጥተዋል። ይህን ሁኔታ ሠብሠብ አድርገን ስናስቀምጠው ደግሞ በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ምላሽ የሠጡ ተጠኝዎች 75.7% ሲሆኑ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ብለው የመለሱ ተጠኝዎች ደግሞ 7.6% ናቸው። ቀሪዎቹ 17.4% መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው። ይህም የሚያሳየን የእጩ መምህራኑ ተልእኮ ለስልጠና ከሚሰማሩባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያለው መስተጋብር በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን ነው።

በሌላ መልኩ ሁኔታውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶችን ለሚመሩት ርእሰ መምህራን፣ምክትል ርእሰመምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማጠናከር ተሞክሯል።የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮ

እና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጧቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቶች ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማወቅ ለቀረበው ቃለመጠይቅ ጉልበት የተባለው ተጠኚ ሲመልስ ‹‹የመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ተልእኮ ከሀገራዊ የትምህርት ፖሊሲው ጋር የተያያዘ በመሆኑ የተልእኮ ግጭት አይታይም፡፡ አላማውም አንድ አይነት በመሆኑ እስከአሁን የገጠመን ችግር የለም፡፡›› (ቃሀሳስ 4/2003ዓ.ም) በማለት ገልጾታል፡፡ አጥኚው በትምህርት ቤቶች በነበረው ቆይታና በአደረገው ምልከታ ያገኘው መረጃም ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

በተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት ላይ እንደታየው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እጩ መምህራን ለሚሰማሩበት የማስተማር ተግባር ብቁ ሊያደርግ የሚችል ተቋማዊ ተልእኮ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ይህንኑ ሁኔታ Armstrong (1991፣90)፡፡ የመምህረነት ተግባር በብቃት ለመፈጸም የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ንድፈ ሀሳባዊ እውቀት በተግባራዊ ልምምድ እየታገዘ ስልጠናው መከናወን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ስልጠና ግለሰቦችን የተቋሙን መሰረታዊ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ጠቃሚ እውቀትና ክህሎት የሚያላብስ ተግባር ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

በመሆኑም ከሠንጠረዥ አንድ የተገኘውን መረጃ ስንመለከተው የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላሠማራቸው እጩ መምህራን የሠጣቸው ተልእኮ ለሠልጣኞች ተግባራዊ አፈጻጸም በቂ እገዛ ከማድረጉም በላይ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም መሆኑም ተረጋግጧል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡እጩ መምህራን በራስ አገዝ ዘዴ ከትምህርት ቤት ተሞክሮ ለመማር የሚያደረጉት ጥረት

| ተራ ቁ. | በመጠይቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 3 | ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በተመደብህበት/ሽበት/ ትምህርት ቤት ውስጥከሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት እራስህን/ሽን/ ለማስተማር የምታደርገው/ጊው/ ጥረት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 17 | 53.1 | 41 | 68.3 | 58 | 63.0 |
| | | ጥሩ | 10 | 31.3 | 15 | 25.0 | 25 | 27.2 |
| | | መካከለኛ | 3 | 9.4 | 4 | 6.7 | 7 | 7.6 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | - | - | 1 | 1.1 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | - | - | 1 | 1.1 |
| 4 | የትምህርት ቤቱን አስተዳድራዊ ስርአቶች በመቃኘት ለወደፊት ቋሚ ተግባርህ/ሽ/ የሚያግዝ ማስታወሻ የመያዝ ልምድህ/ሽ/ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 10 | 31.3 | 22 | 36.6 | 32 | 34.8 |
| | | ጥሩ | 15 | 46.9 | 29 | 48.3 | 44 | 47.9 |
| | | መካከለኛ | 4 | 12.5 | 7 | 11.6 | 11 | 11.9 |
| | | ዝቅተኛ | 3 | 9.4 | 2 | 3.3 | 5 | 5.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

በሠንጠረዥ 2 የተተነተነው እጩ መምህራን ራስ አገዝ በሆነ መንገድ ከትምህርት ቤቶች ተሞክሮ ለመማር እያደረጉት ያለውን ጥረት ለመቃኘት ታስቦ ለተዘጋጁት ሁለት ጥያቄዎች የሠጡት ምላሽ ነው። የመጠይቆቹ ይዘት፣ የመጀመሪያው ጥያቄ ተጠኝዎች ከትምህርት ቤቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለመማር ያለቸውን ፍላጐትና ጥረት የሚቃኝ ሲሆን ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ የተግባር ልምምዱን በራስ አገዝ ጥረት ለማጐልበት የሚያስችል የማስታወሻ አያያዝ ልምድ መኖር አለመኖሩን ለመዳሠስ የቀረበ ነው። በተገኘው መረጃ መሠረትም እጩ መምህራን ራሳቸውን ከትምህርት ቤቱ ተሞክሮ ለማስተማር እያደረጉት ያለውን ጥረት 63.0% በጣም ጥሩ ብለው ሲመልሱ 27.2% ደግሞ ጥሩ ብለው ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ እነዚህን ሁለት አማራጮች የመለሱ ተጠኝዎች ድምር 90.2% ነው። ለዚህ ጥያቄ ዝቅተኛ የሚል ምላሽ የሠጡት 1.1% ሲሆኑ በጣም ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 1.1% ናቸው። የነዚህም ድምር ውጤት ሲታይ 2.2% ይሆናል። ቀሪዎቹ 7.6% የሰጡት ምላሽ ደግሞ መካከለኛ የሚል ነው።

በመሆኑም እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቶች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ራሳቸውን ለማስተማር እያደረጉት ያለው ጥረት በአጥጋቢ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

ከዚሁ ነጥብ ጋር በተሣሠረ ሁኔታ ሠልጣኞች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚከናወኑ አስተዳደራዊ ስርአቶችን በትኩረት ቃኝተው ጠቃሚ ልምዶችን በማስታወሻ የመያዝ ልምዳቸውን ለመፈተሽ ለቀረበው ጥያቄም ከጠቅላላ ተጠኝዎች መካከል 34.8% በጣም ጥሩ ሲሉ 47.9% ደግሞ ጥሩ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል። የነዚህ ሁለት ምድቦች የመቶኛ ስሌት ድምር 82.7% ነው። ለዚህ ጥያቄ 5.4% ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሲሠጡ በጣም ዝቅተኛ ያለ ተጠኝ ግን የለም፡፡ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡት ደግሞ 11.9% ናቸው። ስለዚህ እጩ መምህራን በተያዘላቸው እቅድ መሰረት ራሳቸውን ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረት በትክክለኛ አቅጣጫ ላይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተውም እጩ መምህራን በራስ አገዝ ዘዴ ራሳቸውን ብቁ መምህር ለማድረግ እየጣሩ ያሉ መሆኑን ነው። ለአብነት ያህል ሰማይነህ የተባለው ተጠኚ በሰጠው ገለጻ

> *እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች ሲመጡ በመጀመሪያ ምልከታ ያደርጋሉ። በዚህ ሂደት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር አጋር መምህራንና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እገዛ እያደረገ የማብቃት ተግባር እንዲከናወን ሁኔታዎችን ስለምናመቻች የሚያገኙት እውቀት በጣም ጠቃሚ ነው። (ታህሳስ 4/2003ዓ.ም)*

በማለት ገልጾታል። ይህም ሁኔታ የሚያመለክተው እጩ መምህራን በራስ አገዝ ዘዴ ከትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለመማር የሚያደርጉት ጥረት በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን ነው። በምልከታ የተገኘው መረጃም የሚያመለክተው ከላይ በመጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው።

በተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ላይ እንደተገለፀው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በስራ

ላይ ልምምድ የሚሳተፉ ድርጅቶችን ተግባርና ሀላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ (አብከመ 1997፣63) ስልጣኛች የስልጠናውን ግብ ለማሳካት በስራ ላይ ልምምድ የተመደቡበትን ድርጅት ያሰራርና አመራር ሂደት ከመገንዘብ ጀምሮ ልምምዱን በትጋት በማከናወን ራስን ብቁ ባለሙያ ለማድረግ መጣር እንዳለባቸው ያብራራል፡፡

በመሆኑም እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከተሠማሩባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ በራስ አገዝ ዘዴ ለመማር እያደረጉት ያለው ጥረት የተጠናከረ መሆኑን የተገኘው መረጃ አረጋግጧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያላቸው ዝግጅት**

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 5 | ስልጠና እየወሰድህበት/ሽበት/ ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሃ-ግብር መሣካት እያደረገ ያለው ትብብር ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 15 | 46.9 | 30 | 50.0 | 45 | 48.9 |
| | | ጥሩ | 11 | 34.4 | 21 | 35.0 | 32 | 34.8 |
| | | መካከለኛ | 4 | 12.5 | 8 | 13.3 | 12 | 13.0 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 1 | 1.7 | 3 | 3.3 |
| | | በ/ ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 6 | እጩ መምህራን ሁሉንም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ቃኝተው ራሣቸውን ከተግባር እንዲያስተምሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቱ አስተዳደር የፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 11 | 34.4 | 24 | 40.0 | 35 | 38.0 |
| | | ጥሩ | 8 | 25.0 | 25 | 41.6 | 33 | 35.9 |
| | | መካከለኛ | 8 | 25.0 | 4 | 6.7 | 12 | 13.0 |
| | | ዝቅተኛ | 5 | 15.6 | 7 | 11.6 | 12 | 13.0 |
| | | በ/ ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

በሠንጠረዥ 3 ላይ የተተነተነው አሃዝ የሚያሣየው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያላቸውን ዝግጅት

በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተጠኝዎች የሠጡትን ምላሽ ነው፡፡ ይህን ነጥብ ለመፈተሽ ሁለት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሐ-ግብርን ለማሣካት እያደረጉ ያለው ትብብር ምን ይመስላል? የሚልና እጩ መምህራን ራሣቸውን ከተግባር ማስተማር ይችሉ ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቱ አስተዳደር የፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው፡፡ ለመጀመሪያው ጥያቄ 48.9% በጣም ጥሩ፣ 34.8% ጥሩ የሚል አስተያየት ሠጥተዋል። የሁለቱ ድምር ደግሞ 83.7 ሆኗል። ለዚህ ጥያቄ 13.0% ተጠኝዎች መካከለኛ የሚል ምላሽ ሲሠጡ 3.3% ደግሞ ዝቅተኛ ብለዋል፤ በጣም ዝቅተኛ የሚለውን አማራጭ መልስ የመረጠ ተጠኝ ግን የለም። ይህም የሚያሳየን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች ለስልጠናው የሰጡት ትኩረትና ያላቸው ዝግጁነት ስልጠናውን ለማሳካት በሚያስችል ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሃሣብ በቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ 38.0% በጣም ጥሩና 35.9% ጥሩ ብለው መልሠዋል። የነዚህ ሁለት ምድብ መልሶች ድምር 73.9% ይሆናል፡፡ 13.0% ተጠኝዎች መካከለኛ የሚል ምላሽ ሲኖራቸው በተመሣሣይ ሁኔታ 13.0% የሆኑት ደግሞ ዝቅተኛ ብለው ሰጥተዋል። በጣም ዝቅተኛ የሚለውን አማራጭ የመረጠ ተጠኝ ግን የለም። ከዚህም የምንረዳው ሰልጣኞች እራሳቸውን ከተግባር ያስተምሩ ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች በተለይ በአስተዳደራዊ ስራዎች ለማሳተፍ ያላቸው ዝግጁነት በትኩረት ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን ነው።

በምልከታ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተውም ትምህርትቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም ሊሰራባቸው የሚችሉ መለስተኛ ችግሮች ያሉ መሆኑን ነው።

በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት በተደረገው የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት እንደተገለፀው የባህርዳር ዩኒቨርስቲ የርቀት ትምህርት ክፍል ባዘጋጀው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሞጁዩል BDU (2008፡13-15) MOE 2003 በመጥቀስ

እንዳብራራው ትምህርት ቤቶች ለስልጠና የሚመደቡላቸውን እጩ መምህራን በሁሉም የክፍል ደረጃዎችና የትምህርት አይነቶች ተግባራዊ ተሞክሮ እንዲያገኙ የሚያስችል ምቹ መርሀ ግብር የመዘርጋትና እያንዳንዱን ሰልጣኝ አገዛና ክትትል የሚያደርግለት አጋር መምህር የመመደብ ሀላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

በመሆኑም የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እየተካሄደባቸው ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፕሮግራሙን የተሳካ ለማድረግ የበኩላቸውን ጥረትና ዝግጅት እያደረጉ ቢሆንም ትኩረት ተሰጥቶት ሊታይ የሚገባው ችግር ያለ መሆኑንም መረጃው አመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ ተግባራት ለመማር እያደረጉት ያለው ጥረት

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 7 | እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ ሁለገብ እንቅስቃሴ በመማር ራሣቸውን ብቁ መምህር አድርገው ለመቅረጽ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | በ /ጥሩ | 12 | 37.5 | 24 | 40.0 | 36 | 39.1 |
| | | ጥሩ | 11 | 34.4 | 24 | 40.0 | 35 | 38.0 |
| | | መካከለኛ | 6 | 18.8 | 10 | 16.6 | 16 | 17.4 |
| | | ዝቅተኛ | 3 | 9.4 | 1 | 1.7 | 4 | 4.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | 1 | 1.7 | 1 | 1.1 |
| 8 | እጩ መምህራን የትምህርት ቤቱን ህግን ደንብ አክብረው ተልዕኳቸውን ለመፈፀም እያደረጉት ያለውን ጥረት እንዴት ታየዋለህ /ታይዋለሽ/? | በ/ጥሩ | 15 | 46.9 | 31 | 51.6 | 46 | 50.0 |
| | | ጥሩ | 11 | 34.4 | 19 | 31.6 | 30 | 32.5 |
| | | መካከለኛ | 5 | 15.6 | 5 | 8.3 | 10 | 10.9 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | 4 | 6.7 | 5 | 5.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | 1 | 1.7 | 1 | 1.1 |

ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተሠማሩ እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ ከሚከናወኑ የትምህርት ቤት ተግባራት ለመማር እያደረጉት ያለውን ጥረት ለመለካት በመጠይቁ ላይ የሠፈሩት ሁለት ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ለነዚህ

ጥያቄዎች የተሠጠው ምላሽ በአሃዝ ተጠቃልሎ በመቶኛ ሲሠላ እጩ መምህራት የትምህርት ቤቶችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በመቃኘት እራሣቸውን ብቃት ያለው መምህር አድርገው ለመቅረጽ የሚያደርጉትን ጥረት የሚለካውን ጥያቄ 39.1% በጣም ጥሩ ብለው ሲመልሱ 38.0 ጥሩ፣ 17.4% መካከለኛ፣ 4.4% ዝቅተኛ፣ 1.1% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሚል መልስ ሠጥተዋል። የተጠኝዎች ምላሽ ተሠባስቦ ሲታይ ደግሞ 77.1% የሆኑት ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ 5.5% የሆኑት ደግሞ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ብለው መልሠዋል። ቀሪዎቹ 17.4% የሆኑት ደግሞ መካከለኛ ብለው የመለሱ ናቸው። ይህም መረጃ እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ እንቅስቃሴዎች ለመማር እና ለመለወጥ የሚያደርጉት ጥረት በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

እጩ መምህራን ከትምህርት ቤት ህግና ደንብ አክባበርና አፈፃፀም ለመማር የሚያደርጉትን ጥረት ለመለካት የቀረበው ጥያቄ ላይ ደግሞ 50.0% በጣም ጥሩ፣ 32.5% ጥሩ፣ 10.9 መካከለኛ፣ 5.4% ዝቅተኛ፣ 1.1% በጣም ዝቅተኛ ብለው ምላሽ ሠጥተዋል። በዚህ ጥያቄ ላይ የተሠጠው ምላሽ ሲሰበሰብ 82.5% በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ 6.5% ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ያሉ ናቸው። ቀሪዎቹ 10.9% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል። ከዚህ ጥያቄ አንጻር ሲታይ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤቶች ህግና ደንብ ያላቸው ተገዥነት በአጥጋቢ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ሁኔታውን ለትምህርት ቤቶች አስተዳደር ሰራተኞች በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማጠናከር በተደረገው ጥረት የተገኘው ውጤትም እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ በሚከናወኑ የትምህርትቤቶች ተጓዳኝ ተግባራት ላይ ያላቸው ተሳትፎ በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ ተመስገን የተባለው ተጠኚ ሲገልጽ

> *መምህርነት ሙያው ሁለገብነት ይታይበታል። በመሆኑም ስልጠናው የክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጭም በሚከናወኑ ተግባራት ያተኩረ መሆን አለበት። በመሆኑም እጩ መምህራን በክበባት ተሳትፎ፣ በተማሪዎች መልካም ስነ- ምግባር ግንባታ፣ በትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ በትምህርት ቤት ጽዳትና ውበት በመሳሰሉት ላይ ንቁ ተሳትፎ አላቸው። (ታህሳስ 8/2003ዓ.ም)*

በማለት አብራርተዋል። ይህም የሚያመለክተው ከክፍል ውጪ በሚከናወኑ የትምህርት ተግባራት ላይ የእጩ መምህራኑ ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ቆይታቸው ከትምህርት ቤቶች ሁለንተናዊ የክፍል ውጭ እንቅስቃሴ ለመማርና እራሣቸውን ብቁ መምህር አድርገው ለማውጣት እያደረጉት ያለው ጥረት ጠንካራና ውጤታማ መሆኑን ከተጠኞዎች የተገኘው መረጃ አመልክቷል።

ሠንጠረዥ 5፡እጩ መምህራንና የትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር ያላቸው ግንኙነት

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 9 | አንተ/አንቺ ከትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ሠራተኞች የሚሠጥህን/ሽን/ ተልእኮ ለመፈፀም ያለህ/ሽ/ ተነሣሽነት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 17 | 53.1 | 41 | 68.3 | 58 | 63.0 |
| | | ጥሩ | 8 | 25.0 | 14 | 23.3 | 22 | 23.9 |
| | | መካከለኛ | 5 | 15.6 | 4 | 6.7 | 9 | 9.8 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | 1 | 1.7 | 2 | 2.2 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | - | - | 1 | 1.1 |
| 10 | የአስተዳደር ሠራተኞች ለእጩ መምህራን ያላቸው ትብብር ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 8 | 25.0 | 20 | 33.3 | 28 | 30.4 |
| | | ጥሩ | 11 | 34.4 | 19 | 31.7 | 30 | 32.6 |
| | | መካከለኛ | 7 | 21.9 | 14 | 23.3 | 21 | 22.8 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 4 | 6.6 | 6 | 6.5 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 4 | 12.5 | 3 | 5.0 | 7 | 7.6 |

የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሃ-ግብር ተግባራዊ እየሆነባቸው ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ለእጩ መምህራን ተግባራዊ ስልጠና እያደረገው ያለውን እገዛና እጩ መምህራኑም ከትምህርት ቤቶች አስተዳደር ጋር ፈጥረውት ያለውን መስተጋብር ለማወቅ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተጠኞዎች የሠጡት ምላሽ ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ተተንትኗል።

ከተጠኝዎች በተገኘው መረጃ መሠረትም እጩ መምህራን፣ የአስተዳድር ሠራተኞች ለሚሠጡዋቸው ትእዛዝና መመሪያ ያላቸውን አቀባበል ለመለካት የቀረበውን ጥያቄ ከጠቅላላው ተጠኝዎች መካከል 63.0% በጣም ጥሩ፣ 23.9% ጥሩ፣ 9.8% መካከለኛ፣ 2.2% ዝቅተኛ፣ 1.1% በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሠዋል፡፡ ውጤቱ ከአፈፃፀም ቅርበቱ አንፃር ሲታይ 86.9% ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ያሉ ሲሆን ዝቅተኛና በጣም ዝቀተኛ ብለው የመለሱት ደግሞ 3.3% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 9.8% መካከለኛ ብለው መልሠዋል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት መልሶች የሚያረጋግጡት እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የሚሰጣቸውን ተግባር ለመፈጸም ያላቸው ፈቃደኝነት በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡

የአስተዳድር ሠራተኞች ለእጩ መምህራን ተልእኮ መሣካት እያደረጉት ያለውን ትብብር ለማወቅ ለተዘጋጀው ጥያቄ ደግሞ ከጠቅላላው ተጠኝዎች መካከል 30.4% በጣም ጥሩ፣ 32.6% ጥሩ፣ 22.8% መካከለኛ፣ 6.5% ዝቅተኛ፣ 7.6% በጣም ዝቅተኛ በማለት ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች 63.0% ሲሆኑ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ ብለው የመለሱት ደግሞ 14.1% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 22.8% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡ ከነዚህ ምላሾች የምንረዳው ደግሞ ምንም እንኳን የተገኘው ውጤት በአመዛኙ መልካም ነገሮችን ቢያመለክትም በአስተዳደር ሰራተኞችና በእጩ መምህራን መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማዳበር መሰራት ያለባቸው ቀሪ ተግባራት ያሉ መሆኑን ነው፡፡

በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተውም በመጠይቁ ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ለምሳሌ ደፈረ የተባለው ተጠኚ ሁኔታውን በተመለከተ ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው ምላሽ

> *እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲወጡ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ትምህርት ቤቶች ለሰልጣኞች ያላቸውን ግዴየለሽነት ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የፕራክቲከም ኮሚቴ አዋቅሮ ለሰልጣኞች የሚመች የስልጠና መርሃ ግብር ማዘጋጀት አለበት፡፡ (ታህሳስ 8/2003 ዓ.ም)*

በማለት ከትምህርት ቤቶች አስተዳደር አኳያ በትኩረት ሊታዩ የሚገባቸውና መስተካከል ያለባቸው ተግባራት እንዳሉ አመልክቷል።

በምልከታ የተገኘው መረጃም ቢሆን የእጩ መምህራኑን ተልእኮ ከፖሊስ ማስፈጸም አኳያ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተቀበለው ቢሆንም በተወሰኑት ትምህርትቤቶች ዘንድ ብዙም ትኩረት እንዳልተሰጠው አመልካች ሁኔታዎች ታይተዋል።

በአጠቃላይ ከተጠኚዎች በሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰበው መረጃ ሲተነተን በእጩ መምህራንና ለተግባራዊ ስልጠና በተሠማሩባቸው ትምህርት ቤቶች አስተዳደር መካከል ያለው ግንኙነትና ኃላፊነትን የመወጣት እንቅስቃሴ በአመዛኙ ጥሩ ቢሆንም ለተሻለ ውጤት መገኘት ሊስተካከሉ የሚገባቸው ተግባራት ያሉ መሆኑን መረጃው አረጋግጧል።

ሠንጠረዥ 6፡ የእጩ መምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 11 | አንተ/አንቺ በምታከናውነው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባር በአጠቃላይ ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ጋር ያለህን/ሽን/ ግንኙነት እንዴት ታየዋለህ /ታይዋለሽ/? | በ/ጥሩ | 12 | 37.5 | 29 | 48.3 | 41 | 44.6 |
| | | ጥሩ | 13 | 40.6 | 23 | 38.3 | 36 | 39.1 |
| | | መካከለኛ | 4 | 12.5 | 6 | 10.0 | 10 | 10.9 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 2 | 3.3 | 4 | 4.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | - | - | 1 | 1.1 |
| 12 | በምታስተምርበት/ሪበት/የማስተማር ልምምድ በምታደርግበት/ጊበት/ ክፍል ውስጥ ካሉት ተማሪዎች ጋር ያለህ/ሽ/ ግንኙነት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 13 | 40.6 | 37 | 61.7 | 50 | 54.4 |
| | | ጥሩ | 15 | 46.9 | 16 | 26.7 | 31 | 33.7 |
| | | መካከለኛ | 1 | 3.1 | 5 | 8.3 | 6 | 6.5 |
| | | ዝቅተኛ | 3 | 9.4 | 2 | 3.3 | 5 | 5.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 13 | የምታስተምራቸው /ሪያቸው/ ተማሪዎች ለአንተ /አንቺ/ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 9 | 28.1 | 27 | 45.0 | 36 | 39.1 |
| | | ጥሩ | 16 | 50.0 | 23 | 38.3 | 39 | 42.4 |
| | | መካከለኛ | 6 | 18.8 | 9 | 15.0 | 15 | 16.3 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | 1 | 1.7 | 2 | 2.2 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

ከላይ በአሃዝ በተተነተኑት ሦስት ጥያቄዎች ከተጠኝዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በሚከናወንባቸው ትምህርት ቤቶች ያሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና እጩ መምህራን ያላቸውን ግንኙነት ለሚፈትሸው ጥያቄ ተጠኝዎች 44.6% በጣም ጥሩ፣ 39.1% ጥሩ፣ 10.9% መካከለኛ፣ 4.4% ዝቅተኛ፣ 1.1% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡

ከተጠኝዎች የተገኘው መረጃ የእጩ መምህራኑንና የተማሪዎችን ግንኙነት በሚያሣይ መልኩ ሲቀናጅ ደግሞ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በአጠቃላይ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለሚመጡ እጩ መምህራን ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የቀረበውን ጥያቄ ተጠኝዎች 83.7 በጣም ጥሩና ጥሩ፣ 5.5% ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ፣ 10.9% ደግሞ መካከለኛ ብለው መልስ ሰጥተውበታል። በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለእጩ መምህራን ያለቸው አመለካከትና ከበሬታ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረጃው አሳይቷል።

እጩ መምህራን ለማስተማር ልምምድ የሚገቡት በተወሠኑ ክፍሎች ብቻ በመሆኑ ከነዚህ በቀጥታ በመማር ማስተማሩ ተግባር ከሚያገኟቸው ተማሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ሊመስል ይችላል? የሚለውን መረጃ ለማግኘት በቀረበው ጥያቄ ላይም ከጠቅላላ ተጠኝዎች 54.4% በጣም ጥሩ፣ 37.7% ጥሩ፣ 6.5% መካከለኛ፣ 5.4% ዝቅተኛ ብለው ምላሽ ሲሰጡ በጣም ዝቅተኛ የሚለውን አማራጭ መልስ የመረጠ ተጠኝ ግን የለም።

እያንዳንዱ እጩ መምህር በቀጥታ የመማር ማስተማር ተግባር ከሚያገኛቸው ተማሪዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያመለክት ለተዘጋጀው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ሲሰባሰብ 88.1% በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ 5.4% ተጠኝዎች ደግሞ ዝቅተኛ ብለው መልሠዋል። በጣም ዝቅተኛ የሚለው አማራጭ ግን በተጠኝዎች አልተመረጠም። ቀሪዎቹ 6.5% ደግሞ መካከለኛ የሚለውን አማራጭ ተጠቅመዋል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው ለልምምድ በተሰማሩት እጩ

መምህራንና በመደበኛ ተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ያለ መሆኑን ነው።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ከእጩ መምህራን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የክፍል ተማሪዎች ለእጩ መምህራን ያላቸውን ግምትና አመለካከት በእጩ መምህራኑ አስተያየት ለመለካት በቀረበው ጥያቄ ላይ ደግሞ ተጠኝዎች 39.1% በጣም ጥሩ፣ 42.4% ጥሩ፣ 16.3% መካከለኛ፣ 2.2% ዝቅተኛ ብለው ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ የሚለውን አማራጭ አልተጠቀሙበትም።

ተማሪዎች ለእያንዳንዱ እጩ መምህር ያላቸውን አመለካከት እንዲጠቁም ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ሲጠቃለል ደግሞ 81.5% ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ምላሽ ሲሠጡ 16.3% መካከለኛ፣ 2.2% ደግሞ ዝቅተኛ ሲሉ በጣም ዝቅተኛ የሚለው አማራጭ ግን አልተነካም። ከዚህ ትንታኔ ማጠቃለል የሚቻለው እጩ መምህራን የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉባቸው ክፍሎች ካሉ ተማሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን ነው።

ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የሚያመለክቱት ደግሞ የእጩ መምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት ገና ወደፊት ሊስተካከል የሚገባው ተግባር ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ታገለ የተባለው ተጠኚ ሲገልጽ ‹‹በተማሪዎችና በእጩ መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት የከፋ ገጽታ ባይታይበትም እጩ መምህራን ወደ ተማሪዎች ቀርበው ትብብር ሲያደርጉ አይታይም፡፡›› (ታህሳስ 5/2003 ዓ.ም) በማለት ገልጾታል፡፡

ስለሆነም የመጠይቁን ጥያቄዎች ተከትለው በተሠጡ ምላሾች ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በእጩ መምህራንና በመጀመሪያ ደረጃ መደበኛ ተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ ቢሆንም ለተሻለ ውጤት መስተካከል የሚገባቸው ነገሮች ያሉ መሆኑን ደግሞ የቃለ መጠይቁ ምላሽ አመልክቷል።

ሠንጠረዥ 7፡አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚያደርጉትን እገዛ

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች ቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 14 | የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን መርሃ-ግብር በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ለአንተ/አንቺ የተመደበልህ/ሽ/ አጋር መምህር እያደረገልህ/ሽ/ ያለው እገዛ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 20 | 62.5 | 45 | 75.0 | 65 | 70.7 |
| | | ጥሩ | 8 | 25.0 | 9 | 15.0 | 17 | 18.5 |
| | | መካከለኛ | 1 | 3.1 | 4 | 6.7 | 5 | 5.4 |
| | | ዝቅተኛ | 3 | 9.4 | 2 | 3.3 | 5 | 5.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 15 | አጋር መምህርህ/ሽ/ አንተ /አንቺ/ ለምታከናውናቸው /ኛቸው/ ተግባራት የሚሠጥህ ግብረ መልስ ያለው የገንቢነት ሚና ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 14 | 43.8 | 38 | 63.3 | 52 | 56.5 |
| | | ጥሩ | 13 | 40.6 | 17 | 28.3 | 30 | 32.6 |
| | | መካከለኛ | 3 | 9.4 | 3 | 5.0 | 6 | 6.5 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | 2 | 3.3 | 3 | 3.3 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 1 | 3.1 | - | - | 1 | 1.1 |

አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚያደርጉትን እገዛ ለመፈተሽ በቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች የተሠጠው የተጠኝዎች ምላሽ በአሃዝ ሲተነተን ውጤቱ ተቀራራቢ ነው፡፡ አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን እያደረጉት ያለውን እገዛ በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ እንደሚያሳየው ተጠኝዎች 70.7% በጣም ጥሩ፣ 18.5% ጥሩ፣ 5.4% መካከለኛ 5.4% ዝቅተኛ ብለው ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ የሚለው አማራጭ በተጠኝዎች አልተመረጠም፡፡ የተጠኝዎች ምላሽ ሲጠጋጋ ደግሞ 89.2% የሆኑት ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ 5.4% ደግሞ ዝቅተኛ ብለዋል፡፡ መካከለኛ የሚለውን አማራጭ መልስ የወሠዱት ደግሞ 5.4% ናቸው፡፡ ስለዚህ አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን እያደረጉት ያለው እገዛና ክትትል በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ብሎ መደምደም የሚያስችል መረጃ ተገኝቷል፡፡

እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው የሚያገኙትን ግብረ መልስ በተመለከተ የቀረበውን ጥያቄ ደግሞ 56.5% በጣም ጥሩ፣ 32.6% ጥሩ፣ 6.5% መካከለኛ፣ 3.3% ዝቅተኛ 1.1% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ የተጠኝዎችን ምላሽ እጩ

መምህራት ከአጋሮቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመመዘን በሚያስችል መልክ ብናየው ደግሞ 89.1% ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ብለው የመለሱት ደግሞ 4.4% ናቸው፡፡ መካከለኛ የሚለውን አማራጭ የመረጡት ተጠኝዎች ደግሞ 6.5% ናቸው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የተሰጡ መልሶች እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው ያገኙት ግብረ መልስ በስልጠናው ሂደት ውስጥ የገንቢነት ሚና ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃም ቢሆን ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ፡፡ መለስተኛ ችግሮች ያሉ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ለምሳሌ ተመስገን የተባለው ተጠኚ ሲገልጽ ‹‹በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ሁኔታ እንደአጠቃላይ ሲታይ ጥሩ ነው፡፡አልፎ አልፎ ግን መጠነኛ ግጭቶች ይከሰታሉ፡፡ እነዚህንም ለማስተካከል ተከታታይ ውይይቶችን እያካሄድን ነው፡፡›› (ታህሳስ 8/2003 ዓ.ም) በማለት አብራርቷል፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛ መምህርነት እያስተማሩ ያሉና እጩ መምህራን ለልምምድ ሲመደቡ እገዛና ክትትል በማድረግ በመጨረሻም የበኩላቸውን ውጤትና አስተያየት ሠጥተው የሚልኳቸው አጋር መምህራን ለተግባራዊ ስልጠና ከተመደቡት እጩ መምህራን ጋር ያላቸውን ግንኙነት መረጃ ለማግኘት የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች በተቀራራቢ ሁኔታ ተጠኝዎች ከ89.1% በላይ በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ምላሽ ሠጥተዋቸዋል፡፡ ይህም በእጩ መምህራኑና በአጋሮቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት የከፋ ችግር የሌለበት መሆኑን አመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 8፡እጩ መምህራን በተጓዳኝ ትምህርት ያላቸው ተሣትፎ

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 16 | በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሚከናወኑ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እያደረግህ/ሽ/ ያለኸው/ሽው/ ተሣትፎ ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 13 | 40.6 | 21 | 35.0 | 34 | 36.9 |
| | | ጥሩ | 12 | 37.5 | 27 | 45.0 | 39 | 42.4 |
| | | መካከለኛ | 5 | 15.6 | 8 | 13.3 | 13 | 14.1 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 1 | 1.7 | 3 | 3.3 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | 3 | 5.0 | 3 | 3.3 |
| 17 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በሚያቅዳቸው ትምህርት ቤቱን የማልማት ተግባራት እያደረግህ/ሽ/ ያለኸው/ሽው/ ተሣትፎ ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 9 | 28.1 | 22 | 36.7 | 31 | 33.7 |
| | | ጥሩ | 16 | 50.0 | 29 | 48.3 | 45 | 48.9 |
| | | መካከለኛ | 5 | 15.6 | 6 | 10.0 | 11 | 11.9 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 2 | 3.3 | 4 | 4.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | 1 | 1.7 | 1 | 1.1 |

በሠንጠረዥ 8 ላይ የሠፈረው አሃዝ በዝርዝር ሲታይ እጩ መምህራን በትምህርት ቤቱ የተጓዳኝ ተግባራት ማለትም በልዩ ልዩ ክበባት ና የትምህርት ቤት ልማት ውስጥ ገብተው በመምራትና በመስራት ያላቸውን ተሣትፎ የሚለካ ነው፡፡ ተጓዳኝ ትምህርትን የሚመለከተውን ጥያቄ 36.9% በጣም ጥሩ፣ 42.4% ጥሩ፣ 14.1% መካከለኛ 3.3% ዝቅተኛ 3.3% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሚል መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይህም ማለት 79.3% በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ 6.6% ደግሞ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ያሉ ናቸው፡፡ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡት ደግሞ 14.1% ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው እጩ መምህራን በተጓዳኝ የትምህርት ተግባራት ያላቸው ተሳትፎ ከአጠቃላይ ተሳትፎ አንጻር በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡

እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ቆይታቸው የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በሚያቅዳቸው የትምህርት ቤት ልማት ተግባራት ለመሣተፍ ያላቸውን ፍላጐት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ 33.7% በጣም ጥሩ፣ 48.9% ጥሩ፣ 11.9% መካከለኛ፣ 4.4% ዝቅተኛ፣ 1.1% በጣም ዝቅተኛ ብለዋል፡፡ ይህ ውጤት የሚያመለክተው 82.6% በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል አመለካከት ያላቸው መሆኑን ሲሆን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚሉት ደግሞ 5.5%

መሆናቸውን ነው። ስለዚህ እጩ መምህራን በትምህርት ቤቶች የልማት እንቅስቃሴ ለመሳተፍና ከዚህም ለመማር ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ብዙዎቹ እጩ መምህራን በክበባትና በትምህርት ቤት ልማት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኞች መሆናቸውን ነው። የምልከታ መረጃውም ቢሆን ተመሳሳይ ሁኔታዎችን የሚያመለክት ነው።

ስለሆነም እጩ መምህራት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለአንድ ወሠነ ትምህርት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምድ ሲያደርጉ በተጓዳኝ ትምህርት /ክበባትና/ በትምህርት ቤት ልማት እቅዶች አፈፃፀም ላይ ያላቸው ተሣትፎ ጥሩ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 9፡ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለስልጠና ያሠማራቸውን እጩ መምህራን የሚከታተልበት ሁኔታ

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 18 | የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ እያደረገ ያለው እገዛ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 5 | 15.6 | 13 | 21.7 | 18 | 19.6 |
| | | ጥሩ | 16 | 50.0 | 25 | 41.7 | 41 | 44.6 |
| | | መካከለኛ | 7 | 21.9 | 13 | 21.7 | 20 | 21.7 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 7 | 11.7 | 9 | 9.8 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 2 | 3.3 | 4 | 4.4 |
| 19 | ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን አጠቃላይ እንቅስቃሴ እየተከታተለ ያለበት ስልት በአንተ /አንቺ/ እይታ እንዴት ይገመገማል? | በ/ጥሩ | 5 | 15.6 | 14 | 23.3 | 19 | 20.7 |
| | | ጥሩ | 15 | 46.9 | 17 | 28.3 | 32 | 34.8 |
| | | መካከለኛ | 4 | 12.5 | 17 | 28.3 | 21 | 22.8 |
| | | ዝቅተኛ | 5 | 15.6 | 6 | 10.0 | 11 | 11.9 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 3 | 9.4 | 6 | 10.0 | 9 | 9.8 |

መሠረታዊ ተግባሩ መምህራንን ማሠልጠን የሆነው የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሠማራቸውን እጩ መምህራን እያደረገላቸው ያለውን ክትትልና እገዛ

ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኝዎች 19.6% በጣም ጥሩ፣ 44.6% ጥሩ፣ 21.7% መካከለኛ፣ 9.8% ዝቅተኛ 4.4% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ይህ አሃዝ ሲጠቃለል ደግሞ በጣም ጥሩና ጥሩ ያሉት ተጠኝዎች 64.2% ሲሆኑ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ብለው የመለሱት ደግሞ 14.2% ናቸው፡፡ 21.7% ተጠኝዎች ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ ለስልጠና ላሰማራቸው እጩ መምህራን እያደረገ ያለው እገዛ አናሳ መሆኑን እና በጥንቃቄ ታስቦበት ሊስተካከል የሚገባው ችግር ያለ መሆኑን መረጃው አመልክቷል፡፡

የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እየተከታተለበት ያለውን ስልት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ 20.7% በጣም ጥሩ፣ 34.8% ጥሩ፣ 22.8% መካከለኛ፣ 11.9% ዝቅተኛ 9.8% ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ይህም ወደ ተጠቃለለ የትኩረት ነጥብ ሲሠበሰብ 55.5% በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 21.7% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 22.8 ደግሞ መካከለኛ ብለው መልሠዋል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ ለእጩ መምህራኑ እየሰጠ ያለው ድጋፍና ክትትል ክፍተት ያለበት መሆኑን መረጃው አረጋግጧል፡፡

በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ስንመለከተው ደግሞ በመጠይቅ መረጃ ሲፈተሽ የታየውን ደካማ ጎን አጎልቶ የሚያወጣ ነው፡፡ ለምሳሌ ተዋበ የተባለው ተጠኚ ‹‹የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እንዴት ይከታተሉታል?›› ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ

> *ትልቁ ችግር ከዚህ ላይ ነው፡፡ አሰልጣኝ ኮሌጆች ሰልጣኞችን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት በሴሚስተሩ መጨረሻ አካባቢ ለአንድ ወይም ሁለት ቀን ብቅ ብለው ውጤታቸውን ከመሙላት በስተቀር ሰልጣኞች ስልጠናውን እንዴት እያስኬዱት እንደሆነ በመርሃ ግብር የታቀፈ ክትትል አያደርጉም፡፡ በመሆኑም በማጠቃለያ ግምገማ የመምህራኑን ስልጠና ለውጥ መለካትና ድክመትና ጥንካሬውን መለየት ያስችላል ብዬ አላምንም፡፡ (ታህሳስ 6/2003ዓ.ም)* በማለት

አብራርቶታል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ነጥብ ላይ ተጠኝዎች የሠጡት ምላሽ እስከአሁን ሲተነተኑ ከቆዩት ሃሳቦች ጋር ሲነፃፀር ለየት ባለ ሁኔታ 44.5% የሚሆኑ ተጠኝዎች መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ ምላሾችን መስጠታቸው አሠልጣኝ የመምህራን ኮሌጁ ሠልጣኞችን የሚከታተልበት ሁኔታ ተገቢ አለመሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ መፈታት ያለባቸው ችግሮች ያሉ መሆናቸውን መረጃው አሳይቷል፡፡

### ሠንጠረዥ 10፡የመምህራን ኮሌጁና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመርሃ ግብር መጠጣም

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 20 | ለስልጠና የተሠማራህበት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ትግበራ ያዘጋጀው መርሃ-ግብር ከማሠልጠኛ ኮሌጁ የአፈጻጸም መርሀ ግብር ጋር ያለው ትስስር እንዴት ነው? | በ/ጥሩ | 7 | 21.9 | 18 | 30.0 | 25 | 27.2 |
| | | ጥሩ | 18 | 56.3 | 29 | 48.3 | 47 | 51.1 |
| | | መካከለኛ | 3 | 9.4 | 7 | 11.7 | 10 | 10.9 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 3 | 5.0 | 5 | 5.4 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 2 | 6.3 | 3 | 5.0 | 5 | 5.4 |

እጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለማድረግ የተሠማሩባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መርሃ-ግብር ከመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ መርሃ-ግብር ጋር ያለውን ትስስር ለመለካት በቀረበው ጥያቄ ላይ 27.2% በጣም ጥሩ፣ 51.1% ጥሩ፣ 10.9% መካከለኛ፣ 5.4% ዝቅተኛ፣ 5.4% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ተሠጥቶበታል፡፡

ይህ መረጃ ተጠቃልሎ ሲታይ በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች 78.3% ሲሆኑ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 10.8% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 10.9% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡ ሁኔታው ከእጩ መምህራኑ ምላሽ አንጻር ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በመምህራን ማሰልጠኛ

ኮሌጆች መካከል የመርሃ-ግብር ስምምነት ያለ መሆኑን መረጃው ቢያመለክትም፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ደግሞመርሃ ግበሩ ባይደናቀፍም የሚከናወነው ተግበር ጫና ያልተለየው መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ሰለሞን የተባለው ተጠኚ የሁለቱን ተቋማት በተመለከተ የሰጠው ምላሽ

> *የእጩ መምህራኑ ስልጠና በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ጫና መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡... ነገር ግን ይህንን ጫና ተሸክመን ስልጠናውን ማካሄድ ካልቻልን ተተኪ ሀይላትን የማፍራት አላማችን አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ብለን ስለምናምን ነው ሰልጣኞችን ተቀብለን ለማስተናገድ የፈቀድነው፡፡ ( ሀዳር 24/2003ዓ.ም)*

በማለት ገልጸታል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብርና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያዘጋጁት የአፈጻጸም መርሀ ግብር ስሙሙነት ቢታይባቸውም በተወሰነ መልኩ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተግባር ላይ ጫና የሚፈጥር መሆኑን መረጃው አመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ ከእጩ መምህራን በ10 መሠረታዊ ነጥቦች ላይ ባተኮሩ 20 የጽሁፍ ጥያቄዎች፣10 የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችና በምልከታ አማካይነት የተሠበሠቡት መረጃዎች ከላይ በዝርዝር እያየነው የመጣውን የተልእኮ አፈፃፀም ብቃት ቢያመለክትም፣ በትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባር ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑት አጋር መምህራን ያላቸውን አመለካከትም መፈተሽ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ለአጋር መምህራን የተሠራጨው መጠይቅ የያዛቸው 20 ጥያቄዎች በ9 መሠረታዊ ነጥቦች በማጠቃለል ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.2 ለአጋር መምህራን ከቀረበው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

እጩ መምህራን የሚያደርጉትን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በቅርበት እየተከታተሉ እንዲያግዙ፣ እንዲመሩና በመጨረሻም እንዲገመግሙ ኃላፊነት የተጣለባቸው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛነት የሚያስተምሩ አጋር መምህራን የበኩላቸውን መረጃ እንዲሠጡ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ ለአጋር መምህራኑ የተዘጋጀ መጠይቅ 20 ጥያቄዎችን ከአምስት

አማራጭ መልሶች ጋር ያካተተ ነው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ትኩረት ከሚሠጡበት መሠረታዊ ነጥብ አንፃር ሲታዩ ወደ ዘጠኝ ተጠቃልለው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ከዘጠኙ መሠረታዊ ነጥቦች አንፃር የተገኘው መረጃ ቀጥሎ ባሉት ዘጠኝ ሠንጠረዦች ተተንትኗል፡፡

ሠንጠረዥ 11፡በመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን መርሀ ግብር መጣጣም

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተመደቡት እጩ መምህራን ይዘውት የመጡት የአፈጻጸም መርሀ ግብር ከመደበኛ ትምህርት ቤቱ መርሀ ግብር ጋር ያለው መጣጣም እንዴት ይገመግሙል? | በ/ጥሩ | 11 | 44.0 | 10 | 27.0 | 21 | 33.9 |
| | | ጥሩ | 12 | 48.0 | 13 | 35.1 | 25 | 40.3 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8.0 | 11 | 29.7 | 13 | 20.9 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | 3 | 8.1 | 3 | 4.8 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

ከአጋር መምህራን በተሠበሠበው መረጃ መሠረት የእጩ መምህራን የኮሌጅ መርሀ ግብር ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መርሀ ግብር ጋር ያለውን መጣጣም ተጠኝዎች 33.9% በጣም ጥሩ፣ 40.3% ጥሩ፣ 20.9% መካከለኛ፣ 4.8% ዝቅተኛ፣ ብለው ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ የሚለውን አማራጭ ግን አልተጠቀሙበትም፡፡ የተጠኝዎች ምላሽ ሲጠቃለል 74.2% በጣም ጥሩና ጥሩ ሲሉ 4.8% የሆኑት ደግሞ ዝቅተኛ ብለዋል፡፡ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡት ደግሞ 20.9% ናቸው፡፡

በመሆኑም ተጠኝዎች በመልሣቸው እንዳረጋገጡት እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሠማሩ የሚሠጣቸው የአፈጻጸም መርሀ ግብር ከሚሄዱባቸው ትምህርት ቤቶች መደበኛ መርሀ ግብር ጋር ያለው መጣጣም መጥፎ በሚባለበት ደረጃ ላይ ባይሆንም አሳሳቢና ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ያሉ መሆኑን መረጃው አሳይቷል፡፡ ይህን

ሁኔታ ለእጩ መምህራን ከቀረበው መጠይቅና ለአስተዳደር ሰራተኞች በቀረበው ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ሲፈተሽም የስልጠናው መርሀ ግብር በመደበኛ ትምህርት ቤቶች መርሀ ግብር ላይ ጫና ሊፈጥር እንደሚችል አመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 12፡ በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እጩ መምህራን እያደረጉት ያለው ራስ አገዝ ጥረት

| ተ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 2 | እጩ መምህራን ከአጠቃላዩ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ለመማር ያላቸው ስሜት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 12 | 48.0 | 8 | 21.6 | 20 | 32.3 |
| | | ጥሩ | 9 | 36.0 | 22 | 59.5 | 31 | 50.0 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8.0 | 4 | 10.8 | 6 | 9.7 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 8.0 | 3 | 8.1 | 5 | 8.1 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 3 | እጩ መምህራን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት ጋር ራሣቸውን ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 11 | 44.0 | 8 | 21.6 | 19 | 30.7 |
| | | ጥሩ | 12 | 48.0 | 16 | 43.2 | 28 | 45.2 |
| | | መካከለኛ | 1 | 4.0 | 9 | 24.3 | 10 | 16.1 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 4 | 10.8 | 5 | 8.1 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በመሣተፍ ላይ ያሉት እጩ መምህራን ራሣቸውን ብቁ መምህር አድርገው ለመቅረጽ እያደረጉት ያለው ራስ አገዝ ጥረት በአጋር መምህሮቻቸው እይታ ሲፈተሽ ቀጥሎ ያለው መረጃ ተገኝቷል፡፡

እጩ መምህራን ከአጠቃላይ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ለመማር እያሣዩት ያለውን ስሜት በተመለከተ ለተጠኝ አጋር መምህራን የቀረበው ጥያቄ 32.3% በጣም ጥሩ፣ 50.0% ጥሩ፣ 9.7% መካከለኛ፣ 8.1% ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሲያገኝ በጣም ዝቅተኛ የሚለው አማራጭ አልተወሠደም፡፡ መረጃው ለሚዛን በሚያመች መልክ ሲጠቃለል ደግሞ በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት 82.3% ሲሆኑ፣ ዝቅተኛ የሚል መልስ የሠጡት ደግሞ 8.1% ናቸው፡፡ ከተጠኝዎች መካከል 9.7% የሚሆኑት ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡

ከዚህ የመረጃ ትንታኔ ለመረዳት የሚቻለው እጩ መምህራን በትምህርት ቤት

ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እራሳቸውን ብቁ መምህር ለማድረግ እየፈጸሙት ያለው እራስ አገዝ ጥረት በአጥ.ጋቢ. ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡

እጩ መምህራን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት ጋር ራሣቸውን ለማለማመድ እያደረጉት ያለውን ጥረት በተመለከተ የቀረበውን ጥያቄ ደግሞ 37.7% በጣም ጥሩ፣ 45.2% ጥሩ፣ 16.1% መካከለኛ፣ 8.1% ዝቅተኛ፣ ሲሉ በጣም ዝቅተኛ የሚለው አማራጭ አልተመለሰም፡፡ መረጃው ሲጠቃለል ደግሞ 82.9% በጣም ጥሩና ጥሩ ሲሉ 8.1% ዝቅተኛ ብለዋል መካከለኛ ያሉት ደግሞ 16.1% ናቸው፡፡ ይህም ሁኔታ እጩ መምህራን እራሳቸውን ከትምህርት ቤቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ጋር ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ መረጃው የሚያመለክተው እጩ መምህራን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመጡበትን ዓላማ ለማሣካት እያደረጉት ያለው ራስ አገዝ ጥረት በአጋር መምህሮቻቸው እይታ በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 13፡ እጩ መምህራን ከሌሎች መደበኛ መምህራንና ከአጋር መምህሮቻቸው ጋር ያላቸው ትብብርና ያመጡት ሙያዊ መሻሻል

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 4 | እጩ መምህራን የአጋር መምህሮቻቸውን ምክርና እገዛ ተቀብለው ድክመቶቻቸውን ለማስተካከል የሚያደርጉትን ጥረት እንዴት ያዩታል? | በ/ጥሩ | 9 | 36.0 | 13 | 35.1 | 22 | 35.5 |
| | | ጥሩ | 14 | 56.0 | 16 | 43.2 | 30 | 48.4 |
| | | መካከለኛ | 1 | 4.0 | 6 | 16.2 | 7 | 11.3 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 2 | 5.4 | 3 | 4.8 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 5 | እጩ መምህራን ከሌሎች መምህራን ጋር ተጠግተውና ተባብረው ለመስራት የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 5 | 20.0 | 8 | 21.6 | 13 | 20.9 |
| | | ጥሩ | 17 | 68.0 | 16 | 43.2 | 33 | 53.2 |
| | | መካከለኛ | 3 | 12.0 | 12 | 32.4 | 15 | 24.2 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | 1 | 2.7 | 1 | 1.6 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

እጩ መምህራን ከሌሎች መደበኛ መምህራንና ከአጋር መምህሮቻቸው ጋር ተቀራርበውና ተስማምተው በመስራት ያመጡትን ሙያዊ መሻሻል ለማወቅ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች ተጠኝዎች ምላሽ ሠጥተውባቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት እጩ መምህራን የአጋር መምህሮቻቸውን ምክርና እገዛ ተቀብለው ድክመቶቻቸውን ለማስተካከል የሚያደርጉትን ጥረት 35.5% በጣም ጥሩ፣ 48.4% ጥሩ፣ 11.3% መካከለኛ፣ 4.8% ዝቅተኛ፣ ብለው ምላሽ ሲሰጡ በጣም ዝቅተኛ የሚለው አማራጭ አልተመረጠም፡፡

የተጠኝዎች ምላሽ ተሠባስቦ ሲታይ 83.9% ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ 4.8% ደግሞ ዝቅተኛ ብለው የመለሱ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 11.3% ተጠኝዎች ደግሞ መካከለኛ ብለው መልሠዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ በመነሳት እጩ መምህራን የአጋር መምህሮቻቸውን ምክርና እገዛ ተቀብለው በስራ ላይ ለማዋል ያለቸው ፈቃደኝነት በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን መረጃው አመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል እጩ መምህራን ከሌሎች የትምህርት ቤቱ መምህራን ጋር ተጣግተውና ተባብረው ለመስራት ያላቸውን ተነሣሽነት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ 20.9% በጣም ጥሩ፣ 53.2% ጥሩ፣ 24.2% መካከለኛ 1.6% ዝቅተኛ ብለው ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ይህ መረጃ ደግሞ ለማመዛዘን በሚያመች መልኩ ሲሠባሰብ 74.1% በጣም ጥሩና ጥሩ ሲሉ፤ ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 1.6% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 24.2% ተጠኝዎች ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም እጩ መምህራን ከሌሎች የትምህርት ቤቱ መምህራን ጋር ተጣግተውና ተባብረው ለመስራት የሚያሳዩት ተነሳሽነት የሚቀረው ነገር ያለ ቢሆንም በአጠቃላይ ገጽታው ግን በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በነዚህ መረጃዎች መሠረት በእጩ መምህራን፣ በአጋር መምህራንና ሌሎች የትምህርት ቤቱ መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት በአጠቃላይ ሲታይ መልካም እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 14፡የእጩ መምህራን ንድፈ ሃሣብን ወደ ተግባር የመለወጥ አቅም

| ተራ ቁ. | ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 6 | እጩ መምህራን ከማሠልጠኛ ኮሌጁ የተማሩትን ንድፈ ሃሣባዊ እውቀትና ክህሎት በተግባር ለመሞከር የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል? | በጣም ጥሩ | 5 | 20.0 | 8 | 21.6 | 13 | 20.9 |
| | | ጥሩ | 15 | 40.5 | 13 | 35.1 | 28 | 45.2 |
| | | መካከለኛ | 4 | 16.0 | 13 | 35.1 | 17 | 27.4 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 3 | 8.1 | 4 | 6.5 |
| | | በጣም ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመሠማራታቸው በፊት በነበራቸው የኮሌጅ ቆይታ በንድፈ ሃሣባዊ አቀራረብ የተማሩዋቸው የመምህርነት ሙያዊ ተግባራት አሉ፡፡ አሁን የተሠማሩበት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድም መሠረታዊ አላማው ይህን ንድፈ ሃሣባዊ እውቀታቸውን በተግባር እንዲለማመዱበት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ 20.9% በጣም ጥሩ፣ 45.2% ጥሩ፣ 27.4% መካከለኛ፣ 6.5% ዝቅተኛ፣ በማለት ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ ያለ ግን የለም፡፡ መረጃው የሚያመለክተውን መሠረታዊ ነጥብ አጠቃልሎ ለመመዘን 66.1% በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ ያገኘ ሲሆን 6.5% ተጠኝዎች ደግሞ ዝቅተኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 27.4% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥያቄ ላይ የተገኘው መረጃ እጩ መምህራን ንድፈ ሃሣባዊ ትምህርታቸውን በተግባር በማዋል ሙያዊ ክህሎት ለመቅሠም እያደረጉት ያለው ጥረት በአጋሮቻቸው አተያይ መጥፎ ነው ባይባልም አሳሳቢ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር መፈተሽ ያለባቸው ተግባራት እንዳሉ መረጃው አረጋግጧል፡፡

ሠንጠረዥ 15፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ለእጩ መምህራን ተግባራዊ ስልጠና የሠጠው ትኩረት

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 7 | የትምህርት ቤቱ አስተዳድር ለእጩ መምህራን ስልጠና መሣካት እየፈጠረ ያለው ምቹ ሁኔታ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 19 | 76.0 | 13 | 35.1 | 32 | 51.6 |
| | | ጥሩ | 6 | 24.0 | 18 | 48.7 | 24 | 38.7 |
| | | መካከለኛ | - | - | 5 | 13.5 | 5 | 8.1 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | 1 | 2.7 | 1 | 1.6 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 8 | የትምህርት ቤቱ አስተዳድር የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባራዊ አፈፃፀም ለመከታተል የሚያደርገው ጥረት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 17 | 68.0 | 6 | 16.2 | 23 | 37.1 |
| | | ጥሩ | 6 | 24.0 | 17 | 45.9 | 23 | 37.1 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8 | 9 | 24.3 | 11 | 17.7 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | 5 | 13.5 | 5 | 8.1 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከማሣካት አንፃር የተሠጣቸው የራሣቸው ተግባርና ኃላፊነት አላቸው፡፡ በመሆኑም ይህን ተልእኳቸውን እየተወጡበት ያለውን ብቃት ለመመዘን ለተዘጋጁት ጥያቄዎች በተጠኝነት የተመረጡት አጋር መምህራን ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ከምላሹ በተገኘው መረጃ መሠረት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለስልጠናው መሣካት እየፈጠረ ያለውን ምቹ ሁኔታ በተመለከተ የቀረበውን ጥያቄ 51.6% በጣም ጥሩ፣ 38.7% ጥሩ፣ 8.1% መካከለኛ፣ 1.6% ዝቅተኛ ብለው ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ ብሎ የመለሰ ተጠኝ የለም፡፡ የተጠኝዎች ምላሽ ሲጠቃለል በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች 90.3% ሲሆኑ ዝቅተኛ ያሉት ግን 1.6% ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 8.1% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ መሆናቸውን መረጃው አረጋግጧል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የመጀረመሪያ ደረጃ

ትምህርት ቤቶች አስተዳድር ለእጩ መምህራን ተግባራዊ ስልጠና ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡

የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባራዊ አፈፃፀም ለመከታተል የሚያደርገውን ጥረት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ 37.1% በጣም ጥሩ፣ በተመሣሣይ ሁኔታ 37.1% ጥሩ፣ 17.7% መካከለኛ 8.1% ዝቅተኛ ብለው ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ ያለ የለም፡፡ ይህን መረጃ ስናጠቃልለው ደግሞ በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ ያላቸው 74.2% ሲሆኑ ዝቅተኛ የሚል ምላሽ የሠጡት ደግሞ 8.1% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 17.7% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ቤቶች አስተዳደር የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር መዘርጋት ብቻ ሳይሆን የክትትል ስልቱም በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን መረጃው አመልክቷል፡፡

ከልምከታ የተገኘውም መረጃ ይህን ሁኔታ የሚያጠናክር ነው፡፡ በአራቱም ትምህርት ቤቶች በተደረገው ምልከታ ለእጩ መምህራን የሰአት መቆጣጠሪያ ደብተር ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡‹‹ የፕራክቲክም ኮሚቴ ›› የሚባል አካል ተደራጅቶ የእጩ መምህራኑን አጠቃላይ እንቅስቃሴ እንዲከታተል ተደርጓል፡፡ አጋር መምህራን ተመድበው እጩ መምህራኑን እንዲያግዙ መርሀ ተሰጥቷል፡፡ ለእጩ መምህራኑ የተጓዳኝ ትምህርት መርሀ ግብር ተዘርግቶላቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራኑን ስልጠና በመርሀ ግብሩ ውስጥ አካትቶ እየሰራበት መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የተሠበሰበው መረጃ የሚያመለክተው እውነታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባራዊ አፈፃፀም የበኩላቸውን ኃላፊነት ለመወጣት እያደረጉት ያለው ጥረት ጥሩ መሆኑን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 16፡አጋር መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ፕሮግራም የሠጡት ትኩረት

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 9 | እርስዎ በአጋር መምህርነትዎ የእጩ መምህራኑን ተልእኮ ለማሣካት የሚያከናውኑት የታቀደ ተግባር ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 14 | 56.0 | 9 | 24.3 | 23 | 37.1 |
| | | ጥሩ | 9 | 36.0 | 22 | 59.5 | 31 | 50.0 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8.0 | 6 | 16.2 | 8 | 12.9 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 10 | እጩ መምህራን በሚያደርጉት የተግባር ልምምድ ከሚሠሯቸው ስህተቶች እንዲማሩ ለማድረግ የዘረጉት የተጠናከረ ስልት ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 10 | 40.0 | 12 | 32.4 | 22 | 35.5 |
| | | ጥሩ | 12 | 48.0 | 17 | 45.9 | 29 | 46.8 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8.0 | 5 | 13.5 | 7 | 11.3 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 3 | 8.1 | 4 | 6.5 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በሚደረግባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለየትምህርት አይነቱ ባላቸው ቀረቤታና በግል ፈቃደኝነታቸው ላይ በማተኮር ለእጩ መምህራት አጋር መምህር ተመድቧል፡፡ የአገር መምህራን መሠረታዊ ተልእኮም እጩ መምህራኑን በማገዝ፣ በማበረታታት፣ በማረምና በማስተካከል ብቁ መምህር መሆን ይችሉ ዘንድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡ የነዚህ መምህራን ተግባራዊ አፈፃፀም ለአጠቃላዩ የተልእኮ አፈፃፀም ብቃት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። በመሆኑም ይህን የተመለከተ መረጃ ተሠብስቦበታል፡፡ የተሠበሠበው መረጃም እያንዳንዱ አጋር መምህር የተመደበለትን እጩ መምህር ተልእኮ ለማሣካት እያከናወነው ያለውን በእቅድ የታገዘ ተግባር በተመለከተ 37.1% በጣም ጥሩ፣ 50.0% ጥሩ፣ 12.9% መካከለኛ በማለት ምላሽ የሠጡ ሲሆን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል ግን የለም፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች 87.1% ሲሆኑ ቀሪዎቹ 12.9% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም አጋር መምህራን ለዚህ መርሀ-

ግብር መሣካት በእቅድ ላይ ተመስርተው ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑን የሚያረጋግጥ መረጃ ተገኝቷል፡፡

በሌላ መልኩ እጩ መምህራን ከስህተታቸው እንዲማሩ አጋር መምህራን የዘረጉትን ስልት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ 35.5% በጣም ጥሩ፣ 46.8% ጥሩ፣ 11.3% መካከለኛ፣ 6.5% ዝቅተኛ ሲሉ በጣም ዝቅተኛ ብሎ የመለሠ ግን የለም መረጃው ተጠቃሎ ሲታይ ደግሞ 82.3 በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 6.5% ደግሞ ዝቅተኛ ብለው መልሰዋል፡፡ ቀሪዎቹ 11.3% መካከለኛ ብለው የመለሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም አጋር መምህራን የእጩ መምህራኑን ጥረት ለማገዝ ያላቸው ፍላጎትና ድጋፍ በጥሩ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን መረጃው አመልክቷል፡፡

በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተውም በስራ መደራረብ ምክንያት ከሚፈጠር ምሬት ባሻገር እያንዳዱ አጋር መምህር እጩ መምህሩን ለማገዝና ልምድ ለማካፈል በጎ ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ተግባር ላይ የተሰበሰበው መረጃ አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን እየሰጡት ያለው ድጋፍና የትምህርትቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሰጡት ትኩረት በአጥጋቢ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን አሳይቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 17፡ እጩ መምህራን ለአጋር መምህራን ግብረ መልስ የሰጡት ትኩረት**

| የጥያቄው ተራ ቁ. | በመጠይቁ ላይ የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 11 | እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው የሚሠጣቸውን ግብረ መልስ (Feed back) ተቀብለው በተግባር ለማዋል ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 9 | 36.0 | 6 | 16.2 | 15 | 24.2 |
| | | ጥሩ | 13 | 52.0 | 24 | 64.9 | 37 | 59.7 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8.0 | 6 | 16.2 | 8 | 12.9 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 1 | 2.7 | 2 | 3.2 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 12 | እጩ መምህራን የተሠጣቸውን ግብረ መልስ ተቀብለው እራሣቸውን የሚያስተካክሉበት ፍጥነት እንዴት ይገመገማል? | በ/ጥሩ | 6 | 24.0 | 4 | 10.8 | 10 | 16.1 |
| | | ጥሩ | 12 | 48.0 | 20 | 54.1 | 32 | 51.6 |
| | | መካከለኛ | 6 | 24.0 | 9 | 24.3 | 15 | 24.2 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 4 | 10.8 | 5 | 8.1 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |

ከላይ የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች መሠረታዊ አላማ እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው ለሚሠጣቸው ግብረ መልስ (feedback) ያላቸውን የአቀባበል ብቃት መለካት ነው፡፡ በመሆኑም እጩ መምህራን የሚሠጣቸውን ግብረ መልስ ተቀብለው ወደ ተግባር ለመለወጥ ያላቸውን ፍላጐት የሚመለከተውን ጥያቄ 24.2% በጣም ጥሩ፣ 59.7% ጥሩ፣ 12.9% መካከለኛ፣ 3.2% ዝቅተኛ ብለው ምላሽ ሲሠጡ በጣም ዝቅተኛ የሚለውን አማራጭ አልመረጡትም፡፡ ይህን የተጠኝዎችን ምላሽ በተጠቃለለ ሁኔታ ስናየው ደግሞ 83.9% የሆኑት ተጠኝዎች በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ሲመልሱ ዝቅተኛ ያሉት ግን 3.2% ናቸው፡፡ መካከለኛ የሚለውን አማራጭ የወሠዱ ደግሞ 12.9% ናቸው፡፡ በመሆኑም እጩ መምህራን አጋር መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን ግብረ መልስ ተቀብለው ወደ ተግባር ለመለወጥ ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን መረጃው አመልክቷል፡፡

እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው የሚያገኙትን ግብረ መልስ ተቀብለው ራሣቸውን የሚያስተካክሉበት ፍጥነት ምን እንደሚመስል ለማወቅ የቀረበውን ጥያቄ ደግሞ ተጠኝዎች 16.1% በጣም ጥሩ፣ 51.6% ጥሩ፣ 24.2% መካከለኛ 8.1% ዝቅተኛ ብለው ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ይህንንም ጉዳይ አጠቃለን ብናስቀምጠው 67.7% በጣም ጥሩና ጥሩ ብለው ምላሽ ሲሠጡ 8.1% ዝቅተኛ 24.2% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው የሚሰጣቸውን ግብረ መልስ ተቀብለው ወደ ተግባር የሚለውጡበት ፍጥነትና ቅልጥፍና ከጥሩ ደረጃ ላይ ያልደረሰ መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው የሚያገኙትን ግብረ መልስ በአግባቡ ተቀብለው ወደ ተግባር በመለወጥ እራሣቸውን ለማሻሻል ጥረት እያደረጉ ቢሆንም የተገኘውን ግብረ መልስ ወደ ተግባር የሚለወጡበት ፍጥነት ግን ችግር ያለበት መሆኑን መረጃው አረጋግጧል፡፡

ሠንጠረዥ 18፡የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እያደረገው ያለው ድጋፍና ክትትል

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶቻቸው | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 13 | የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን ስምሪት በተጠናና ምሬትና መሥላቶት በማያስከትል መልኩ የማካሄድ ብቃቱ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 5 | 20.0 | 2 | 5.4 | 7 | 11.3 |
| | | ጥሩ | 10 | 40.0 | 13 | 35.1 | 23 | 37.1 |
| | | መካከለኛ | 9 | 36.0 | 15 | 40.5 | 24 | 38.7 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 5 | 13.5 | 6 | 9.7 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | 2 | 5.4 | 2 | 3.2 |
| 14 | የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን ተልእኮ አፈፃፀም ለማገዝ እየፈፀመው ያለው በእቅድ የታገዘ ተግባር ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 5 | 20.0 | 4 | 10.8 | 9 | 14.5 |
| | | ጥሩ | 10 | 40.0 | 9 | 24.3 | 19 | 30.7 |
| | | መካከለኛ | 7 | 28.0 | 17 | 45.9 | 24 | 38.7 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 8.0 | 5 | 13.5 | 7 | 11.3 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 2 | 5.4 | 3 | 4.8 |
| 15 | የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ቆይታቸው የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል የሚያደርገው ጥረት ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 2 | 8.0 | 4 | 10.8 | 6 | 9.7 |
| | | ጥሩ | 10 | 40.0 | 12 | 32.4 | 22 | 35.5 |
| | | መካከለኛ | 5 | 20.0 | 11 | 29.7 | 16 | 25.8 |
| | | ዝቅተኛ | 6 | 24.0 | 7 | 18.9 | 13 | 20.9 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 2 | 8.0 | 3 | 8.1 | 5 | 8.1 |
| 19 | የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ከአጋር መምህራን ጋር ተቀራርቦ የመስራት ልምዱስ ምን ይመስላል? | በ/ጥሩ | 1 | 4.0 | 2 | 5.4 | 3 | 4.8 |
| | | ጥሩ | 2 | 8.0 | 6 | 16.2 | 8 | 12.9 |
| | | መካከለኛ | 8 | 32.0 | 5 | 13.5 | 13 | 20.9 |
| | | ዝቅተኛ | 10 | 40.0 | 19 | 51.4 | 29 | 46.8 |
| | | /ዝቅተኛ | 4 | 16.0 | 5 | 13.5 | 9 | 14.5 |

የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሃ-ግብር ዋነኛ ባለቤት የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ መርሃ-ግብር ተጠቅመው ንድፈ ሃሣባዊ እውቀታቸውን በተግባራዊ ልምምድ የሚያዳብሩት የኮሌጁ ተማሪዎች የሆኑት እጩ መምህራን ናቸው፡፡ በመሆኑም መርሃ-ግብሩን በቅርበት ተከታትሎ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ የኮሌጁ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ምን ይመስላል በማለት መርሃ-ግብሩን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቅርብ ክትትል እያደረጉበት ላሉት አጋር መምህራን ለቀረቡት አራት ጥያቄዎች የተሠጠው ምላሽ በመቶኛ ሲሠላ የሚከተለውን መረጃ ሠጥቷል፡፡

ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን የስልጠና ስምሪት በጥናት ላይ ተመስርቶ ስለማከናወኑ የቀረበውን ጥያቄ ተጠኝዎች፣ 11.3% በጣም ጥሩ፣ 37.1% ጥሩ፣ 38.7% መካከለኛ፣ 9.7% ዝቅተኛ 3.2% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተውታል፡፡ ይህ መረጃ ተጠቃልሎ ሲታይ ደግሞ በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች 48.4% ናቸው፡፡ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 12.9% ሲሆኑ፣ 38.7% ተጠኝዎች መካከለኛ የሚል ነው፡፡

ከዚህ አሃዛዊ መረጃ የተገኘው ሃሣብ የሚያመለክተው እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲሠማሩ ለመርሃ-ግብሩ አፈፃፀም ያለው ምቹ ሁኔታ ምን ይመስላል? የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችስ እጩ መምህራኑን ተቀብሎ የማስተናገድ አቅም ምን ያህል ነው? የሚሉ የቅድመ ስምሪት ጥናት የሚጠይቁ ጉዳዮች ብዙም ትኩረት ያልተሠጠባቸው መሆናቸውን ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ላይ ለቀረበው ጥያቄ የተሠጡት ምላሾች በአመዛኙ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል ሆኖ መገኘቱ የትኩረቱን አናሣነት በማሳየቱ ነው፡፡

የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን ተልእኮ አፈፃፀም ለማገዝ እየፈፀመው ያለውን በእቅድ የታገዘ ተግባር በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኝዎች 14.5% በጣም ጥሩ 30.7% ጥሩ 38.7% መካከለኛ 11.3% ዝቅተኛ 4.8% በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡ ይህ አሃዝ ለማመዛዘን በሚያመች መልክ ሲጠቃለል በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት ተጠኝዎች 45.2% ሲሆኑ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ ብለው የመለሱት ደግሞ 16.1% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 38.7% ተጠኝዎች ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡

በመረጃው መሠረት ኮሌጁ ለእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ እያደረገ ያለው በእቅድ የታቀፈ እገዛ አመርቂ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፣ ምክንያቱም ከጠቅላላ ተጠኝዎች መካከል 54.8% የሆኑ አጋር መምህራን የሠጡት ምላሽ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ደረጃ መሻሻል የሚጠይቁ ተግባራት እንዳሉ መረጃው አመልክቷል፡፡

ኮሌጁ እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል እያደረገ ያለውን ጥረት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ 9.7% በጣም ጥሩ፣ 35.5% ጥሩ፣ 25.8% መካከለኛ፣ 20.9% ዝቅተኛ 8.1% በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሠዋል፡፡ የዚህ ውጤት ሲጠቃለል በጣም ጥሩና ጥሩ ምላሽ የሠጡት 45.2% ሲሆኑ፤ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 29.0% ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 25.8% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡

ከዚህ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ኮሌጁ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያሠማራቸውን እጩ መምህራን በስልጠናው ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል እየተጫወተው ያለው ሚና አናሣ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም 54.8% ተጠኝዎች የሠጡት ምላሽ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል መሆኑ ይህን ያረጋገጠ ነው፡፡

የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ከአጋር መምህራን ጋር ተቀራርቦ የመስራት ልምዱ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ 4.8% በጣም ጥሩ፣ 12.9% ጥሩ፣ 20.9% መካከለኛ 46.8% ዝቅተኛ 14.5% በጣም ዝቅተኛ የሚል መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይህም አሃዝ ለሚዛን እንዲበቃ ሆኖ ሲጠቃለል በጣም ጥሩና ጥሩ ያሉት ተጠኝዎች 17.7% ሲሆኑ፤ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ የሚል ምላሽ የሠጡት ደግሞ 61.3% ናቸው፡፡ መካከለኛ ያሉት ደግሞ 20.9% ናቸው፡፡

አሃዛዊ መረጃው የሚያመለክተው የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያሠማራቸውን እጩ መምህራን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በመከታተል በመጨረሻም ግብረ መልስ ሠጥተው ከሚሠዷቸው አጋር መምህራን ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ከተጠኝዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያመለክተው 61.3% ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል ሲሆን 20.9% ተጠኝዎች ደግሞ መካከለኛ የሚል አመለካከት ያላቸው ናቸው፡፡
ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተውም የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር

ልምምድ ላሰማራቸው እጩ መምህራን ያለው እገዛና ክትትል ድክመት የሚታይበት መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ሰራዊት የተባለው ተጠኚ ‹‹የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተለዋል?›› ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ

> *ትልቁ ጉድለት ያለው ከዚህ ላይ ነው፡፡ አሰልጣኝ ኮሌጆች የሰልጣኞችን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለማስተካከል የሚያደርጉት ጥረት የለም፡፡ ይህም በሰልጣኙ የስልጠና ሂደት የታየውን አውንታዊና አሉታዊ ለውጥ ለመለየት አያስችልም፡፡ ኮሌጆች ለእጩ መምህራን የሚያደርጉት የሂደት ሳይሆን የማጠቃለያ ግምገማ ነው፡፡* (ታህሳስ 7/2003ዓ.ም)

በማለት ያብራራዋል፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላሠማራቸው እጩ መምህራን እያደረገው ያለው ድጋፍና ክትትል ከፍተኛ ጎድለት የሚታይበት መሆኑን በጥናቱ የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ19፡አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | ሴት | | ወንድ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 16 | እርስዎ ለእጩ መምህራን በአጋር መምህርነት ሲመረጡ የተሠማዎ ውስጣዊ ስሜት ምን ይመስል ነበር? | በ/ጥሩ | 16 | 64.0 | 15 | 40.5 | 31 | 50.0 |
| | | ጥሩ | 6 | 24.0 | 13 | 35.1 | 19 | 30.6 |
| | | መካከለኛ | 3 | 12.0 | 6 | 16.2 | 9 | 14.5 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | 2 | 5.4 | 2 | 3.2 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 0- | - | 1 | 2.7 | 1 | 1.6 |
| 17 | በአጋር መምህርነትዎ ለእጩ መምህራን እየሠጡት ያለው ድጋፍ ከእውነተኛው አቅም ጋር ሲያመዛዝኑት ምን ያህል ነው? | በ/ጥሩ | 12 | 48.0 | 11 | 29.7 | 23 | 37.1 |
| | | ጥሩ | 8 | 32.0 | 20 | 54.1 | 28 | 45.2 |
| | | መካከለኛ | 4 | 16.0 | 5 | 13.5 | 9 | 14.5 |
| | | ዝቅተኛ | 1 | 4.0 | 1 | 2.7 | 2 | 3.2 |
| | | በ/ዝቅተኛ | - | - | - | - | - | - |
| 18 | እርስዎና ሌሎች አጋር መምህራን በእጩ መምህራኑ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ላይ ምን ያህል ውይይት አድርጋችኋል? | በ/ጥሩ | 9 | 36.0 | 5 | 13.5 | 14 | 22.6 |
| | | ጥሩ | 10 | 40.0 | 17 | 45.9 | 27 | 43.6 |
| | | መካከለኛ | 2 | 8.0 | 8 | 21.6 | 10 | 16.1 |
| | | ዝቅተኛ | 2 | 8.0 | 7 | 18.9 | 9 | 14.5 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 2 | 8.0 | - | - | 2 | 3.2 |
| 20 | አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የምትሞሉት የግምገማ ቅጽ ምን ያህል በነባራዊው እውነታ ላይ የተመሠረተ ነው? | በ/ጥሩ | 2 | 8.0 | 3 | 8.1 | 5 | 8.1 |
| | | ጥሩ | 15 | 60.0 | 12 | 32.4 | 27 | 43.6 |
| | | መካከለኛ | 6 | 24.0 | 9 | 24.3 | 15 | 24.2 |
| | | ዝቅተኛ | - | - | 8 | 21.6 | 8 | 12.9 |
| | | በ/ዝቅተኛ | 2 | 8.0 | 5 | 13.5 | 7 | 11.3 |

በዚህ ሠንጠረዥ የተገለፀው መረጃ እንዲያስረዳ የታለመው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ ያሉ መደበኛ መምህራን በትምህርት ቤታቸው ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለተመደቡ እጩ መምህራን ተገቢ ድጋፍና ክትትል እንዲያደርጉ ሲመደቡ የሚያሣዩትን ፍላጎት ነው፡፡ የአጋር መምህራኑ ፍላጎት ሲነሳሳና ሲቀዘቅዝ በመርሃ-ግብሩ ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊና

አሉታዊ ተፅእኖ አለው፡፡ በመሆኑም አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን በድጋፍ ሠጭነት መመረጣቸው ያሣደረባቸውን ስሜት ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኝዎች 50.0% በጣም ጥሩ፣ 30.6% ጥሩ፣ 14.5% መካከለኛ 3.2% ዝቅተኛ፣ 1.6% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ሲጠቃለል ደግሞ 80.6% በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ ሲሠጡ፤ በጣም ዝቅተኛና ዝቅተኛ ያሉት 4.8% ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 14.5% ተጠኝዎች ደግሞ መካከለኛ ብለዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሃሣብ ላይ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን በአጋርነት ሲመደቡ ያላቸው ስሜት ጥሩ መሆኑን ነው፡፡

እያንዳንዱ አጋር መምህር ያለውን ሙሉ አቅም በማሚጠጥ ለእጩ መምህራን ድጋፍ ማድረግ አለማድረጉን ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኝዎች 37.1% በጣም ጥሩ፣ 45.2% ጥሩ፣ 14.5% መካከለኛ፣ 3.2% ዝቅተኛ በማለት ሲመልሱ በጣም ዝቅተኛ ያለ የለም፡፡ መረጃው ሲመዛዘን በጣም ጥሩና ጥሩ የሚል ምላሽ የሠጡት 82.3% ሲሆኑ፤ ዝቅተኛ ያሉት ደግሞ 3.2% ብቻ ናቸው፡፡ መካከለኛ የሚለውን አማራጭ የመረጡት ደግሞ 14.5 ናቸው፡፡

ይህ መረጃ የሚያረጋግጠው አጋር መምህራን ያላቸውን አቅም ሁሉ ተጠቅመው የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለማሣካት እየሠሩ መሆኑን ነው፡፡

አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚሠጡትን ድጋፍና አቅጣጫ ከሌሎች ጋር ተደጋጋፊነትና ወጥነት ያለው ለማድረግ የእርስ በእርስ ግንኙነትና ምክክር ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ ለተዘጋጀው ጥያቄ ደግሞ ተጠኝዎች 22.6% በጣም ጥሩ፣ 43.6% ጥሩ፣ 16.1% መካከለኛ፣ 14.5% ዝቅተኛ፣ 3.2% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ የተጠኝዎችን ምላሽ አሠባስበን ስናስቀምጠው ደግሞ 66.2% በጣም ጥሩና ጥሩ ሲሉ፤ 17.7% ደግሞ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 16.1% ደግሞ መካከለኛ ያሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ በአጋር መምህራን መካከል ጥቂት የማይባል የእርስ በእርስ መመካከርና መደጋገፍ ያለ መሆኑን መረጃው ቢያመለክትም ከተሰጡት

ምላሾች አንጻር በአጋር መምህራት መካከል የትብብርና ቅርርብ ስሜት ለመፍጠር ሰፊ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ መረጃው አመልክቷል፡፡

አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚሞሉላቸው ውጤት ከእውናዊው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያለውን መጣጣም ለማወቅ ታልሞ ለቀረበው ጥያቄ ተጠኝዎች 8.1% በጣም ጥሩ፣ 43.6% ጥሩ፣ 24.2% መካከለኛ፣ 12.9% ዝቅተኛ 11.3% በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ ይህ መረጃ ሲጠቃለል 51.7% በጣም ጥሩና ጥሩ ሲሉ፣ 24.2% ደግሞ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ያሉ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 24.2% ደግሞ መካከለኛ የሚል ምላሽ የሠጡ ናቸው፡፡

ይህ መረጃ በአስተውሎት ሲመዘን ጥንቃቄ የታከለበትና ትኩረት ሊለየው የማይገባ ችግር እንዳለ የሚያመለክት ነው፡፡ አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚሞሉት የመገምገሚያ ቅጽ የመምህርነት ብቃታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተሠጠው ምላሽ ደግሞ 24.2% ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ቀሪው 24.2% ደግሞ መካከለኛ የሚል ከማእከላዊ ነጥብ ያልዘለለ ሃሣብ ነው፡፡ የነዚህ ሁለት መረጃዎች ድምር ደግሞ ከጠቅላላው ተጠኝዎች መካከል 48.4% መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ የሠጡ መሆናቸውን ይገልፅልናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ መረጃው እያሳየው ያለው ችግር አሳሳቢነቱ ቀላል አይደለም፡፡ ስለዚህ አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የሚሰጡትን የግምገማ ውጤት ከችግር ነጻ ለማድረግ መሰራትና መስተካከል ያለባቸው ተግባራት ያሉ መሆኑን መረጃው አሳይቷል፡፡

ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሲፈተሽ ደግሞ በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ ጉልበት የተባለው ተጠኚ «አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?» ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ

> *ይህን ሁኔታ በሁለት መልክ ማየት ያስፈልጋል፡፡ የተወሰኑት መምህራን በፈቃደኝነት ተቀብለው እጩ መምህራንን በማገዝ ለማብቃት ጥረት ያደረጋሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ እጩ መምህራኑን ማስተማር እንደማይችሉ አድርገው የተገነዘቡና ዝቅ አድርገው የሚመለከቷቸው አሉ፡፡* (ታህሳስ 4/2003ዓ.ም)

በማለት የተወሰኑ አጋር መምህራንን ትኩረት ባነሰው መንገድ ሰልጣኞችን የሚያስተናግዱ መሆኑን ገልጿል፡፡

በአጠቃላይ አጋር መምህራን ከጐናቸው ለሚመደቡት እጩ መምህራን ሊያደርጉ የሚገባውን ድጋፍና ክትትል በተመለከተ ከተጠኝዎች የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው እንቅስቃሴው ትኩረት አዘል ጥረት ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በሁሉም ጥያቄዎች የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት ችግር ያልተለየው መሆኑን ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሣብ

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ትግበራ ያላቸውን ኃላፊነት የመወጣት ብቃት ለመመርመር የተካሄደ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሣትም በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሂደት ዋነኛ ተሣታፊ የሆኑት እጩ መምህራን በተመደቡባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሊጫወቱ የሚችሉትን ሚና ለይቶ ማሣየት፤ ተለይተው የታወቁትን ሚናዎች በተገቢው መንገድ መወጣት መቻል አለመቻላቸውን መመርመር፤ በማስተማር ልምምድ ወቅት እጩ መምህራን ከመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ጋር ተባብረው በመስራት ሊያከናውኑ የሚችሉትን ተግባር መተንተን፤ እጩ መምህራን ከማሠልጠኛ ኮሌጁ ለልምምድ ሲወጡ የሚሠጣቸው ተልእኮ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደት ጋር ያለውን መጣጣም መመርመርና መገምገም፣ የሚሉ ዝርዝር አላማዎችን አካትቶ የተካሄደ ነው፡፡

ዋና ትኩረቱን ያደረገውም በአማራ ብሔራዊ ክልል፣ ምስራቅ ጐጃም ዞን፣ በደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኙና በናሙናነት በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በነዚህ ትምህርት ቤቶች ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በተሠማሩት የደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እጩ መምህራን፣ ከየትምህርት ቤቶቹ በአጋር መምህርነት በተመረጡ መምህራንና በትምህርት ቤቶች የአስተዳድር ሠራተኞች ላይ ነው፡፡

በተጠቀሱት አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተመደቡት የ10+3 መርሃ-ግብር እጩ መምህራን ሴት 32 ወንድ 60 ድምር 92 ናቸው፡፡ ለነዚህ እጩ መምህራን አጋር ሆነው የተመደቡትና በየትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩት መደበኛ መምህራንም ሴት 25 ወንድ 37 ድምር 62 ናቸው፡፡

የትምህርት ቤቶችን አስተዳደራዊ ተግባር እያከናወኑ ያሉት ርእሠ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ደግሞ ሴት 2 ወንድ 9 ድምር 11 ናቸው፡፡ እነዚህ በአመቺ የናሙና ስልት የተመረጡ ተጠኝዎች በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካይነት መረጃ እንዲሠጡ ተደርጓል፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ በዋና የመረጃ መሠብሠቢያነት ለእጩ መምህራንና ለአጋር መምህራን የቀረቡ ሁለት አይነት መጠይቆች ተዘጋጅተው በስራ ላይ ውለዋል፡፡ መጠይቆቹ በተጠኝዎች ስነ-ልቦናና የኃላፊነት መለያየት የተነካ በተለያየ መልክ እንዲዘጋጁ ተደረገ እንጅ የይዘት አንድነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በርእሰ መምህራን፣ ምክትል ርእሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ምላሽ የተሠጠባቸው ቃለ መጠይቆችና አጥኝው በተደጋጋሚ ያካሄዳቸው ምልከታዎች በአጋርነት መረጃውን ለማሠባሰብ አገልግለዋል፡፡ በነዚህ መሣሪያዎች የተሠበሰቡት መረጃዎች በጥናቱ ምእራፍ አራት ላይ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

መረጃዎቹ ሲተነተኑም፡

- የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በማስተግበር ሂደት ኮሌጁ በሚሠጠው ተልእኮና በመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መርሃ-ግብር መካከል ግጭት አለመፈጠሩን አመልክቷል፣
- እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ያዳብሩታል ተብሎ የተያዘላቸውን የማስተማር ክሂል ለማሣካት እያደረጉት ያለው ጥረት አበረታች መሆኑን አሣይቷል፣
- እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከተሠማሩባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋር ያላቸው ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን አስረድቷል፣
- መሠረታዊ ተልእኳቸው በንድፈ ሃሣብ የቀሠሙትን የስነ-ትምህርት እውቀት በተግባር መለማመድ የሆነው እጩ መምህራን በተመደቡባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እያከናወኑት ያለውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በመልካም ሁኔታ ላይ መሆኑን አረጋግጧል፣

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የእጩ መምህራኑን ስልጠና ለማሣካት የዘረጉት የአሠራር ትልምና እያከናወኑት ያለው አፈፃፀም በጥሩ ደረጃ ላይ

የሚገኝ መሆኑንም አስረድቷል፣

- እጩ መምህራኑን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያሠማራው የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሠልጣኞችን ሁኔታ በቅርበትና በትኩረት እንደማይከታተልም አሣይቷል፣

በአጠቃላይ ጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር የተጣለባቸውን ኃላፊነት የመወጣት ብቃታቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ በተሰበሰቡት መረጃዎችና ከመረጃዎች ትንተና በተገኘው ውጤት አሳይቷል፡፡

## 5.2. የመፍትሔ ሃሣብ

የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ይቻል ዘንድ አጥኝው የሚከተሉትን የመፍትሔ ሃሣቦች አቅርቧል፡፡

1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና እጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በማስተግበር ሂደት ኃላፊነታቸውን የመወጣት ብቃታቸው በአመዛኙ ጥሩ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ሆኖም በጥናቱ አብላጫ አሃዝ የተዋጡና በተለያዩ ተግባራት ላይ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ አፈፃፀም አለ የሚሉ ተጠኝዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ በመሆኑም እስከአሁን ያለው የአፈፃፀም ብቃት እየተጠናከረ አልፎ አልፎ የሚታዩ የአፈፃፀም ድክመቶች የሚወገዱበት ስልት በትምህርት ቢሮው፣በአሰልጣኝ ኮሌጁና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የግልና የጋራ ጥረት ቢፈለግ፣

እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚቀበሏቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ የእነዚህን ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ አቅምና የመስተንግዶ ባህሪ የሚያውቁት ደግሞ የትምህርት ቤቶች አመራሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ከመሠማራታቸው በፊት የነዚህ ትምህርት ቤቶች የመቀበል አቅምና ፈቃደኝነት ከትምህርት ቤቶች አመራር ጋር በሚደረግ ውይይት

እየተዳሠሰ አሳምኖ የማስፈጸም ተግባር ቢከናወን፣

3. በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡ ነገር ግን ኮሚቴው የሚመራበት የስራ መርህና ኃላፊነት በግልፅ የአልተሠጠው መሆኑን አጥኚው በምልከታ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ኮሌጁንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አጣምሮ የመምራት ሃላፊነት ያለበት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የኮሚቴውን ኃላፊነትና የስራ ድርሻ ለይቶ መመሪያ ቢያዘጋጅ፣

4. አጨ፡ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያሠማራው የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጁ መርሃ-ግብሩን ስኬታማ የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ነገር ግን የትምህርት ቤት አመራሮች፣ መምህራንና እጩ መምህራን የኮሌጁን ክትትልና እገዛ ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በጥናቱ የመረጃ ትንተናም የታየው ውጤት ይህንኑ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንም ሆነ የእጩ መምህራኑን የተልዕኮ አፈፃፀም ይጐዳዋል፡፡ በመሆኑም ኮሌጁ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር በቅርበት ሊያገናኘው የሚችል የአሠራር ስልት ዘርግቶ ስልጠናውን ቢከታተል፣

5. የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ብቁ መምህር በማፍራት ትውልድን በተሻለ ሁኔታ ለመቅረጽ ያስችላል ተብሎ የሚገመት መርሃ-ግብር በመሆኑ የአፈፃፀሙን ብቃት ለማሣደግ በዚህ ዘርፍ ሌሎች ተጨማሪ ጥናቶች ቢካሄዱ፣

## ዋቢ መጻህፍት


ሂሩት አምሃ ::(1998)::‹‹ በፕራክቲከም የማስተማር ልምምድ የሱፐርቪዥን አተገባበር በደቡብ ኢትዮጵያ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ 10+3 የመምህራ ስልጠና መርሃ ግብር::›› *ለአማርኛ ማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት (ያልታተመ)::

በላይሁን አውላቸው ::(1999):: ‹‹በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ10+3 መርሀ ግብር በአማርኛ ቋንቋ ድህረ የማስተማር ልምምድ የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ አሰጣጥ ፍተሻ::›› *ለአማርኛ ማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት (ያልታተመ)::

ተስጠ አሰፋ ::(1997)::‹‹ የፕራክቲከም የማስተማር ልምምድና የሱፐርቪዥን አተገባበር በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርተፊኬት 10+1 መርሀ ግብር::›› *የአርትስ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ*: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: (ያልታተመ)::

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ (2002):: ‹‹የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አፈጻጸም መመሪያ::››የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ:: ባህርዳር (ያልታተመ)::

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት:: (1997)::‹‹ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተጠቃለሉ ህጎች::›› *በስራ ላይ ልምምድ የሚሳተፉ ድርጅቶች ተግባርና ሃላፊነት*፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት:: ባህርዳር:: (ያልታተመ)::

ዓለም እሸቱ:: (1988)::‹‹ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ ክፍል ድህረ የማስተማር ልምምድ ውይይት የሱፐርቫይዘሮች ምግበ መረጃ ትንተና::›› *የአርትስ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)::

አለማየሁ ተክለማሪያም::(1997):: ‹‹የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ›› ሥርአተ ትምህርት መጽሔት ቅጽ 2 ገጽ 2::

ያለው እንዳወቀ:: (2001)::*የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር::* ንግድ ማተሚያ ድርጅት:: አዲስ አበባ (ሁለተኛ እትም)

Alemayehu, D. (1998). "Teacher Education Trends in Some countries: Implications for the Ethiopian content." *In proceeding of the National conference Held in Awassa collage of Teacher Education* July 12-18.

Arm Strong, O. (1991). *A Hand book of Human Resources Management.* London Kogan page, Ltd.

Azeb, D. (1984). "Elements of General Methods of Teaching." Addis Ababa University (unpublished)

Bahir Dar University. (2008). *Manual and Guide Line For practicum I, Practicum II, Practicum III,* Bahir Dar University.

Befekadu T/sadik. (1998). *Quality of Education in Ethiopia, visions for 21st century,* Institute of Educational research, Addis Ababa University.

Bridges, D and Marew, Z. (Eds.) (2000). *Secondary Teacher Education in Ethiopia*: An over view Addis Ababa. Addis Ababa University.

C. r. Ko thari. (2006). *Research Methodology.* New age International (p) Ltd, publisher, Delhi.

E.B Castle. (1993). *Principles of Education for Teachers in Africa,* Oxford University press. Oxford.

Ellis, R. (1986). "Activities and Procedures for teachers Training." *ELT Journal* Vol. 40 No 2 PP91-99.

Gebremedhin S. (2001). "Aspects of Teacher Development for English Language Teaching: Implication for quality of Education in Primary Schools". *In proceedings of the National conference held in Adama Ras Hotel* November 9-11.

Kindalem, D. (2005). "The Implementation of Practicum in the Education Faculty of AAU. ELT in Focus", *M.A Thesis,* Addis Ababa University (un Published).

Lokesh Koul. (2006). *Methodology of Educational research.* (Third Revised Edition), wikay publishing House PVT LTD.

Mangal, S.K. (2007). *Essential Educational Psychology*, Presentice- Hall of India Private Limited. Ne Delhi.

Mra Pollack Sadke, Dallid Miller Sadker. (2000). *Teachers Schools and Society* , (fifth edition).

Ministry of Education. (2003). " Teach Education System overhaul (TESO) Hand book".

Natalie, G., Christine, M., Dlores, D., Bryan, D. (1998). *Learning to Teach, A critical approach to field experiences*, Lawrence Erlbaum Associates publisher. London.

Perrott, E. (1982). *Effective Teaching a Practical Guide to Improving your Teaching*, New York: Longman.

Smith, B. O. (1972). "An Approach to Systematic Training" in stones, E. and Morris, S. (Eds) *Teaching Practices Problems and Perspectives*, pp 231-244 Condon Methuen and Co. Ltd.

Srivastava, Rc, and Bose, K. (1978). *Theory and Practice of Teacher Education in India*, New delhi: Chugh Publications.

Shiundu, J and Omulando, S. (1992). *Curriculum: Theory and Practice in Kenya*. Nairobi: Oxford University Press.

Tirusew Teffera. (2006). " An Introductory Note on the Educational system and Teacher education" *paper presented at 1st Meeting of National Coordinators for Training Initiative for sub Sahran Africa* 7-9 March, 2006 BREDA, Dakar Senegal Higher Education

Walters, E. (1986). "Top Ten principles for Teaching Reading Class room" *ELT Journal* Vol. 40 No. 1 pp 42-45.

________(1960). *Teacher Training college In The west Indies*. London; Oxford University Press.

Http://www. Jamensah, comp sseeches, practicum 20 in Teacher %20 Educ%20 do.

Http://www. Jamensah Com/speeches/ practicum % 20 in Teacher %20 Educ%20 Do Janamuahmen sah

# አባሪዎች

አባሪ 1

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የስነ- ትምህርት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በእጩ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

መግቢያ

የዚህ መጠይቅ መሰረታዊ ዓላማ እጩ መምህራንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ/practicum/ አተገባበር ሂደት የተሰጣቸውን ሀላፊነት የመወጣት ብቃት በጥናት ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ማሰበሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የሚሰበሰበው መረጃ ለጥናቱ ብቻ የሚያገለግል ሲሆን በምንም አይነት መንገድ ለሌላ ወገን ተላልፎ አይሰጥም፡፡ ስለሆነም የጽሁፍ መጠይቁን በአግባቡ ሞልተው በመመለስና ትክክለና መረጃ በመስጠት የበኩልዎን በጎ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉልኝ እተማመናለሁ፡፡

ለተደረገልኝ ቅን ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል አንድ- አጠቃላይ መረጃ

1. እጩ መምህሩ (ሯ) የሚሰለጥንበት/የምትሰለጥንበት የመምህራን ኮሌጅ ስም ----
   --------------------------
2. እጩ መምህሩ(ሯ) የሚሰለጥንበት/የምትሰለጥንበት መርሀ ግብር መደበኛ
   መደበኛ ☐ ተከታታይ ☐
3. እጩ መምህሩ(ሯ) ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተመደበበት(ችበት) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ስም ---------------------
4. የእጩ መምህሩ(ሯ) እድሜ ------------------ ፆታ ---------------------
   የጋብቻ ሁኔታ፣ ያገባ(ች) ☐ ያላገባ(ች) ☐
   የሚያጠናው (የምታጠናው) የትምህርት አይነት አብይ-------------
   ንዑስ -----------
5. ለእጩ መምህሩ(ሯ) በአጋርነት የተመደበው(ችው) መምህር ፆታ ----------------

6. አጋር መምህሩ(ሯ) የሚያስተምረው( የምታስተምረው) የትምህርት አይነት

## ክፍል ሁለት- መጠይቆች

ከዚህ ቀጥሎ ስለቀረቡት ጥያቄዎች ያለህን(ሽን) ግንዛቤ ከፊት ለፊት በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ ካለት አማራጭ መልሶች በአንዱ ላይ (×) ምልክት በማድረግ መልስ ስጥ(ጭ)።

| | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በጣም ጥሩ | ጥሩ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርህ ግብር ወደ ተመደብህበት(ሽበት) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመምጣትህ(ሽ) በፊት ከምትማርበት(ሪበት) ኮሌጅ የተሰጠህ(ሽ) የተግባር አፈጻጸም ተልእኮ አሁን ለምታደርገው(ጊው) ተግባራዊ ልምምድ ምን ያህል እገዛ አድርጎልሃል(ሽል)? | | | | | |
| ከማሰልጠኛ ኮሌጁ የተሰጠህ(ሽ) የተግባራዊ ልምምድ አፈጻጸም ተልእኮ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አቀባበል ጋር ስታገናኘው(ኚው) ስምምነቱ ምን ይመስላል? | | | | | |
| ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በተመደብህበት/ሽበት/ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደት እራስህን(ሽን) ለማስተማር የምታደርገው (ጊው) ጥረት ምን ይመስላል? | | | | | |
| የትምህርት ቤቱን አስተዳደራዊ ስርአቶች በመቃኘት ለወደፊት ቋሚ ተግባርህ(ሽ) የሚያግዝ ማስታወሻ የመያዝ ልምድህ(ሽ) ምን ይመስላል? | | | | | |
| ስልጠና እየወሰድህበት(ሽበት) ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርህ ግብር መሳካት እያደረገ ያለው ትብብር ምን ይመስላል? | | | | | |
| እጩ መምህራን ሁሉንም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ቃኝተው እራሳቸውን ከተግባር እንዲያስተምሩ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቱ አስተዳደር የፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምን ይመስላል? | | | | | |
| እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ ሁለገብ እንቅስቃሴ በመማር እራሳቸውን ብቁ መምህር አድርገው በመቅረጽ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| እጩ መምህራ የትምህርት ቤቱን ህግና ደንብ አክብረው ተልእኳቸውን ለመፈጸም እያደረጉት ያለውን ጥረት እንዴት ታየዋለህ(ታይዋለሽ)? | | | | | |
| አንተ/አንቺ ከትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ሰራተኞች የሚሰጥህን/ሽን ተልእኮ ለመፈጸም ያለህ/ሽ/ ተነሳሽነት ምን ይመስላል? | | | | | |
| የአስተዳደር ሰራተኞች ለእጩ መምህራን የላቸው ትብብር ምን ይመስላል? | | | | | |
| አንተ/ አንቺ በምተከናዉነው /ኚው/ የትምህትር ቤት | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ተግባር በአጠቃላይ ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ጋር ያለህን(ሽን) ግንኙነት እንዴት ታየዋለህ(ታይዋለሽ)? | | | | | |
| 12 | በምታስተምርበት/ሪበት/ ወይም የማስተማር ልምምድ በምታደርግበት(ጊበት) ክፍል ውስጥ ካሉት ተማሪዎችስ ጋር ያለህ(ሽ) ግንኙነት ምን ይመስላል? | | | | | |
| 13 | የምታስተምራቸው(ሪያቸው) ተማሪዎች ለአንተ/ አንቺ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? | | | | | |
| 14 | የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን መርሀ ግብር በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ለአንተ/አንቺ የተመደበልህ(ሽ) አጋር መምህር እያደረገልህ(ሽ) ያለው እገዛ ምን ይመስላል? | | | | | |
| 15 | አጋር መምህርህ(ሽ) አንተ/አንቺ ለምታከናውናቸው(ኛቸው) ተግባራት የሚሰጥህ ግብረ መልስ ያለው የገንቢነት ሚና ምን ይመስላል? | | | | | |
| 16 | በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሚከናወኑ ተጓዳኝ የትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እያደረገህ(ሽ) ያለኸው (ሽው) ተሳትፎ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 7 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በሚያቅዳቸው ትምህርት ቤቱን የማልማት ተግባራት እያደረግህ(ሽ) ያለኸው(ሽው) ተሳትፎ ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 8 | የመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ እያደረገ ያለው እገዛ ምን ይመስላል? | | | | | |
| 9 | ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን አጠቃላይ እንቅስቃሴ እየተከታተለ ያለበት ስልት በአንተ/አንቺ እይታ እንዴት ይገመገማል? | | | | | |
| 0 | ለስልጠና የተሰማራህበት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለትምህርት ቤቱ ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ትግበራ ያዘጋጀው መርሀ ግብር ከማስልጠኛ ኮሌጁ የአፈጻጸም መርሀ ግብር ጋር ያለው ትስስር እንዴት ነው? | | | | | |

አባሪ 2

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የስነ- ትምህርት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለአጋር መምህራን/ Mentors/የቀረበ መጠይቅ

መግቢያ

ይህ መጠይቅ የቀረበበት መሰረታዊ ዓላማ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ/Practicum/ የተሰማሩ እጩ መምህራንና ልምምዱ ተግባራዊ የሚደረግባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተሰጣቸውን ሀላፊነት የመወጣት ብቃታቸውን በጥናት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃ ለማሰባሰብ ነው። በመሆኑም በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የሚሰበሰብ ማንኛውም መረጃ በግብአትነት ለጥናቱ ብቻ የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ በምንም አይነት ሁኔታ ለሌላ ወገን ተላልፎ አይሰጥም። በመሆኑም እርስው በነጻ ሀሊናና በተባባሪነት መንፈስ መጠይቁን በእውነት ላይ በተመሰረት አካሄድ ሞልተው ትክክለኛ መረጃ በመስጠት የበኩልዎን እገዛ ያደርጉልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ።

ለተደረገልኝ ቅን ትብብርዎ በቅድሚያ አመሰግናለሁ!

ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መረጃ

1. የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------
2. መጠይቁን የሞላው(ችው) አጋር መምህር እድሜ --------------

ጾታ ------------------------

የትምህርት ደረጃ --------------------------

ያጠናው(ችው) የትምህርት አይነት ------------------

የአገልግሎት ዘመን ------------------

በመምህራን እድገት መሰላል የደረሰበት/ችበት ደረጃ -----------------

ክፍል ሁለት፡- መጠይቆች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከፊት ለፊታቸው በተሰጠው ሰንጠረዥ ላይ ከተቀመጡት አማራጮች እርስዎ የሚስማሙበትን(×) ምልክት በማድረግ ስሜትዎን ይግለጹ፡፡

| ተ.ቁ | መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ጥሩ | ጥሩ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተመደቡት እጩ መምህራን ይዘውት የመጡት የአፈጻጸም መርሀ ግብር ከትምህርት ቤቱ መደበኛ ፕሮግራም ጋር ያለው መጣጣም እንዴት ይገመገማል? | | | | | |
| 2 | እጩ መምህራን ከአጠቃላዩ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ለመማር ያላቸው ስሜት ምን ይመስላል? | | | | | |
| 3 | እጩ መምህራኑ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት ጋር እራሳቸውን ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 4 | እጩ መምህራን የአጋር መምህራሮቻቸውን ምክርና እገዛ ተቀብለው ድክመታቸውን ለማስተካከል የሚያደርጉትን ጥረት እንዴት ያውቃል? | | | | | |
| 5 | እጩ መምህራን ከሌሎች መምህራን ጋር ተጠግተውና ተባብረው ለመስራት የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 6 | እጩ መምህራን ከማስልጠኛ ኮሌጅ የተማሩትን ንድፈ ሀሳባዊ እውቀትና ክህሎት በተግባር ለመሞከር የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል? | | | | | |
| 7 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለእጩ መምህራን ስልጠና መሳካት እየፈጠረ ያለው ምቹ ሁኔታ ምን ይመስላል? | | | | | |
| 8 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የእጩ መምህራንን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተመር ልምምድ ተግባራዊ አፈጻጸም ለመከታተል የሚያደርገው ጥረት ምን ይመስላል? | | | | | |
| 9 | እርስዎ በአጋር መምህርነትዎ የእጩ መምህራኑን ተልእኮ ለማሳካት የሚያከናውኑት የታቀደ ተግባር ምን ይመስላል? | | | | | |
| 10 | እጩ መምህራን በሚያደርጉት የተግባር ልምምድ ከሚሰሯቸው ስህተቶች እንዲማሩ ለማድረግ የዘረጉት የተጠናከረ ስልት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 11 | እጩ መምህራን ከአጋር መምህሮቻቸው የሚሰጣቸውን ግብረ መልስ(Feedback) ተቀብለው በተግባር ለማዋ ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 12 | እጩ መመህራን የተሰጣቸውን ግብረ መከልስ ተቀብለው እራሳቸውን የሚያስተካከሉበት ፍጥነት እንዴት ይገመገማል? | | | | | |
| 13 | የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን ስምሪት በተጠናና ምሬትና መሰለቸት በማያስከትል መልክ መካሄድ ብቃታቱ ምን ይመስላል? | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራንን ተልእኮ አፈጻጸም ለማገዝ እየፈጸመው ያለው በእቅድ፣የታገዘ ተግባር ምን ይመስላል? | | | | | |
| 15 | የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ እጩ መምህራን በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ቆይታቸው የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል የሚያደርገው ጥረት ምን ይመስላል? | | | | | |
| 16 | እርስዎ ለእጩ መምህራን በአጋር መምህርነት ሲመረጡ የተሰማዎ ውስጣዊ ስሜት ምን ይመስል ነበር? | | | | | |
| 17 | በአጋር መምህርነትዎ ለእጩ መምህራኑ እየሰጡት ያለው ድጋፍ ከእውነተኛው አቅም ጋር ሲያመዛዝኑት ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 18 | እርስዎና ሌሎች አጋር መምህራን በእጩ መምህራኑ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተመር ልምምድ ላይ ምን ያህል ውይይት አደርጋችኋል? | | | | | |
| 19 | የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ ከአጋር መምህራን ጋር ተቀራርቦ የመስራት ልምዱስ ምን ይመስላል? | | | | | |
| 20 | አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን የምትሞሉት የግምገማ ቅጽ ምን ያህል በነባራዊው እውነታ ላይ የተመሰረተ ነው? | | | | | |

አባሪ 3

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የስነ- ትምህርት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የቀረበ ቃለ መጠይቅ

II. አጠቃላይ መረጃ

ሀ. እድሜ -----------------------------

ለ. ፆታ -----------------------------------------

ሐ. የትምህርት ደረጃ ---------------------------------

መ. የተመረቁበት የትምህርት ዘርፍ ---------------------

ሠ. የአገልግሎት ዘመን -------------------------------

III. የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

1. የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው። እርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ? እንዴት?
2. የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአትና ደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው ነው የመማር ማስተማሩን የሚያከናውኑት። ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውክም?እንዴት?
3. እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

4. የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን? ምክንያት ካለው?
5. የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር፣ እንዴት ይከታተሉታል?
6. ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?
7. እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ?
8. አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

   አወንታዊ?

   አሉታዊ ?

   ለምን?
9. በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?
10. በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ?

አባሪ 4

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የስነ- ትምህርት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------------

ምልከታ የተደረገበት ቀን ------------------------

ፊረቃ -------------------------- ሰአት --------------------------

| ተ.ቁ | የትኩረት ተግባራት | በጣም ጥሩ | ጥሩ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ትምህርት ቤቱ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ተግባራዊ ለማድረግ ያለው ብቃት፤ | | | | |
| 2 | ትምህርት ቤቱ እጩ መምህራኑን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ለመቀበል ያለው ፈቃደኝነት፤ | | | | |
| 3 | የእጩ መምህራንና የትምህርት ቤቱ መምህራን ግንኙነት፤ | | | | |
| 4 | የእጩ መምህራንና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ግንኙነት፤ | | | | |
| 5 | የእጩ መምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት፤ | | | | |
| 6 | እጩ መምህራን በትምህርት ቤቱ ከሚከናወኑ ልዩ ልዩ ተግባራት እራሳቸውን ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረት፤ | | | | |
| 7 | እጩ መምህራን ትምህርት ቤቱ ለሚገኝበት አካባቢ ማህበረሰብ ያላቸው አመለካከት | | | | |
| 8 | የአካባቢው ማህበረሰብ ለእጩ መምህራን ያለው አመለካከት | | | | |
| 9 | ተማሪዎች ለእጩ መምህራን ያላቸው አመለካከት | | | | |
| 10 | መምህራን ለእጩ መምህራን ያላቸው አመለካከት | | | | |
| 11 | አስተዳደር ሰራተኞች ለእጩ መምህራን ያላቸው አመለካከት | | | | |
| 12 | የእጩ መምህራን የሰአት አከባበር | | | | |
| 13 | የእጩ መምህራን የህግና ደንብ አካባበር | | | | |
| 14 | የእጩ መምህራን የግል ስብዕና አጠባበቅ | | | | |
| 15 | እጩ መምህረን በተጓዳኝ ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ | | | | |
| 16 | የእጩ መምህራኑ የማስታወሻ አያያዝ | | | | |
| 17 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለእጩ መመህራን የትምህርት ቤት ልማት ተሳትፎ የፈጠረው ምቹ ሁኔታ | | | | |
| 18 | አጋር መምህራን በእጩ መምህራን ላይ የሚታዩ ደካማ ጎኖችን ለማረም የሚወስዷቸው እርምጃዎች | | | | |
| 19 | ተማሪዎች እጩ መምህራን ለሚሰጡት ትምህርት ያላቸው አቀባበል | | | | |
| 20 | የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለእጩ መምህራን ያለው የማስተማሪያ መሳሪያዎች አቅርቦት | | | | |
| 21 | የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ እያደረጉ ያለው ጥረት | | | | |

አባሪ 5 ለቃለ መጠይቁ የተሰጠ ምላሽ

የንጉስ ተክለሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ር/መምህር

እድሜ 31

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት አይነት- ታሪክ

የአገልግት ዘመን- 7 ዓመት

ለቃለ መ

ጥያቄ ቁጥር 1- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሃ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው፡፡ ርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራን የማፍራት እልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ?

መልስ፡- መርሀ ግብሩ በትክክል ከተሰራበት ውጤት ሊያመጣ የሚችል ነው፡፡ አሁን ባለበት ትኩረት ያነሰውና ወጣ ገባ የበዛበት ሁኔታ ግን የሚጠበቀውን ግብ ለመምታት ይቻላል ብዬ አላምንም፡፡ ምክንያቱም ኮሌጁ በትኩረት እየሰራበት አይደለም ክትትሉ በጣም አነስተኛ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአትና በደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው የመማር ማስተማር ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡ ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውከውም?

መልስ፡- የእጩ መምህራኑ መምጣት አንጻራዊ የሆነ ጫና አለው ሆኖም የጎላ ችግር ሆኖ አትዶችንን ያደናቅፋል ብይ አላምንም፡፡ ጫናውን ለማቃለል ኮሌጁ የቅድመ ስምሪት ጥናት በማካሄድ በተለይ በከተማ ትምህርት ቤቶች የሚመደብባቸውን እጩ መምህራን ቁጥር ሊመጥን ይገበዋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3፡- እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት

ይቆያሉ። በ.በ.ህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ?

መልስ፡- አዎ! ብዙዎቹ ጥሩ ስነ ምግባር ያላቸው ናቸው። የእኛም መምህራን በቂ ልምድ ያላቸውና ነባር በመሆናቸው ከዚህ ሂደት ለቀጣዩ የመምህረነት ተግባራቸው የሚያግዝ እውቀትና ልምድ ያገኛሉ ብዬ አምናለሁ። ሆኖም እጩ መምህራኑ የሚገበዩት እውቀት በኮሌጁ ክትትል ሊደረግበት ይገባ ነበር፤ ግን የለም።

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጧቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያለው መጣጠም ምን ይመስላል?

መልስ፡- በመጀመሪያው አካባቢ ችግር ነበር አሁን ግን እየጠበበ የመጣ ነው። ምክንያቱም ኮሌጁ በትምህርት ቤት የፕራክቲከም ኮሚቴ አቋቁሞ ሃላፊነት ከመስጠቱም በላይ በኮሌጁ ደረጃ ሂደቱን የሚከታተል ባለሙያ መድቧል። በመሆኑም ከተልእኮ አንጻር የነበረው ግጭት እየጠበበ መጥቷል።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- የእጩ መምህራን የስልጠና ሂደት የሚከታተል የኮሌጁ አካል የለም እንዴ ከተመደቡ በኋላ ኮሌጁ ዘወር ብሎ አያያቸውም ማስልጠኑ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ክትትሉ ማነሱ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ ጠቃሚ ሙያዊ እድገት ማምጣት የሚያስችል ግምገማ አይደረግምና ለጥሩ ውጤት የሚያበቃ ሂደታዊ ግምገማ መደረግ ይኖርበታል።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህሩ ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- እጩ መምህሩ እኛ ካሰራናቸውና ስራ ከፈጠርንላቸው በክበባትም ሆነ በትምህርት ቤት ክበከቤ ውስጥ ለመሳተፍ አያመነቱም ነገር ግን በራስ ተነሳሽነት ከልዩ ልዩ ከሚቴዎችና ክበባት ልምድ ለመማር የሚደረጉት ጥረት አለያሁም።

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ መሰረት አድርገው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ ፡- በእጩ መምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ ነው። ምክንያቱም እጩ መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ አጋር መምህራን በክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ። በመሆኑም ተማሪዎች የተለያ ባህሪ ለማሳየት እድል አያገኙም ከክፍል ውጭ ግን ብዙም ግንኙነት ያላቸውም።

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ የአቀባባል ስሜታቸው ምን ይመስላል?

መልስ፡- መደበኛ መምህራን በአጋርነት መመደባቸው እየተለመደ የመጣ በመሆኑ መጥፎ ስሜት አይታይም። እንዲያውም እንደ ክፍተት መሙያ ስለሚጠቀሙባቸው ለምን ‹‹ለኔ አልተመደበልኝም?›› የሚል ጥያቄ ነው ያለው። በመሆኖም ችግር የለም ማለት ይቻላል።

ጥያቄ ቁጥር 9፡-በእጩ መምህራንና በአጋር መምህን መካከል ያለው ግንኙነትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- በእጩ መምህራንና በአጋር መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ ነው ብሎ ማጠቃላል ይቻላል።

ጥያቄ ቁጥር 10፡- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ?

መልስ፡- ሰልጣኞች ከአለባበስና ስብእና ጀምሮ እራሳቸውን ለመምህርነት ማዘጋጀት አለባቸው ኮሌጁም እጩ መምህራኑን በሀጻናቱ ፊት የሚፈለግባቸውን ስብዕና በተመለከተ የቅድሚያ ግንዛቤ መፍጠር አለበት ብይ አምናለሁ።

የተክለሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርእሰ መምህር

እድሜ -37

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+2

የተመረቁበት የትምህርት ዘርፍ- ሂሳብ

የአገልግት ዘመን- 17 ዓመት

ለቀረባላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

ጥያቄ ቁጥር 1፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና

የማስተማር ልምምድ/ practicum/ ነው። ይህ መርሀ ግብር ተግባራዊ መደረጉ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን እውን ያደርገዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ ፡- የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አላማ መምህራኑ በእውናዊው የማስተማር ልምምድ ከመሰማራታቸው በፊት በአሰልጣኙ ኮሌጁ መምህራን በአጋር (Mentors) መምህራን እየታገዙ የተግባር ክህሎት እንዲያገኙ ማድረግ በመሆኑ ከአላማ አንጻር ትክክል ነው። በተግባር ደረጃ ሲታይ ግን ችግር አለው። ችግሩም መምህራን ማሰልጣኛ ኮሌጁ ሰልጣኞቹን ካሰማራ በኋላ ዞወር ብሎ አያያቸውም። ክትትልና ቁጥጥርም አያደርገም። በትምህርት ቤት ደረጃ በሚቋቋም ኮሚቴ ብቻ ክትትል ተደርጎ አሰልጣኝ ኮሌጁ በመጨረሻ ውጤት ለመሰብሰብ መምጣቱ የታለመውን ለውጥ ያመጣል ብዬ አላምንም።

ጥያቄ ቁጥር 2፡ የመምህራኑ ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአት ደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው የመማር ማስማሩን ተግባር ያከናውናሉ። ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና በመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መደበኛ ተግባር ላይ መደረቡ መደበኛውን የመማር ማስተማር ተግባር አያውከውም? እንዴት?

መልስ፡- በእርግጥ የተወሰነ ተፅእኖ የለውም ማለት አይቻልም። ተማሪዎችን አነጋግረናል። እጩ መምህራን ብቁ እውቀትና የማስተማር ልምድ እንደሌላቸው በቁመውናል። ለማጆች ቢሆኑም ለማጅነታቸው በህጻናቱ ግንባቤ ሊያገኝ አይችልም። ነገር ግን እጩ መምህራኑ የህጻናቱን ማህበራዊ መሰረት ተረድተው ተግባራቸው መፈጸም ነበረባቸው ነገር ግን አያደርጉትም። እጩ መምህራኑ እራሳቸው የሚሉት ልዩነት አለ። ይኸውም በኮሌጁ ውስጥ የምንማረውና አሁን በተግባር እያየነው ያለነው ነገር ይለያያል። የሚል ነው። ይህም አሰልጣኝ ኮሌጁ የራሱን ክትትልና ፍተሻ ማድረግ እንዳለበት የሚያመለክት ነው። እናም ተፅእኖው በመደበኛ ተማሪዎችም በእጩ መምህራኑም ላይ ይታያል።

ጥያቄ ቁጥር 3፡- እንደሚታወቀው ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡት እጩ መምህራን ቆይታቸው አንድ ወሰነ ትምህርት ነው። በዚህ ቆይታቸው የሚያደርጉት ልምምድ ወደፊት ለሚጠብቃቸው እራስን ችሎ የማስተማር ተግባር የሚያግዝ በቂ እውቀትና ክህሎት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡- ሁኔታውን ካለፈው የስልጠና ሂደት ጋር ማነጻጸር ያስፈልጋል። ቀደም ሲል የነበረው የአሰለጣጠን ልምድ ለአንድ ወር ብቻ በሚደረግ ልምምድ የሚጠቃለል ነባር አሁን ግን አንድ ወሰነ ትምህርት ሙሉ የሚከናወን ተግባር ነው። ይህም በቂ ነው ማለት አይችልም ግን ካለፈው የተሻለ ግንዛቤ ያስጨብጣል ብሎ መግለጽ ይቻላል። ምክንያቱም በዚህ የስድስት ወር ቆይታ ከትምህርት ቤቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴና ከታማሪዎች ባህሪ ጋር ለመላመድ የተሻለ እድል ስለሚፈጥርላቸው ነው።

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርቱ ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን? እንዴት?

መልስ- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲያሰማራ ለእጩ መምህራኑ የሚሰጠው ተልእኮና የሚያስጨብጣቸው ዓላማ ከትምህርት ቤቱ አላማ ጋር የሚጋጭበት ምክንያት የለም ። ምክንያቱም እኛም በዚህ . እጩ መምህራን ስልጠና ሂደት ውስጥ ባለ ድርሻ መሆናችንን ስለመንገነዘብ ነው። በመሆኑም ከተልእኮና አላማ አንጻር ግጭት የለም።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተለዋል?

መልስ፡- ትልቁ ጉድለት ያለው ከዚህ ላይ ነው። አሰልጣኝ ኮሌጆች የሰልጣኞችን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለማስተካከል የሚያደርጉት ጥረት የለም ይህም በሰልጣኙ የስልጠና ሂደት የታየውን አዎንታዊና አሉታዊ ለውጥ ለመለየት አያስችልም። የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለእጩ መምህራን የማያደርጉት የሂደት ግምገማ ሳይሆን የማጠቃለያ ግምገማ ነው። ይህ ደግሞ ሊያመጣ የሚችለው ለውጥ ትክክለኛ ይሆናል ብዬ አልገምትም።

ጥያቄ ቁጥር 6:- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ:- በእኛ ትምህርት ቤት ትልቅ ተሳትፎ እያደረጉ ነው። የመተባበር ድርጊታቸውም 90% ጥሩ ነው ብዬ አምናለሁ። በልዩ ልዩ ተግባራት፣ ክበባትና የጋራ ስራዎች የሚያደርጉት ተሳትፎ አጥጋቢ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 7:- እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉት ምልከታና የገጠማቸውን ችግር ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገፅታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ: እጩ መምህራን በራሳቸው የሚያደርጉት እቅስቃሴ ከተማሪዎች ጋር ግጭት ይፈጠራል። ይህንን ችግር ለመቅረፍም እጩ መምህሩ ከአጋር መምህሩ ጋር በአንድነት ወደ ክፍል መግባት እንዳለባቸው አቅጣጫ በመስጠታችን ችግሩን ቀርፈነዋል። እጩ መምህሩ ብቻውን ሲገባ ግን ችግር አለ።

ጥያቄ ቁጥር 8:- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲሰጡ በአጋርነት ሲመደቡ ለመቀበል የሚያሳዩት ፍላጎት ምን ይመስላል?

መልስ:- ለስልጠኛ የሚመጡት እጩ መምህራን ቁጥር በጣም ብዙ ነው። ብዙን ሀይል ማስተናገድ ደግሞ በጣም አስቸጋሪና ከባድ ነው። በመሆኑም ለአንድ መምህር በርከት ያሉ እጩ መምህራን ሲመደቡለት መሰላቸትና ግዴየለሽነት ያስከትላል። በመሆኑም የትምህርት ቤታችን መምህራንም የተወሰነ ጉርምርምታና ቅሬታ ያሰማሉ።

ጥያቄ ቁጥር 9:- በአጠቃላይ ሲታይ በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ: በዚህ ትምህርት ቤት ደስ የሚለውና ሊበረታታ የሚገባው ነገር በአጋር መምህራኑን በእጩ መምህራኑ መካከል ያለው መግባባት ነው በዚህ መግባባታቸውም ውጤት ይመጣል ብዬ አምናለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 10:- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብካለ ቢገልፁልኝ?

መልስ፡ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አላማው የተሻለ መምህር ማፍራት ነው፡፡ ኮሌጁ የተሻለ መምህር ማፍራት ይችል ዘንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትብብር ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ክፍተት በሁለቱ መካከል አለና ይህ ክፍተት መሞላት ይኖርበታል፡፡ የሚላኩት እጩ መምህራን ቁጥር የትምህርት ቤቱን አቅም ያገናዘበና በቅድመ ስምሪት ጥናት የታገዘ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለአጋር መምህራኑም ማትጊያ ያስፈልጋቸዋልና ይህም ሊታሰብበት ይገባል፡፡

የንኑስ ተክለሃይማኖት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የጉድኝት ሱፐርቫይዘር

እድሜ - 38

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት አይነት- ፔደጎጂክስ

የአገልግት ዘመን- 16ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው፡፡ እርስው ይህ መር ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡- መርሀ ግብሩ ትክክለኛና አስፈላጊ ነው፡፡ በኮሌጁ የሚሰለጥኑ እጩ መምህራን ከመጀሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር በሚፈጥሩት መስተጋብር የንድፈ ሀሳብ እውቀታቸውን በተግባራዊ ልምምድ የሚያግዙበት በመሆኑ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሰማርተው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን መርሀ ግብር ይተገብራሉ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአት በደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው መደበኛ የመማር ማስተማር ተግባራቸውን ያከናወናሉ፡፡ ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያወከውም?

መልስ፦ ከፕሮግራም አንጻር በተጣጣመ መልኩ የሚከናወንና ዋናውን ስራ በማይነካ መልኩ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። ሆኖም ጫና መፍጠሩ አይቀሬ ነው። ስለዚህ የሚፈጠረው ጫና የሚያስከትለውን ችግር ለመቅረፍ ጥረት ይደረጋል።

ጥያቄ ቁጥር 3፡ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ተስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት

መልስ፦ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲመጡ በመጀመሪያ ምልከታ ያዳርጋሉ። በዚህም ሂደት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ አጋር መምህራን አጠቃላዩ የትምህርት ቤት ማህብረሰብ እገዛ እያደረገ የማብቃት ተግባር እንዲከናወን ሁኔታዎችን ስለምናመቻች የሚያገኙት እውቀት በጣም ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልክ የሚሰጣቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውነ?

መልስ፦ የመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ተልእኮ ከሀገራዊ የትምህርት ፖሊስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የተልእኮ ግጭት አይታይም። አላማውም አንድ አይነት በመሆኑ እስካሁን የገጠመን ችግር የለም።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበርን እንዴት ይከታተለዋል?

መልስ፦ የኮሌጁ መምህራን እጩ መምህራኑን ለስልጠና ካሰማሩ በኋላ ተከታታይ ግምገማ አያደርጉም። በመሆኑም የእጩ መምህራንን የባህሪ ለውጥ አያውቁትም። ተልእኮአቸውን የተወጡና ያልተወጡ እጩ መምህራንንም አያውቋቸውም። በመሆኑም ክትትልን በተመለከተ ክፍተት አለ ብሎ ለመናገር ያስደፍራል።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህረት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡ መምህር ሙያው ሁለገብነት ይታይበታል። በመሆኑም ስልጠናው የክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጭም በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። በመሆኑም እጩ መምህራን በክበባት ተሳትፎ፣ በተማሪዎች መልካም ስነ-ምግባር ግምገማ፣ በትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ በትምህርት ቤት ዕዳትና ውበት በመሳሰሉት ላይ ንቁ ተሳትፎ አላቸው።

ጥያቄ ቁጥር 7፦ እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገፅታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡ በተማሪዎችና በእጩ መምህራኑ መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ዝግጅት የጎደላቸውና አቅም ያነሳቸው እጩ መምህራንን ተማሪዎች ሲያማርሩ መስማታችን አልቀረም።

ጥያቄ ቁጥር 8፦ አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፦ እያንዳንዱ እጩ መምህር አጋር መምህር ተመድቦለታል። በመሆኑም አጋር መምህሩ እጩ መምህሩን ለመርዳት ያለው ፍላጎት አወንታዊ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 9፦ በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ፡ በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ ነው በመተጋገዝና በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 10፦ በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ?

መልስ፦ ባለ ድርሻ አካላት በትምህርት ስልጠናው ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው ለምሳሌ ኮሌጁ ለፕራክቲክም አተገባበር ለፕራክቲክም ኮሚቴው ስልጠና ይሰጣል። ስልጠናው ግን እጩ መምህራን ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከተላኩ ከሁለት ወር በኋላ በመሆኑ ከፍተኛ ብክነት ታይቶበታል። የቅድመ ስምሪት ጥናትም በአግባቡ አልተካሄደም የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤትም የበኩሉን እገዛ ቢያደርግ። በሌላ መልኩ ስልጠናው የከተማ ትምህርት ቤቶችንም ቢያካትት ጥሩ ይሆናል።

የአብማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ር/መምህር

እድሜ - 30

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት መስክ - ኬሚስትሪ

የአገልግት ዘመን- 8 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፡ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጣን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው፡፡ እርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት አልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡- እጩ መምህራን በትምህርት ቤታችን ውስጥ አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ፡፡ እንቅስቃሴያቸው ሲለካ ደግሞ እንደየግለሰቦች የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዶቹ በብቁ ችሎታ ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ አሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ተማሪዎች እንዳይገቡብን ብለው የሚታገሏቸው ከእጩ መምህራን አሉ፡፡ በሰአት ገብተው በሰአት የመውጣት ፍላጎት የላቸውም፡፡ የትምህርት ቤቱን ህግጋት አክብረው ለመንቀሳቀስ ፍላጎት የላቸውም በመሆኑም በዚህ ቆይታቸው የሚጠበቅባቸውን ብቃት ተስመዋል ለማለት አልደፍርም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2፡ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሰማርተው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአትና በደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው መደበኛ የመማር ማስተማር ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡ ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውክም?

መልስ፡ ለእጩ መምህሩ የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ መጠን በመመሪያ የተሰጠ ቢሆንም በአንድ የትምህርት አይነት በርካታ እጩ መምህራን ሲመደቡ ለነሱም በቂ ክፍለ ጊዜ ለመስጠት አይቻልም፡፡ በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይም ጫና ይፈጥራልና ችግር አለው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3፡ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ፡፡

በዚህ ቀይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡ ይህ ከላይ የገለፁሁት ነው፡፡ አመዳደባቸው የትምህርት ቤቱን የመቀበል አቅም ያገናዘበ አይደለም፡፡ የፕሮግራም መደራረብ አለ፡፡ የብዙዎቹ ሰልጣኞች የፍላጎት ማነስ ሌላው ችግር ነው በመሆኑም ፕሮግራሙ ከተጣላለት ግብ አኳያ ተገቢውን እውቀት ቀስመዋል ለማለት አልደፍርም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጠም ነውን? እንዴት

መልስ፡- ከተልእኮ አንጻር፣ የሚታይ ችግር የለም፡፡ ችግር የሚኖረው ሰልጣኞቹ የተሰጣቸውን ተልእኮ ለመወጣት ያላቸው ፍቃደኝነትና ተነሳሽነት ላይ ነው፡፡ ብዙዎቹ ተልእኳቸውን በአግባቡ እየተወጡት አይደሉም፡፡ የሚሰሩትን ተግባር ሁሉ እንደ ችሮታ የሚቆጥሩ እጩ መምህራን ብዙ ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- የኮሌጁ መምህራን እጩ መምህራንን የቀን ተቀን ክትትል አያደርጉባቸውም፡፡ በእጩ መምህሩ ላይ ያለውን ለውጥም አያውቁትም፡፡ እንዲያውም በአንድ ወቅት እጩ መምህራት የኮሌጁ መምህሩን «እናንተ እኮ በተናችሁን እንጂ የት እንዳለን አታውቁንም›› ብለው በምሬት ሲወቅሱት ሰምቻለሁ፡፡ የኮሌጁ መምህራን የሚመጡት በሲምስተሩ መጨረሻ ለግምገማ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለለውጥ አያበቃም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6፡ ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- በዚህ አረገድ እጩ መምህራት ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው የሚመጡት ክፍለ ጊዜያቸውን ጠብቀው ብቻ ነው፡፡ ከመጡም በኋላ ከክፍል ከወጡ በኋላ በቡድን ቆመው ከማውራት በስተቀር ከክፍል ውጭ ተግባራት በመማር ጥረት አያደርጉም፡፡ እንዲሰሩ ሲጋብዙም ፈቃደኝነት የላቸውም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 7፡ እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡ በዚህም ረገድ የከፋ ነገር ባይታይም ተጠቃሽ ተግባር የለም እጩል መምህራኑ ራሳቸውን ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ለመቀላቀል የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 8፦ አጋር መምህራኑ ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፡ መደበኛ መምህራን በአጋር መምህርነት ከተመደቡ በኋላ ከእጩ መምህሩ ጋር በክፍ ውስጥ ተገኝተው ድጋፍ ማድግ ሲገባቸው እንደመደበኛ መምህር ብቻቸውን ጥለዋቸው የሚወጡ አጋር መምህራን አሉ፡፡ አንዳንዶቹ መምህራን እጩ መምህራንን በተማሪዎች ፊት የሚያሳጡ እንዳሉም ይታወቃል፡፡ ማመናጨቅና ጥላቻ ማሳየትም አለ፡፡ ይህንንም በየጊዜው በሚደረጉ የጋራ ውይይቶች ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9፦ በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ፦ በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራኑ መካከል ያለው ግንኙነት ከሞላ ጎደል ጥሩ ነው ግን እጩ መምህራኑ እርስ በእርሳቸው እንኳ ተግባብተው አይታዩም ከክፍል ውጭ በሚሆኑበት ጊዜ በወረዳ ተከፋፍለውና ተቧድነው ነው የሚቀመጡ፡፡ ሲላው ቀርቶ ከተለያየ ኮሌጅ የሚመጡ እጩ መምህራን ተግባብተው አይሰሩም፡፡ ይህን በተመለከተ ብዙ ጊዜ ብናማክራቸውም ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 10፦ በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ ቢገልፁልኝ?

መልስ፦ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲወጡ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሀላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የትምህርት ቤቶች አስተዳደር ለሰልጣኞች የሚያሳየውን ግድየለሽነት ማስወገድ አለበት፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የፕራክቲከም ኮሚቴ አዋቅሮ ለሰልጣኞች የሚመች የሰልጠና መርሀ ግብር ማዘጋጀት አለበት፡፡ በመደበኛ ሰልጣኞችና በማታ ተማሪዎች መካከል እየታየ ያለው የመስተንግዶ

ልዩነት መወገድ አለበት። የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ብዙ አጋር መምህራንን በመመደብ እገዛና ድጋፍ ሊሰጥ ይገበዋል። የኮሌጅ መምህራንም በተከታታይ ወደ ስልጣኞ በመምጣት አስፈላጊውን እገዛ ሊያደርጉ ይገባል። የወረዳ ትምህርት ቤቶች ይህን የእጩ መምህራን ስልጠና አያውቀውም። በመርሃ ግብሩም አላካተታቸውም ስለዚህ በተጣይ ተግባሩ ሁኔታውን የሚከታተልበት ስልት ቢዘረጋ ጥሩ ነው።

የአብማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል C/መምህር

እድሜ -42

ፆታ- ሴት

የትምህርት ደረጃ- 10+3

የትምህርት አይነት- ቋንቋ

የአገልግት ዘመን- 24 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠኝ ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብር ነው። እርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራን የማፍራት እልማችንን ያሳካዋል ብለው ያምናሉ?

መልስ፦ በዚህ አጭር ጊዜ ቆይታ ብቁ መምህራን ማፍራት ይችላል ብዬ አላምንም። ምክንያቱም መምህራን ለእጩ መምህራን መልካም አቀባበል የላቸውም ምክንያቱም ልናስተምርበት የምንችለውን ጊዜ ለእጩ መምህሩ ሰጥተን በምንፈልገው መልክ ሊያስተምር ስለማይችል በትምህርት ጥራት ተጠያቂ ያደርገናል የሚል ስጋት አላቸው። ሆኖም መርህ በመሆኑ ተቀብለው እየተገበሩት ነው።

ጥያቄ ቁጥር 2፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ይተገበራሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአትና በደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው የመማር ማስተማር ሂደታቸው ያከናውናሉ። ታዲያ የእጩ መምህራን ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውኩውም? እንዴት?

መልስ- በመደበኛ የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል። ይህንን በተመለከተ መምህራኑም በየጊዜው ጥያቄና እሮሮ ያሰማሉ። ነገር ግን ከላይ የመጣ መርህ በመሆኑ የመፈፀም ግዴታ አለብን በርግጥ የሚያስተምሩት በእቅዱ መሰረት ነው ነገር ግን ውጤታማ ነው ለማለት ያስቸግራል።

ጥያቄ ቁጥር 3፦ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፦ ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርሁት የጊዜ እጥረት፣ የፕሮግራም መደራረብና የፍላጎት አናሳነት ባለበት ሁኔታ በቂ ልምድ ቀስመዋል ለማለት አልደፍርም። ሆኖም ከሙያው ጋር መጠነኛ ትውውቅ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ጥያቄ ቁጥር 4፦ የመምህራ ማሰልተኛ ኮሌጆች እጩ መምህንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን? እንዴት?

መልስ፦ ከተልእኮ አንጻር ሲታይ ብዙም እንቅፋት ሊሆን የሚችል ችግር የለም ነገር ግን ችግሩ የሚመነጨው ተልእኮውን ለመፈጸም ባለው ተነሳሽነት ላይ ነው። እጩ መምህራኑ በአብዛኛው ሲታይ ቆይታቸውን ሸፍነው ውጤት ለማስመዝገብ እንጂ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ሲተጉ አይታዩም ሆኖም አልፎ አልፎ ጥረት የሚያደርጉ እጩ መምህራንም አይጠፉም።

ጥያቄ ቁጥር 5፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፦ የአሰልጣኝ ኮሌጆች ክትትልና ትኩረት አናሳ ነው። ምደባቸው በራሱ የእኛን መርህ ግብር የተከተለ አይደለም። ክትትል የሚባል ነገር የለም ሰልጣኞች የት እንዳሉና ምን እንደሚሰሩ አይቃኙትም። አልፎ አልፎ በእኛ ጠያቂነትና ጎትጓችነት ብቅ ቢሉም የተፈጠረውን ወቅታዊ ችግር ለመፍታት እንጂ የሰልጣኞችን የስልጠና ሂደት ለመቃኘት የሚያደርጉት ጥረት የለም።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- በክበባት ይሳተፋሉ። ተሳትፏቸውም ከፍላጎት የመነጨ ነው። የሁሉም እጩ መምህር ተግባር ባይሆንም አንዳንዶቹ ተማሪዎችን ለመርዳትም ጥያቄ እያዘጋጁ የጥያቄና መልስ ውድድር ያካሂዳሉ። በትምህርት ቤት እንክብካቤም ይሳተፋሉ።

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገፅታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- የእጩ መምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት በክፍል ውስጥ አስጊ ነው የሚባል አይደለም። ምክንያቱም በመካከል አጋር መምህሩ አለና ከክፍል ውጭ ሲታይ ግን እጩ መምህራኑ ገለልተኛ ሆነው ነው የሚታዩት። እርስ በርሳቸው እንኳ ብዙም መግባባትና መቀራረብ አይታይባቸውም።

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ ያላቸው አቀባባል ምን ይመስላል?

መልስ፡- መምህራን እጩ መምህራንን ለመቀበል የሚያሳዩት መጥፎ ገጽታ የለም። ነገር ግን ችግሩ የፕሮግራም መደራረብና የጊዜ ጥበት የፈጠረው ችግር ነው። ለመቀበል የፍላጎት ማነስ ሳይሆን የሚታየው ከላይ እንደጠቀስሁት የጫና መብዛት ነው።

ጥያቄ ቁጥር 9፡- በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ ነው እስከአሁን ባለው ሁኔታ የገጠመን ችግር የለም ይመካከራሉ ይተጋገዛሉም። አጋር መምህራኑ ቅሬታቸው በእጩ መምህራኑ ሳይሆን በፕሮግራሙ ላይ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 10፡- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ ቢገልፁልኝ?

መልስስ- የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ለመተግባር እያንዳንዱ እጩ መምህር በሳምንት ቢያንስ አስር ክፍለ ጊዜ ተመደቦለት ሊለማመድ ይገባዋል የሚል አመራር አለ። ነገር ግን አሁን ከተያያዘነው የትምህርት ጥራት አንጻር ይህ ጎጂ ነውና መስተካከል አለበት የሚመለከተው ክፍል ያስብበት።

የአብማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የትድኝት ሱፐርቫይዘር

እድሜ -31

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት አይነት- ታሪክ

የአገልግት ዘመን- 8 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው። እርስዎ፣ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ?

መልስ- ይህ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ በአግባቡ ከተተገበረ በእጩ መምህራኑ ስልጠና ላይ የበኩሉን እሴት በመጨመር ብቁ መምህር ያደርጋቸዋል ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም በዚህ ፕሮግራም እጩ መምህራኑ የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ያዩበታል፣ ከነበር መምህራን ልምድ ይቀስሙበታል፣ እራስን ችሎ የማስተማር ተግባርን ይለምዱበታል። ነገር ግን ችግር ሆኖ የሚታየው መርሀ ግብሩ በእጩ መምህራኑ፣ በኮሌጆች፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አመራርና በአጋር መምህራን የሚሰጠው ትኩረት የተለያየ መሆኑ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 2፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ መደበኛውን የመማር ማስተማር ተግባር የሚያከናውኑት በሰአትና በደቂቃ በተመጠነ እቅድ እየታገዙ ነው። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ላይ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ልምምድ ሲታከል የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውከውም? እንዴት?

መልስ፡- ሁኔታው በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ጫና መፍጠሩ የማይቀር ነው። እንደ አስረጅ ብናየው በከተማ ውስጥ ባሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በርካታ ተለማማጅ መምህራን ይመደባሉ። በመሆኑም ሁሉም ክፍሎች በእጩ መምህራን ከመያዛቸውም በላይ በአንድ ክፍል ሁለትና ሶስት እጩ መምህራን ይመደባሉ። ይህ ደግሞ ለክትትል ካለማመቸቱም በላይ መደበኛ መምህሩ የያዘውን እቅድ ለመፈጸም እንቅፋት ይሆናል ስለሆነም በጥናት ታግዞ መስተካከል ይኖርበታል ብዬ አምናለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 3፡- እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው እንደ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር የሚያግዝ በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ?

መልስ፡- ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ እንደ እጩ መምህራኑ ተነሳሽነት እንደ ትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር የቅርብ ክትትልና እገዛ የሚለያይ ይሆናል ሆኖም በከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በርካታ እጩ መምህራን መመደባቸውና የሚመደቡት እጩ መምህራን ቁጥር የትምህርት ቤቶችን የመቀበል አቅም ያላገናዘበ መሆን የሚያስከትለው የተግባራዊነት ችግር እንዳለ ሆኖ እንደ ሁኔታው አመቺነት የተለያየ እውቀት ሊያዳብሩ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮ የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን?

መልስ፡- ይህን በተመለከተ ችግር አለ። የእጩ መምህራን ተግባራዊ ፍላጎት ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይጣጣምበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ቤተ ሙከራ በሌለበት ሁኔታ በርካታ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ይላካሉ። እጩ መምህራኑ ሙሉ ጊዜያቸውን በተመደቡባቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማጥፋት እንዳለባቸው በቂ ተልእኮ ስለሌላቸው ክፍለ ጊዜያቸውን ብቻ ጠብቀው ወደ ትምህርት ቤት የመምጣት ዝንባሌ ያሳያሉ። ይህ ሁኔታ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- የኮሌጁ መምህራን እጩ መምህራንን አንዴ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ካስረከቡ በኋላ እንቅስቃሴያቸውን አይከታተሉም። የሚመጡት በመጨረሻው አካባቢ ውጤት ለመስጠት ነው። ይኸውም ቢሆን በጣም አጭር ለሆነ ጊዜ፣ ማለትም ለአንድ እጩ መምህር ከአንድ ክፍለ ጊዜ ላልበለጠ ክትትል ነው። በዚህ በኩል የሚታየው ክፍተት ወደሚፈለገው ግብ የሚደረገውን ግስጋሴ በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳዋል ብዬ እገምታለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- እጩ መምህራኑ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከተገኙ በኋላ የትምህርት ቤቱን እንቅስቃሴ ከመቃኘት ይልቅ ሰብሰብ ብለው ተቀምጠው ማውራት ይመርጣሉ። በተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ሲጠየቁም ብዙዎቹ ፍቃደኞች አይደሉም። ይህ ደግሞ ከመነሻው ሲመጡ ተልእኳቸውን በግልፅ ለማስረዳት እንዳልተቻለ ያመለክታል። ስለዚህ ከክፍል ውጭ ተግባራት ለመማር የሚደረገው ጥረት ክፍተት የሚታይበት ነው።

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራ በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- በተማሪዎችና በእጩ መምህራኑ መካከል ያለው ግንኙነት የከፋ ገጽታ ባይታይበትም እጩ መምህራኑ ወደ ተማሪዎች ቀርበው ትብብርና ትስስር ለመፍጠር ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም። ሁኔታው ገለልተኝነት የሚታይበት እንቅስቃሴ እየተከተሉ እንደሆነ ያሳያል። ይህም በተለያዩ እጩ መምህራን ላይ የተለያየ እንደሆነ ተመልክቻለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፦ ይህን በሁለት መልክ ማየት ያስፈልጋል የተወሰኑ መምህራን በፈቃደኝነት ተቀብለው እጩ መምህራኑን በማገዝና ለማብቃት ጥረት የሚያደርጉ መምህራን አሉ። በተቃራኒው ደግሞ እጩ መምህራን ማስተማር እንደማይችሉ አድርገው የተገነዘቡና ዝቅ አድርገው የሚመለከቷቸው መምህራን አሉ። ከዚህ አንጻር ሲታይ መምህራኑን ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ በአግባቡ እንዳልተሰራ እንረዳለን። እጩ መምህራን በተገቢው መንገድ ተስተናግደው አስፈላጊውን ክህሎት ማግኘት ይኖርባቸዋል የሚል እምነትና አቋም አለኝ።

ጥያቄ ቁጥር 9፦ በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ፦ ከላይ የገለፁሁት ይመስለኛል። ሁለት አይነት ባህሪ ነው ያለው የተወሰኑት በጎ በሆነ መልኩ ተደጋግፈውና ተረዳድተው ሲሰሩ የተወሰኑት ደግ የጎሪጥ እየተያዩ ነው። መምህራንም በተወሰኑት እጩ መምህራን ላይ ምሬት ያሰማሉ። እጩ መምህራንም እንደዚሁ።

ጥያቄ ቁጥር 10፦ በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ

መልስ፦ በዚህ ላይ የምሰጠው አስተያየት ጠቅለል ብሎ ሲታይ የመጀመሪያው የሚሆነው ኮሌጁ እጩ መምህራንን ከማሰማራቱ በፊት የቅድመ ስምሪት ጥናት ማካናወን አለበት። የማያቋርጥ ክትትልና የግምገማ ስልት ተዘርግቶ በእጩ መምህሩ ላይ የሚታየው ለውጥ መመዘን ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ፕሮግራሙ የሚጠበቅበትን ስኬት ሊያመጣ አይችልም።

የእንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር

እድሜ -30

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት አይነት- ባዮሎጂ

የአገልግት ዘመን- 10 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው። በርስው ክትትል ሲያዩት ይህ መርሀ ግብር

ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚመጥኑ ብቁ መምህራንን የማፍራት አላማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡- መርሀ ግብሩ በራሱ ነገ የምንፈልጋቸውን መምህራን ለማፍራት የሚያስችልነው። ነገር ግን በአንድ ትምህርት ቤት የሚመደቡት እጩ መምህራን ብዙ መሆናቸው አፈጻጸሙን አስቸጋሪ አድርጎታል። ለምሳሌ በአንድ ክፍል፣ በአንድ የትምህርት አይነት ሁለትና ከዛ በላይ እጩ መምህራን ይመደባሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ለክትትልም አስቸጋሪ ነው። በተለይም ደግሞ በተማሪዎች ዘንድ ጥሩ ሁኔታ አልፈጠረም። ምክንያቱም የግለሰብ ልዩነት ያለ በመሆኑ ነው። የሚፈለገውን ያህል ጊዜ ሰጥቶ ለማሰራትም አልተቻለም። ይህ መሆኑ ደግሞ አላማችንን ለማሳካት ችግር ይሆና እላለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 2፡ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ። የመጀመሪ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግ በሰአት በደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው የመማር ማስተማር ተግባራቸውን ያከናውናሉ። በዚህ በጊዜ ወሰን በሚከናወነው የመማር ማስተማር ተግባር ላይ የእጩ መምህራት ስልጠና ሲታከል ሂደቱን አያውከውምን? እንዴት?

መልስ- ስልጠናው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ቀላል የማይባል ጫና አለው። እጩ መመህራን ልምድ ስለሌላቸው ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነትና እውቀትን የማስተላለፍ አቅማቸው ዝቅተኛ መሆኑን እክፍል ውስጥ ገብቼ አይቻለሁ። ነገር ግን ይህን ጫና ተሸክመን ስልጠናውን ማካሄድ ካልቻልን ተተኪ ሃይላትን የማፍራት አላማችን አደጋ ላይ ይወድቃል ብለን ስለምናምን ነው ሰልጣኞችን ተቀብለን ለማስተናገድ የፈቀድነው።

ጥያቄ ቁጥር 3፡ እጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በመተግበር ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። ይህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠበቅባቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት

መልስ፡ ሙሉ በሙሉ በቂና የሚጠበቅባቸውን ተግባር መወጣት የሚያስችል ልምድ ቀስመዋል ለማለት እቸገራለሁ። ነገር ግን ልምምዱን ማድረጋቸው ጥሩ ነው ብዬ

አምናለሁ፡፡ ሆኖም ከብቃታቸው ጋር በተያያዘ ተጽእኖ በቂ ጊዜ አግኝተው ለመለማመድ ባለመቻላቸው ሙሉ በሙሉ ሆነው ይወጣሉ ብዬ አላምንም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4፡- መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን? እንዴት ?

መልስ፡- ከተልእኮ አንጻር ሲታይ ልዩነት የለም፡፡ ልዩነቱ አፈጻጸሙ ላይ ነው፡፡ ተልእኮው መፈጸም በሚችልበት ሁኔታ መስጠት አለበት፡፡ የኛን አቅም በቅድመ ስምሪት ጥናት መጥነው አይደለም ሰልጣኞችን የሚልኳቸው፡፡ ስለዚህ አፈጻጸሙ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5፡- መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- ኮሌጆች ያላቸውን ፕሮግራም ባናውቅም አልፎ አልፎ ከመምጣት በስተቀር የእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸውን አይከተተሉም የኮሌጆች ክትትል አነስተኛ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ወደኛ የሚመጡት ውጤታቸውን ለመሰብሰብ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የእለት ተእት ችግራቸውን አይተውና አጢነው ችግሩን ለመቅረፍ ይጥራሉ ማለት አይቻልም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መመህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- ብዙዎቹ እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ ባለው እትስቃሴ ለመለማመድ የሚያደፈርጉት ጥረት ዝቅተኛ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከክፍል ውጭ ከሆኑ ወይ ጥላው ይሄዳሉ፣ ወይ ሰብሰብ ብለው ያወራሉ፡፡ በእኛ በኩል ይህን ተግባር አቋርጠው በክበባትና በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት ተጠቅመው የትምህርት መርጃ መሳሪያ እዲያዘጋጁ አነሳስተናቸዋል፡፡ ሆኖም አሁን ለውጥ እየታየ ቢሆንም የግል ተነሳሽነታቸው ግን በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- መሻሻሎች አሉ ግን ብዙም ያደጉ አይደሉም። በመጀመሪያ እጩ መምህራኑ ከተማሪዎቻቸው ጋር በጎ ያልሆነና ግጭት ያለበት እንቅስቃሴ ነባራቸው ይህ ሁኔታ አሁን በትምህርት ቤቱ አስተዳደርና በአጋር መምህሮቻቸው ጥረት መሻሻል እየታያበት ነው።

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል? አወንታዊ? አሉታዊ? ለምን?

መልስ፡- ብዙዎቹ መምህራን ያላቸው አመለካከት አወንታዊ ነው። ነገር ግን አንዳድ መምህራን ጥሩ አመለካከት ያላቸውም። እኛም ይህን ችግራቸውን እንዲያስወግዱ እንደትምህርት ቤት አመራር ከመምህራኑ ጋር ውይይት አድርገናል። ለውጥም እየታየ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 9፡- በእጩ መምህራኑና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ፡- በእጩ መምህራኑ በአጋር መምህራን መካል ያለው ግንኙነት እንደ አጠቃላይ እይታ ጥሩ ነው ነገር ግን ከላይ ለመግለ እንደሞከርኩት አልፎ አልፎ መጠነኛ ግጭቶች ይከሰታሉ። እነዚህንም ለማስተካከል ተከታታይ ውይይቶችን እያከሄድን ነው ያለነው።

ጥያቄ ቁጥር 10፡- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምዱን በተመለከተ መደረግ አበት የሚሉት ነገር ካለ አስተያየትዎን ቢሰጡ?

መልስ፡- ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ኮሌጆች የቅድመ ስምሪት ጥናት ማድረግና የማስተናገድ አቅማችንን ያገናዘበ ምደባ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ከላይ የጠቀስኩት አይነት ክፍተት ይፈጠርና ወደሚፈለገው ግብ ለመድረስ አዳጋች ይሆናል።

የእንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ም/ር/ መምህር

እድሜ -27

ፆታ- ሴት

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት ዘርፍ- ታሪክ

የአገልግት ዘመን- 7 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው፡፡ እርስው በግል ባደረጉት እይታ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ?

መልስ- መርሀ ግብሩ ጥሩ ነው ነገር ግን የሚመጡት እጩ መምህራንን ብቃት አጠያያቂ ነው ምክንያቱም ፍርሃትና በራስ አለመተማመን ይታይባቸዋል

ጥያቄ ቁጥር 2፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በስአትና በደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው ነው የመማር ማስተማሩን ተግባር የሚያከናውኑት፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውከውም? እንዴት?

መልስ፡- መደበኛ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማብቃት በእቅድ ያከተቱት ጊዜ አለ በዚህ እቅድ ላይ የእጩ መምህራን ተግባራዊ ልምምድ ሲታከልበት ጫና ይፈጠራል፡፡ የመማር ማስተማሩም ሂደት ይታወካል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም የጋራ ፕሮግራች የኛ በመሆናቸው ጫናውን በመሸከም ፕሮግራሙን ለማሳካት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3፡- እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ፡፡ በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው እራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ የሚሆን ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ?

መልስ፡- ሰልጣኞች በዚህ ቆይታቸው የሚቀሰመት ትምህርት መጠነኛ እንጂ በቂ አይደለም፡፡ ሆኖም እራሳቸውን ከእውናዊው የመማር ማስማር ተግባር ጋር ያስተዋውቁበታል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤቱ ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤት ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን? እንዴት?

መልስ፡- ተልእኳቸው ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነው ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም አንደኛ እጩ መምህራኑ እራሳቸው ኮሌጅ የተማርነውና አሁን እያየን ያለነው እውነታ ይለያያል ይላሉ። ሁለተኛው ደግሞ የስልጠናው አላማ ሰልጣኞች ከእውናዊው የመማር ማስተማር ተግባር ጋር እንዲለማመዱ ነው። ነገር ግን እጩ መምህራኑ የሚፈጽሙት ተግባር በራሳቸው ላይ ለውጥ ከማምጣት ይልቅ ማርክ በማግኘት ላይ ያተኮረ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- እስካሁን ድረስ ያለው ልምድ እጩ መምህራኑ ከኮሌጁ ይላኩሉ ወደመጨረሻው አካባቢ በተወሰኑ ቀናት በኮሌጅ መምህራን ይገመገሙና ውጤት ይሞላላቸዋል። ከዚህ ውጭ በየጊዜው እያደረጉት ያለውን ጥረትና ለውጥ ክትትል አይደረግበትም። ሌላው ቀርቶ ከእኛ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንኳ የሚለካ ቅኝት አይደረግም።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- ብዙዎቹ እጩ መምህራን ተጠቃሽ የሆነ እንቅስቃሴ የላቸውም የብዙዎቹ ፍላጎት በተመደቡበት ክፍልና በተመደቡበት ክፍለ ጊዜ ተገኝተው ከግቢው መጥፋት፣ ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር መጫወት ነው። ጥቂቶቹም ቢሆኑ በግፊት የተወሰነ ተግባር እንዲያከናውኑ ሲደረግ ምሬት ያሰማሉ።

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከታትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ ፡- በዚህ እረገድ የተመለከትሁት ጥረትም ሆነ መሻሻል የለም።

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፡- የአጋር መምህራን አመለካከት አሉታዊ ነው። እጩ መምህራኑን አይከታተሏቸውም። እጩ መምህራኑም ቢሆኑ የሚፈልጉት ጥሩ ውጤት

እንዲሞላላቸው እንጂ ከአጋሮቻቸው ልምድ ለመውሰድ ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም በመሆኑም የአጋር መምህራን አመለካከታቸው አሉታዊ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 9፡- በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ፡- እስካሁን ድረስ ያየሁት ሃላፊነትን ለመወጣት የሚደረግ እንቅስቃሴ ካልሆነ በስተቀር ከፍላጎት የመነጨ ድጋፍ ለማድረግ የሚከናወን ተግባር የለም።

ጥያቄ ቁጥር 10፡- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ

መልስ፡- ኮሌጆች እጩ መምህራኑን ግልጽ መመሪያ ሰጥተው ቢያሰማሯቸው የኮሌጁ መምህራን ለምልከታ ሲመጡም ከትምህርት ቤቱ አስተዳድርና ከመምህራን ጋር ግንኙነት ያሚፈጥሩበት ሁኔታ ቢመቻች። አጋር መምህራንም የአመለካከት ችግራቸውን አስወግደው እጩ መምህራኑን ለማገዝ ቢጥሩ። እጩ መምህራንም የተሰማሩበትን ሙያ ለማወቅ ቢጥሩና ተዘጋጅተው የመግባት ልምድ ቢያዳብሩ። ጥሩ ነው ብዬ አምናለሁ።

የእንድማጣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የጉድኝት ሱፐርቫይዘር

እድሜ -28

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት ዘርፍ- ጂኦግራፊ

የአገልግት ዘመን- 9 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው። እርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን ያሳካል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡-አዎ! በኮሌጅ ደረጃ የሚማሩ ሰልጣኝ መምህራን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው በንድፈ ሀሳብ የቀሰሙትን ሙያዊ እውቀት በተግባር መለማመዳቸው ብቃታቸውን ያስድገዋል የሚል እምነት አለኝ።

ጥያቄ ቁጥር 2፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን የሚተገብሩት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች በማስማራት ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በስአትና በደቂቃ የተመጠነ የራሳቸው መደበኛ ተግባር አለባቸው፡፡ ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና መደበኛውን የመማር ማስተማር ሂደት አያውከውምን? እንዴት?

መልስ፡- በርግጥ ተለማማጅ መምህራን ከአጋሮቻቸው ጋር እየተመካከሩና እያረሙ ካልሰሩ በርካታ ችግር ይከሰታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህን ችግር መቅረፍ የሚቻለውም አጋር መምህሩ የእጩ መምህሩን እንቅስቃሴ በንቃት መከታተል ሲችል ነው፡፡ እጩ መምህሩ ከአጋር መምህሩ ውጭ ይንቀሳቀስ ቢባል ግን አስቸጋሪ ወደሆነ ነገር ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3፡- እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ፡፡ በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፡- ይህን ሁኔታ ማየት ያለብን ከምንሰጠው ትኩረት አንጻር ነው፡፡ ትኩረቱ የሶስትዮሽ መሆን አለበት፡፡ እጩ መምህራኑ ወደፊት በስፋት ሊገቡበት ለሚዘጋጁለት የማስተማር ሙያ በቂ ስንቅ ለመያዝ መዘጋጀትና ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶችና አጋር መምህራን በተግባር የሚተረጎም እቅድ አውጥተው አፈጻጸሙን መከታተል አለባቸው፡፡ አሰልጣኝ ኮሌጁም ለመርሀ ግብሩ በትክክል መፈጸም በቂ ክትትልና ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡ በዚህ ስልት የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ ይችላል ብዬ አምናለሁ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልዕኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን?እንዴት?

መልስ- ተማሪዎቹ ወደ አፈጻጸም ሲገቡ ከጀማሪነታቸው አንጻር በርካታ ችግሮ ይገጥማቸዋል፡፡ ችግሩን ለማቃለል የአጋር መምህራን ድጋፍና የሱፐርቪዥን እገዛ ያስፈልጋል፡፡ ሰልጣኞች ይዘዋቸው የሚመጡት ስልቶች አዳዲስና ወቅታዊ ናቸው፡፡ እነዚህን አዳዲስ ስልቶች ለመተግበር ሲሞክሩ ተማሪዎች ላይቀበሏቸው ይችላሉ ፡፡

ይህ በአጋር መምህሩ ካልተስተካከል አስቸጋሪ ይሆናል። ተማሪዎችም ከለመዱት ነገር ወጣ ያለ ስለት ሲያዩ ግራ መጋባትና ነባር መምህራንን የመፈለግ ዝንባሌ ያሳያሉ። ሁኔታው በሂደት የሚስተካከል እንጂ በአንዴ የሚጠራ አይደለም። በየጊዜው መወያየትና ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል

መልስ- በዚህ ደረጃ አሁን ያለው ከነበረው የተሻለ ነው። ቀድሞ ሲል የነበረው የኮሌጅ መምህራን ከሴምስተር አንድ ጊዜ ብቻ ነበር የሚመጡት አሁን ግን በየጊዜው ብቅ እያሉ በአፈጻጸሙ ላይ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር እየተመካከሩ ሂደቱን ቀና ለማድረግ ሲጥሩ አይቻለሁ። ሆኖም አሁንም ቢሆን ኮሌጁ ትኩረት የሰጠው ለፕራክቲከም 1 እና 2 እንጂ ለፕራክቲከም 3 እና 4 አይደለም።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- እነዚህ ሰልጣኞች በኮሌጅ ውስጥ በንድፈ ሀሳብ የተማሩት ነገር አለ። ወደ እኛም ሲመጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አወያይተን ነው ወደ ስራ ያስገባናቸው። ነገር ግን ብዙዎቹ በራስ አነሳሽነት ከመስረት ይልቅ ትእዛዝ የመጠበቅ ባህሪ ይታይባቸዋል። ይህንንም ቢሆን በፍላጎት የመፈጸም ዝንባሌ አይታይባቸውም ። በመሆኑም ትኩረታቸው ውጤት አገኝበታለሁ ብለው በሚያስቡት የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ላይ ብቻ ሆኖ አይቸዋለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ ፡- እጩ መምህራኑ እራሳቸውን ከተማሪዎች ጋር ለማጣጣምና ለማመሳሰል ብሎም በመቀራረብ ላይ የተመሰረተ ተግባር ለማከናወን እያደረጉት ያለው ጥረት ብዙም ተጠቃሽ አይደለም። ነገር ግን ከመነሻው ከነበረው አሁን ያለው የተሻለ ነው። ይኸውም በትምህርት ቤቱ አስተዳደርና በአጋር መምህራን ጥረት የመጣ ለውጥ እንጂ እጩ መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ተቀባይነት ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት የጎላ አይደለም።

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፡- ነባር መምህራን እጩ መምህራኑ እንደኛ አድርገው ሊያስተምሩ አይችሉም የሚል እምነት አላቸው ። ነገር ግን አጋር መምህሩ የእጩ መምህሩን እንቅስቃሴ እየገመገሙ ማስተካከያ እንዲሰጡዋቸው መርሀ ተሰጥቶና ውይይት ተካሄዶ ሁኔታው እየተተገበረ ነው። ሆኖም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ነባር መምህራኑ አወንታዊ አመለካከት አላቸው ለማለት አያስደፍርም።

ጥያቄ ቁጥር 9፡- በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነትስ ምን ይመስላል?

መልስ፡- የእጩ መምህራኑና የአጋሮቻቸው ግንኙነት ከላይ እንደጠቀስሁት አይነት ነው ብዙም በመግባባትና በፍላጎት ላይ የተመሰረት ባይሆንም ሃላፊነትን ለመወጣት የሚደረገው ጥረት የግድ ያስተሳስራቸዋል።

ጥያቄ ቁጥር 10፡- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ

መልስ፡ የመመህራን ኮሌጆች እጩ መምህራኑን ለስልጠና ከመለካቸው በፊት ለሚመለከታቸው ክፍሎች ትውውቅ ቢያደርጉ፤ የሚመደቡት እጩ መምህራን ቁጥር ውሱን ቢሆን፤ በአንድ ትምህርት ቤት በዙ እጩ መምህርን ሲመደቡ አፈጻጸሙ አስቸጋሪ ይሆናል። የኮሌጁ መምህራንም በተከታታይ ወደመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤቶች እየመጡ የማጠናከሪ የማገዝ ተግባር ቢያከናውኑ፣ ይገባል ለጥሩ ውጤት እንበቃለን ብዩ አምናለሁ።

የድብዛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ር/መምህር

እድሜ -54

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+2

የትምህርት ዘርፍ- ቋንቋ

የአገልግት ዘመን- 33 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና

የማስተማር ልምምድ ነው። እርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት እልማችንን የሳከል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፦ አንድ መምህር የንድፈ ሀሳብ እውቀቱን በተግባር ካልሞከረው የማስተማር ተግባሩን በትክክል ለመውጣት ችግር ይፈጥርበታል ብዬ አምናለሁ። ስለሆነም እነዚህ እጩ መምህራን በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ቁጥጥርና ክትትል ያልታለየው የተግባር ስልጠና ቢያደርጉ ብቁ መምህር ሆነው እንዲወጡ ያግዛል ብዬ አምናለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 2፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስማራት የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን ይተገብራሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በሰአትና ደቂቃ የተመጠነ መርሀ ግብር ዘርግተው የመማር ማስተማሩን ሂደት ያከናውናሉ ታዲያ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመማር ማስተማሩን ሂደት አያውከውም? እንዴት?

መልስ፦ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ስልጠና በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የተወሰነ ተጽእኖ አለው። ከተጽእኖዎች አንዱና ዋነኛው በአንድ የትምህርት አይነት ለስልጠና የሚመጡት መምህራን በርካታ ይሆኑና በተማሪዎችና በአጋር መምህራን ላይ መሰላቸት ከመፍጠሩም በላይ በክፍለ ጊዜ ድልድልም በኩል የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ አለው። ስልጠናው በሚካሄድበት ጊዜ የኮሌጆች ክትትል አናሳ መሆን ደግሞ ሌላው ችግር ነው የሚነሱ ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት እንኳ አስቸጋሪ እየሆነ ነው። ሰልጣኞችም ከአጋር መምህሮቻቸው ጋር ተባብሮ የመስራት ፍላጎት አናሳ መሆን ሌላው የችግር ምንጭ ነው። በመሆኑም እነዚህ ሁሉ ችግሮች ተደራርበው መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን ማወካቸው አይቀሬ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 3፦ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ተስመዋል ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፦ ሰልጣኞች የትምህርት ቤቱን ፕሮግራም ከመሻማታቸው ባሻገር ከምንም የተሻለ ልምምድ አድርገዋል ማለት ይቻላል። በተለይም ደግሞ ከህዳር ጀምሮ

በአጋር መምህሮቻቸው ቁጥጥር ስር ራሳቸውን ችለው ማስተማራቸው ለቀጣዩ ስራቸው አጋገር የሚሆን ጭብጥ ነው ማለት ይቻላል።

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን?

መልስ፡-ከኮሌጅ ይዘውት የሚመጡት የእጩ መምህራኑ ተልእኮ ከመደበኛ ትምህርት ቤቱ ተልእኮ ጋር የሚጋጭበት ሁኔታ የለም። ይልቁንም እጩ መምህራኑ በትምህርት ቤቱ ያለውን የባለሙያ እጥረት በመቀነስ በኩል እገዛ እያደረጉ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- ትልቁ ችግር ከዚህ ላይ ነው። አሰልጣኝ ኮሌጆች ሰልጣኞች ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማሰማራት በሴምስተሩ መጨረሻ አካባቢ ለአንድ ወይም ሁለት ቀን ብቅ ብለው ውጤታቸውን ከመመልከት በስተቀር ሰልጣኞች ስልጠናውን እንዴት እያስኬዱት እንደሆነ በመርሀ ግብር የታቀፈ ክትትል አያደርጉም። በመሆኑም በማጠቃለያ ግምገማ ብቻ የመምህራኑን የስልጠና ለውጥ መለከትና ድክመትና ጥንካሬውን መለየት ያስችላል ብዬ አላምንም። በዚህ ረገድ ያለው ልምድ በጥናት ታግዞ ሊሻሻል ይገባዋል ብዬ አምናለሁ።

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- እጩ መምህራኑ በትምህርት ቤቱ የተጓደኝ ትምህርት እንቅስቃሴ ውስጥ ይሳተፋሉ። የትምህርት ቤት ውበትን ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረትም የበኩላቸውን እገዛ እያደረጉ ነው። ነገር ግን በራስ አነሳሽነት ከልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ልምድ ለመከሬል የሚያደርጉት ጥረት የለም ማለት ይቻላል።

ጥያቄ ቁጥር 7፡- እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በተማሪዎቻቸው ዘንድ በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ፡- እስካሁን ያየነው የተማሪዎችና የእጩ መምህራን ግንኙነት ከመደበኛ መምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት አይነት ነው፡፡ አልፎ አልፎ የስነ-ምግባር ጉድለት ያለባቸው እጩ መምህራን ባይጠፉም በአብዛኛው በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 8፡- አጋር መምህራን ለእጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባበላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፡- መምህራን በአጋር መምህርነት ለመመደብ የሚያሳዩት መጥፎ ገጽታ የለም፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ የትምህርት አይነቶች የሚመደቡት እጩ መምህራን ቁጥር ሲበዛ ይህ ለክትትል ስለማያመች እሮሮ ያሰማሉ፡፡ ይህ መታረም የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9፡- በእጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

መልስ፡- በእጩ መምህራንና በአጋሮቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት አወንታዊ ነው፡፡ አጋሮች በአጋዢና አማካሪነት እጩ መምህራኑ ደግሞ በተለማማጅነት ተጋግዘው እየሰሩ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 10፡- በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ?

መልስ- የእጩ መምህራን የፕራክቲከም ስልጠና ወሳኝ ነው፡፡ በቀጣይ ለሚሰማሩበት ሙያ ብቁ ያደርጋቸዋል፡፡ እጩ መምህራን ከሜንቶሮቻቸው ጋር አብሮ የመስራት ልምድ ቢያዳብሩ፣ መደበኛ መምህራንም እጩ መምህራኑን ልምድ በማካፈልና በማበረታታት ቢያስለጥኑ፣ አሰልጣኝ ኮሌጆች እጩ መምህራኑ የተግባር ስልጠና ለሚወስዱባቸው ትምህርት ቤቶች የቁሳቁስ ድጋፍ ቢያደርግ፣የግምገማ ስልቱም የማጠቃለያ ግምገማ መሆኑ ቀርቶ ሂደታዊ የሚሆንበት ስልት ቢዘረጋ፤ በትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብና ብቁ መምህራንን ማፍራት ይቻላል ብዬ አምናለሁ፡፡

የድብዛ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የጉድኝት ሱፐርቫይዘር

እድሜ -28

ፆታ- ወንድ

የትምህርት ደረጃ- 12+4

የትምህርት ዘርፍ- ቋንቋ

የአገልግት ዘመን- 7 ዓመት

ጥያቄ ቁጥር 1፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራንን ለማሰልጠን ከሚጠቀሙባቸው መርሀ ግብሮች አንዱና ዋነኛው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ነው። እርስዎ ይህ መርሀ ግብር ብቁ መምህራንን የማፍራት አልማችን ያሳካል ብለው ያምናሉ እንዴት?

መልስ፦ መርሀ ግብሩ ብቁ መምህራንን የማፍራት አልማችንን ያሳካል ብዬ አምናለሁ። እጩ መምህራኑ አሁን በተግባር እየከወኑት ያለውን ሁኔታ ሳይና ተሳትፏቸውን ስመዝን መርሀ ግብሩ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል መሆኑን እንዳምን ያደርገኛል።

ጥያቄ ቁጥር 2፦ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ መርሀ ግብሩን ተግባራዊ የሚያደርጉት እጩ መምህራኑን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስማራት ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን በስአትና በደቂቃ በተመጠነ እቅድ ታቅፎ ያከናውናል። ታዲያ በዚህ ሁኔታ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና መደረቡ መደበኛውን የመማር ማስተማር ሂደት አያውከውም?

መልስ፦ የእጩ መምህራኑ ተግባራዊ ስልጠና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት አያውከውም ብዬ አልገምትም። ያውከዋል። ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ይህንን ለመቆጣም የራሱን እርምጃ ወስዷል። የፕራክቲክም ኮሚቴ ተቋቁሞ ምደባና ስምሪት ይከናወናል። ችግሩን ለማቃለል ጥረት እየተደረገ ቢሆንም በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚፈጥረው ጫና ቀላል አይደለም።

ጥያቄ ቁጥር 3፦ እጩ መምህራን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጥተው አንድ ወሰነ ትምህርት ይቆያሉ። በዚህ ቆይታቸው ወደፊት ለሚጠብቃቸው ራስን ችሎ የማስተማር ተግባር በቂ ትምህርት ቀስመዋል። ብለው ያምናሉ? እንዴት?

መልስ፦ መንግስት የቀረጸው መርሀ ግብር ቢተርጉም ውጤት ሊኖረው ይችል ነበር።ነገር ግን አፈጻጸሙ ብዙ የሚጎለው ነገር አለ። ኮሌጁ ክትትልና ድጋፍ

አያደርግም፡፡ ነባር መምህራንም የሚሰጡት ድጋፍ ያን ያህል ነው፡፡ በሌላ በኩል እጩ መምህራን በመደበኛነት የሚሰማሩት ገጠር ሆኖ ሳለ በከተማ ትምህርት ቤቶች ተሞክሮ እንዲወስዱ መደረጉ ውጤታማ የሚያደርግ አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ ልምምዱ በገጠር ትምህርት ቤቶች መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እጩ መምህራንን ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ ሲልኩ የሚሰጡዋቸው ተልእኮ ከትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነውን? ምክንያት ካለው?

መልስ፡- ከተልእኮ አንጻር ሲታይ ግጭት የለም፡፡ ነገር ግን እጩ መምህራኑ የትምህርት ቤትን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በጥልቀት ለማወቅ ጥረት አያደርጉም፡፡ ተልእኳቸውም በጥልቀት እንዲፈትሹ የሚጋብዝ አይደለም፡፡ ከተልእኮ አንጻር የሚታየው እጩ መምህራን የትምህርት ቤት ተሞክሮን በጥልቀት እንዲቃኙ የሚጋብዝ አለመሆኑ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5፡- የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የእጩ መምህራኑን የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ አተገባበር እንዴት ይከታተሉታል?

መልስ፡- በዚህ ረገድ ሲታይ የኮሌጅ መምህራን ሰልጣኞችን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ከማስማራት በስተቀር ክትትል ሲያደርጉ አይታይም፡፡ እንዲያውም አጠቃላይ አመለካከታቸው ከውጤት ጋር የተሳሰረ እንጂ ከሰልጣኞቹ የባህሪ ለውጥ አንጻር አልሞ የሚከናወን አይደለም፡፡ በመሆኑም ውጤታማ የክትትል ስልት በኮሌጁ ተዘርግቷል ብዬ አላምንም፡፡ ግምገማቸውም የማጠቃለያ ግምጋማ ነው፡፡ እንጂ ሂደታዊ ክትትል አይደረግም ይህም የራሱ የሆነ ጉዳት አለው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6፡- ለትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚመጡ እጩ መምህራን ከትምህርት ቤቱ የክፍል ውጭ ተግባራት ለመማርና ለመልመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል?

መልስ- ይህን ሁኔታ ከላይ ለመጥቀስ ሞክሪያለሁ፡፡ እጩ መምህራኑ በመጀመሪያ ላይ ለተጓዳኝ የትምህርት እንቅስቃሴዎች በጎ አመለካከትና ተነሳሽነት አልነበራቸውም፡፡ እንዲያውም ‹‹ እኔ ያንተን ክበብ ላንቀሳቅስ አይደለም የመጣሁት፣ እኔ የትምህርት ቤት ጥገናና እድሳት ልሰራ አይደለም የመጣሁ፣ እኔ የተማሪዎችን ስርአት የማስጠበቅ ሀላፊነት የለብኝም፣ ወዘተ›› የሚሉ ሀሳቦችን የሚሰነዝሩ እጩ

መምህራን ጠንቂት አልነበሩም። ሆኖም የፕራክቲከም ኮሚቴው ባደረገው ጥረት እየተለወጠ መጥቶ ሙሉ በሙሉ ወደስራው እንዲገቡ ተደርጓል።

ጥያቄ ቁጥር 7፦ አጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ያደረጉትን ምልከታ ተከትለው ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሻሻልና በጎ ገጽታ ለመላበስ የሚያደርጉት ጥረትስ ምን ይመስላል?

መልስ፦ አጩ መምህራኑ 95% የሚሆኑት ብቁ ችሎታ ኖሯቸው የሚሰሩ ሰሆን 5% የሚሆኑት ደግሞ የአቅም ማነስ ስለሚታይባቸው ተማሪዎች እሮሮ ያሰማሉ እንዲዘሀ አይነቱ ችግር ካልሆነ በስተቀር በተማሪዎችና በአጩ መምህራኑ መካከል የሚታይ የከፋ ችግር የለም። የፕራክቲከም ኮሚቴውም ይህን ሁኔታ ለማስተካከል በትጋት ይሰራል።

ጥያቄ ቁጥር 8፦ አጋር መምህራን ለአጩ መምህራን ድጋፍ እንዲያደርጉ ሲመደቡ አቀባባላቸው ምን ይመስላል?

መልስ፦ ነባር መምህራን ፕሮግራሙ ድካም ከመጨመር በስተቀር በመሰረታዊ አላማው ጠቃሚ እንዳልሆነ አድርገው መመልከታቸው አልቀረም። የአጩ መምህራኑን ምደባ በተመለከተ ግን እንደ አጋርም ስለሚጠቀሙባቸው አልቀበልም የሚል አሉታዊ ምላሽ አይታይባቸውም። በመሆኑም በመምህራኑ ላይ ያለው አመለካከት በስሜትና በተግባር የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን።

ጥያቄ ቁጥር 9፦ በአጩ መምህራንና በአጋር መምህራን መካከል ያለው ግኑኑነትስ ምን ይመስላል፡፡

መልስ፦ በአጩ መምህራኑና በአጋሮቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት አወንታዊ ነው። ምክንያቱም ከላይ ለመግጽ እንደሞከርኩት መምህራን ፕሮግራሙን እንደፕሮግራም ጠቀሜታወን ሲያጣጥሉት ቢታዩም አጩ መምህራኑ በሚያከናውኑት የክፍል ውስጥና የክፍል ውጭ ተግባራት ግን ተጠቃሚዎች ናቸው። በመሆኑም በአጩ መምህሩና በአጋር መምህሩ መካከል ያለው ግንኙነት አወንታዊ ነው።

ጥያቄ ቁጥር 10፦ በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድን በተመለከተ መደረግ አለበት የሚሉት ሀሳብ ካለ?

መልስ፦ የማጠቃለያ ሀሳቡን በሶስት መድቤ ብሰጥ ይመቸኛል። የመጀመሪያው የትምህርት ቤት ተሞክሮና የማስተማር ልምምድ የሚያደርጉት አጩ መምህራን

ናቸው። እጩ መምህራኑ እየፈጸሙት ያለው የልምምድ ተግባር በዘላቂው የመምህርነት ሙያቸው ላይ ያለውን ጠቃሚ ሚና በማሰብ በትኩረት ቢሰሩና የትምህርት ቤቱን የሀላፊነት ሚና ተገንዝበው ቢንቀሳቀሱ ጥሩ ይሆናሉ። ሁለተኛው ደግሞ ኮሌጁና የኮሌጁ መምህራን እያንዳንዱን ነጥብ ትኩረት ሰጥተውና ተከታታይነት ባለው መንገድ የሚፈጽምበት ስልት ቢዘረጋ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ሦስተኛው ደግሞ እጩ መምህራኑን ለስልጠና የሚቀበለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትና የትምህርት ቤቱ መምህራን ሰልጣኞችን የማብቃት ሃላፊነት ያለብን መሆኑን በመገንዘብ በቁርጠኝነት ሰርተው ለመለወጥ ቢንቀሳቀሱ የተሻለ ውጤት ልናገኝ እንችላለን ብዬ አምናለሁ። ይህ ከሆነ ደግሞ ሰልጣኞች በስልጠናው ብቁ እውቀት ሊገነዘቡ እንደሚችሉ እተማመናለሁ።

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬ የሚታየው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ተማሪ ስሆን ይህ የሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያ ጥናት የራሴ ስራና የተጠቀምኩባቸውን ምንጮችም በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም

[illegible]

ፊርማ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ጊዜ የካቲት 2003